# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

84ኛ ዓመት ቁጥር 086 ኅዳር 26 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







## የዓባይ ግድብ ለምስራቅ አፍሪካ ሀገራት የጋራ ተጠቃሚነት ተምሳሌት ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- የዓባይ ግድብ ፕሮጀክት የምስራቅ አፍሪካ ሀገራትን በልማት ያስተሳሰረና የጋራ ተጠቃሚነት ተምሳሌት መሆኑ ተገለጸ። ሀገራዊና አህጉራዊ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የመጀመሪያው የፓርላማ የዜጎች መድረክ በትናንትናው ዕለት ተካሂዷል።

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ተጠሪ ሚኒስትር ተስፋዬ ቤልጅጌ (ዶ/ር) የዓባይ ግድብ የፓን አፍሪካኒዝም መንፈስን ከማጠናከር አንፃር ያለውን ሚና አስመልክተው ባቀረቡት ጽሁፍ፤ የዓባይ ግድብ የሃይል ማመንጫ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያውያን ብሔራዊ ኩራት እና አፍሪካውያንን የሚያስተሳስር የፓን አፍሪካን ፕሮጀክት ነው ብለዋል።

በኢትዮጵያውያን አንጡራ ሀብት የተገነባው ይህ ግድብ የምስራቅ አፍሪካ ሀገራትን በልማት ያስተሳሰረ እና ለጋራ ተጠቃሚነት ምሳሌ የሆነ ፕሮጀክት ነው ያሉት ተስፋዬ (ዶ/ር)፤ አፍሪካውያን አይችሉም የሚለውን ጊዜ ያለፈበት አስተሳሰብ የሰበረ፤ የይቻላል ሰንደቅ ነው ሲሉ ሃሳባቸውን ሰንዝረዋል።

ኢትዮጵያ በዓድዋ የቅኝ አገዛዝ ሥርዓትን በመስበር ምሳሌ እንደሆነችው ሁሉ በዓባይ ግድብም ለአፍሪካውያን የኢኮኖሚ ነፃነት ተምሳሌት ሆናለች ብለዋል።

በመድረኩ ጽሁፍ ያቀረቡት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሃይድሮ ፖለቲክስ ምሁሩ ያዕቆብ አርሳኖ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ በዓባይ ጉዳይ ለዘመናት ኢትዮጵያ በርካታ ተግዳሮቶች እንደገጠሟትና እነዚህንም በጠንካራ የዲፕሎማሲና የፖለቲካ ሥራ እንደታለፉ ገልጸው፤ የዓባይ ግድብን ኢትዮጵያ ለፍፃሜ ምዕራፍ ማቃረቧን አስረድተዋል።

አያይዘውም ለዘመናት የቆዩ ኢ-ፍትሐዊ የናይል ወንዝ ውሎች ተሽረው የናይል የትብብር ማዕቀፍ መጽደቁን አንስተው፤ ይህም ኢትዮጵያ ያስመዘገበችው ትልቅ የዲፕሎማሲ ድል መሆኑን አብስረዋል።

የዓባይ ግድብ ግብጽ ባደረገችው አሉታዊ ተጽዕኖ ምክንያት የውጭ ፋይናንስ እንደማይገኝለት በመታወቁ ለአፍሪካ ምሳሌ በሚሆን መልኩ በመላ ኢትዮጵያውያን አንጡራ ሀብትና ትብብር በስኬት መገንባቱን የገለጹት ደግሞ ሌላኛው ጽሁፍ አቅራቢ አምባሳደር ቶፊክ አብዱላሂ ናቸው።


የዓባይ ግድብ ለምሥራቅ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል










## "እኛ ለዜጎቻችን የምናስበውን ያህል ለግብጾችም ለሱዳኖችም እናስባለን"

**- ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ (ዶ/ር)**
**የውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስትር**



**አስቴር ኤልያስ**

አዲስ አበባ፡- "እኛ ለዜጎቻችን የምናስበውን ያህል ለግብጾችም ለሱዳኖችም እናስባለን፤ ለሁሉም የሚሻለው ባልተገባ መንገድ ወዲህና ወዲያ ማለት ሳይሆን በጠረጴዛ ዙሪያ መነጋገር ነው" ሲሉ የውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስትር ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ (ዶ/ር) አስታወቁ። ከዓባይ ግድብ በኋላ ብዙ የዓባይ ግድቦችን መገንባት እንደሚጠበቅም አመለከቱ።

ኢንጂነር ሀብታሙ (ዶ/ር)፣ በተለይ ከአዲስ ዘመን ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ፤ ኢትዮጵያ ሁሌም የምትከተለው የፍትሃዊ ተጠቃሚነትን መርህ ነው። በምትከተለው መርህ መሠረት ለራሷ ዜጎች እንደምታስበው ሁሉ ለግብጾችም፣ ለሱዳኖችም ታስባለች፡፡

በአሁኑ ወቅትም ለግብጻውያን የሚሻለው ባልተገባ መንገድ ወዲህና ወዲያ ማለት ሳይሆን በጠረጴዛ ዙሪያ መነጋገር ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ጥሩው እና አዋጩ መንገድ የትብብር ማዕቀፉ ነው ብለዋል፡፡ ይህ ሕግ ሆኖ የጸደቀው ማሕቀፍ፤ ሁሉንም የተፋሰሱ ሀገሮች ማስጠለል የሚችል ትልቅ ጥላ ነው ሲሉም አስረድተዋል።

"ግብጾች የዓባይ ግድብ ግንባታ እንዳይሳካ ያላደረጉትና ያልሞከሩት ጥረት አልነበረም፡፡ ዛሬ ሲታይ ግን እነርሱ ያሉት ሳይሆን እኛ ያልነው ትክክል ሆኖ ተገኝቷል፡፡" ያሉት ሚኒስትሩ፤ ግድቡ ሙሉ በሙሉ እነርሱን የሚጎዳ አድርገው ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ሲናገሩ የነበረ ቢሆንም፤ መሬት ላይ ያለው እውነታ ግን እንደንግግራቸው አለመሆኑ በግልጽ ሊታወቅ መቻሉን አመልክተዋል፡፡

እንደሚኒስትሩ ከሆነ፤ ግብጻውያኑ በዚህ ተረትተው የሚቆሙ እንዳልሆነ ከድርጊታቸው መረዳት ይቻላል። አይሳካላቸውም እንጂ በቀጣይም ሌላ ከመሞከር አይቦዝኑም። ቀደም ሲል የዓባይ ግድብ ግንባታ ፍጻሜ እንዳያገኝ በብዙ ደክመዋል፤ ግድቡ ኢትዮጵያን ብዙ ዋጋ ያስከፈላት ቢሆንም ግንባታውን ማሳካት ተችሏል። እውነትን ይዘን አሸናፊ መሆን ችለናል፡፡ አሁንም ማድረግ ያለብን ሥራችንን በአግባቡ መሥራት ነው፡፡

በአሁኑ ሰዓት በዓለም መድረክ ላይ ስለ ዓባይ ግድብ እምብዛም እያወሩ አይደለም፡፡ ያንን ትተው አሁን እያደረጉ ያለው ጎረቤት ሀገሮችን በኢትዮጵያ ላይ ማነሳሳት ነው፡፡ ይህ አካሔዳቸው አያዋጣቸውም ያሉት ሚኒስትሩ፣ ምናልባት ለሕዝባቸው "ኢትዮጵያን እንዲህና እንዲያ አድርገናታል" ለማለት ካልሆነ በስተቀር የሚያተርፉት ነገር አይኖርም፡፡ በዓባይ ግድብ


"እኛ ለዜጎቻችን የምናስበውን... ወደ ገጽ 8 ዞሯል


## የሰላም መንገድ አማራጭ የሌለውና ሁሉንም ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የሰላም አማራጭ የሌለው እና ሁሉንም ተጠቃሚ የሚያደርግ መንገድ መሆኑን ከንቲባ አዳነች አቤቤ ገለጹ፡፡ የኦሮሞ ነጻነት ሠራዊት አባላት ወደ ተዘጋጀላቸው ማዕከላት መግባት መቀጠላቸው ተጠቆመ፡፡

የኦሮሞ ነፃነት ሠራዊት ከፍተኛ አመራር በሆኑት ጃል ሰኚ ነጋሳ የተመራ የሠራዊቱ


የሰላም መንገድ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል



ክህሎት መር ኢኮኖሚ እንዴት ይገነባል? 8





# በክልሉ 346 ሺህ ኩንታል በርበሬ ምርት ለመሰብሰብ እየተሠራ ነው

## - እስከአሁን 125 ሺህ ኩንታን በርበሬ ተሠብስቧል

**ማህሌት አብዱል**

አዲስ አበባ፡- በምርት ዘመኑ ከለማው 26 ሺህ 116 ሄክታር መሬት 346 ሺህ ኩንታል በርበሬ ለመሰብሰብ እየተሠራ መሆኑን ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ቡና እና ቅመማ ቅመም ባለሥልጣን አስታወቀ፡፡ እስከ አሁን ድረስ 125 ሺ ኩንታን በርበሬ መሰብሰቡን አመልክቷል፡፡

በማዕካዊ ኢትዮጵያ ክልል ቡና እና ቅመማ ቅመም ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ ቶፊቅ ጁሃር ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንዳስታወቁት፤ በዘንድሮ የምርት ዘመን በክልሉ ባሉ ዞኖች ሁሉ በርበሬን በስፋት ለማምረት እቅድ ተይዞ ተሠርቷል፡፡ በዚህም 28 ሺህ 467 ሄክታር መሬት ለማልማት ታቅዶ የ26 ሺህ 116 ሄክታር መሬት ለምቷል፡፡ ይህም የእቅዱን 98 በመቶ ማሳካት ተችሏል፡፡

በምርት ዘመኑ በዋናነት ስልጤ፣ ሃላባ ፣ ምስራቅ ጉራጌ በከፊልና ማረቆ አካባቢዎች የበርበሬ ክላስተር ተብለው የተለዩ አካባቢዎች መሆናቸወን አንስተው፤ ‹‹ዘንድሮ የበርበሬን ምርታማነት ለማሳደግ ትኩረት ተደርጎ በመሠራቱ ሃላባ ሰባት ሺህ ሄክታር ፤ ስልጤ ስምንት ሺህ 800፤ ምስራቅ ጉራጌ ሶስት ሺህ 200 ሄክታር መሬት ማልማት ተችሏል›› ብለዋል፡፡ ከእነዚህ አካባቢዎች በተጨማሪ ከዚህ ቀደም በበርበሬ እምብዛም በማይታወቁ በጉራጌ፤ ሃድያና ከንባታ ዞኖች ላይ በስፋት እንዲለማ መደረጉንም ጠቁመዋል፡፡



‹‹የዘንድሮ ምርት ካለፉት ዓመታት ከነበረው ተሞክሮ አንፃር በተሻለ መልኩ ምርታማነት ጨምሯል›› የሚሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ለዚህም በተለይም ምርታማነትን ሊቀንሱ የሚችሉ የበርበሬ በሽታዎችን፣ ተባይና አረሞችን የመከላከል እንዲሁም የማሳ እንክብካቤ ሥራዎች በስፋት መሠራታቸውን አመልክተዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት በቆላና ወይና ደጋ የክልሉ አካባቢዎች ከተመረተው ምርት 125 ሺህ ኩንታን ያህሉን መሰብሰቡን ጠቁመዋል፡፡

የክልሉ ግብርና ቢሮ የኤክስቴሽን ሥርዓቱን በመጠቀምና ከልማት ጣቢያ ባለሙያዎች ጋር በመቀናጀት በቅድመ ሆነ በድህረ ምርት ወቅት የሚያጋጥሙ ብክነቶችን ማስቀረት በሚያስችሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ቤት ለቤት በመዘዋወርና በማሳ ላይ መሠራታቸውንም አስረድተዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት በክልሉ ገበያዎች በርበሬ በ400 ብር እየተሸጠ መሆኑን ጠቅሰው፤ በገበያው ላይ ያልተገባ ንረት በሚፈጥሩ ደላሎችና የተንዛዙ አሠራሮችን ለማስቀረት ከሚመለከታቸው ሴክተር ተቋማት ጋር በቅንጅት እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

‹‹ዘንድሮ በተቻለ መጠን ግብይቱ በህብረት ሥራ አማካኝነት እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ይህ ከተደረገባቸው አካባቢዎች ደግሞ ሃላባ፤ ሥልጤና ጉራጌ ላይ የህብረት ሥራ ዩኒየኖች ከአርሶ አደሩ በርበሬ ገዝተው እንዲያከፋፍሉ ውል ተፈፅሟል›› ሲሉ ጠቁመዋል፡፡

በሌላ በኩልም ከአርሷ አደሩ ጋር በመቀናጀት ዛላውንም ሆነ እሴት ጨምረው ወደ ተለያዩ ሀገራት የሚልኩ ነጋዴዎች ቁጥር መጨመሩን አመልክተው፤ ባለፈው የምርት ዘመን ክልሉ ለውጭ ገበያ ባቀረበው የበርበሬ ምርት ሰባት ሚሊዮን ዶላር ማስገባት መቻሉን አስታውሰዋል፡፡

ዘንድሮ ደግሞ ምርቱንም ሆነ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሬ ለመጨመር ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ ‹‹በተለየ ሁኔታ ዩኒየኖች በወጪ ንግድ (ኤክስፖርት) እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ በግብይት ማዕከላት ጭምር በርበሬ እየገባ ሥራቱን የጠበቀ ግብይት እንዲከናወንና ገበያ የማፈላለግ ሥራ ተሠርቷል›› ብለዋል።



# የለውጡ መንግሥት ዘላቂ ሰላም ለማስፈን የወል ትርክት ለመገንባት እየሠራ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የለውጡ መንግሥት በኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላም ለማስፈንና ልማትን ለማረጋገጥ በውይይት የወል ትርክት ለመገንባት እየሠራ መሆኑን የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ አገኘሁ ተሻገር ገለጹ።

"ሀገራዊ መግባባት ለሕብረ ብሔራዊ አንድነት" በሚል መሪ ሃሳብ የሚከበረው 19ኛው የብሔር ብሔረሰቦች ቀን በክልል ደረጃ የማጠቃለያ በዓል በጎንደር ከተማ ትናንት ተከብሯል።

የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ አገኘሁ ተሻገር በዚሁ ጊዜ እንደገለጹት፤ ብዝኃነት ለሀገራዊ መግባባትና ሕብረ-ብሔራዊ አንድነት መሠረት ነው።

ብዝኃነት የልዩነት ምንጭ እንዲሆን ሲቀነቀን መቆየቱን ገልጸው፥ ይህንን ለመፍታት መወያየት ወቅታዊ አጀንዳ ሊሆን ይገባልም ነው ያሉት።

ለሰው ልጅ መሠረቱ አብሮነት ነው፤ ሀገርም ይገነባል ለዚህም ደግሞ መግባባት መነጋገርና መረዳዳትን ይጠይቃል ብለዋል።

ኢትዮጵያ ሕብረ-ብሔራዊነት የሚስተናገዱባት ሀገር ብትሆንም ነጠላ ትርክት እንቅፋት ሆኖ መቆየቱን ገልፀዋል።

የለውጡ መንግሥት በኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላም ለማስፈንና ልማትን ለማረጋገጥ በውይይት የወል ትርክት ለመገንባት እየሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

የአማራ ክልል ብዝኃ ማንነት የሚከበርበት መሆኑን ጠቅሰው፤ ለሀገረ-መንግሥት ግንባታ የበኩሉን ድርሻ በመወጣት ሀገር ያስቀጠለ መሆኑን ጠቁመዋል።

በቅርቡ በክልሉ ፅንፈኝነት የፈጠረው ችግር በክልሉ በተለያዩ ዘርፎች አሉታዊ ጫና ማሳደሩን ጠቅሰዋል።

የፌዴራልና የክልሉ መንግሥት ተደጋጋሚ የሰላም ጥሪ ማቅረቡን የገለጹት አፈ-ጉባዔው፥ ጫካ የገቡ ልጆቻችንና ወንድሞቻችን በሰላም ወደ ሕብረተሰቡ እንዲቀላቀሉ ማድረግና ሰላሙን ማስጠበቅ ይገባል ብለዋል።

ጎን ለጎንም በጎንደር ከተማ የተጀመሩ የልማት ሥራዎች የሕዝቡን ጥያቄና ፍላጎት የሚመጥኑ መሆናቸውን ገልጸው፥ የልማት ሥራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ ብለዋል።

የአማራ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ፋንቱ ተስፋዬ በበኩላቸው፤ በኢትዮጵያ ሥር የሰደደውን ነጠላ ትርክት በውይይት ለመፍታትና የወል ትርክት ለመገንባት ልምምድ ተጀምሯል ሲል ኢዜአ ዘግቧል።

ኢትዮጵያን አንድነቷ የተጠበቀ የአፍሪካ ተምሳሌት ለማድረግ የተጀመረውን ጥረት አማራ ክልልም አጠናክሮ ይቀጥላል ነው ያሉት።

# በደን ሀብት አያያዝና አጠቃቀም ላይ አዲስ አሠራር ሥራ ላይ ሊውል ነው

**ሰላማዊት ውቤ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ዘላቂ የሆነ የደን ሀብት አያያዝና አጠቃቀም ሥርዓትን ለማስፈን የሚረዳ አዲስ አሠራር ሥራ ላይ እንደሚውል ተገለጸ፡፡ የሚተገበረው አሠራር ዓለም አቀፍ የደን አያያዝና አጠቃቀም መስፈርትን (ስታንዳርድን) ከግምት ያስገባ መሆኑ ተጠቁሟል፡፡

የኢትዮጵያ የደን ልማት ዋና ዳይሬክተር አቶ ከበደ ይማም እንደተናገሩት፤ የደን አስተዳደር ደረጃው የተነደፈው በኢትዮጵያ ዘላቂ የደን አያያዝና አጠቃቀም እንዲኖር ለማስቻል ነው። አሠራሩ ሀገራዊ ሁኔታዎችን ከግምት ያስገባና ዓለምአቀፍ ተቀባይነት ያለው እንደሆነም ጠቅሰዋል፡፡

በደን አያያዝና አጠቃቀም ላይ ቀጣይነት ያለው አሠራርን በማረጋገጥ፣ የአካባቢ ጥበቃን ማጎልበት፣ ዓለምአቀፍ የገበያ ትስስርን መፍጠር እና ጥራት ያለው ምርት ለዓለም ገበያ ማቅረብ እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል፡፡

ኢትዮጵያ የደን ሀብቷን ሽፋኗን እያሳደገች እንደምትገኝ የተናገሩት ዋና ዳይሬክተሩ ፤ ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ ላለፉት ስድስት ዓመታት በአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር ከ40 ቢሊዮን በላይ ችግኞችን መትከሏን ገልጸዋል። ሀገሪቱ በ2017/18 ዓ.ም 50 ቢሊዮን ለማድረስ አቅዳ እየሠራች እንዳለችም አብራርተዋል ፡፡

ችግኞችን ከመትከል ጎን ለጎን ደኖች እንዲጠበቁና በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ ወቅታዊና አስፈላጊ ጉዳይ ስለመሆኑም ጠቅሰዋል፡፡

የኢትዮጵያ የደን ሀብት ዘርፈ ብዙ አስተዋጽኦ ያበረክታል ያሉት አቶ ከበደ፤ አዲሱ አሠራር በይፋ መጀመሩም የኢትዮጵያን የደን ዘርፍ ለማሳደግ ወሳኝ ርምጃ ነው ብለዋል፡፡

አዲሱ አሠራር ደኖች ያለአግባብ እንዳይጨፈጨፉ፤ ይልቁንም ለአካባቢው ሕብረተሰብ ተገቢውን ጥቅም እንዲሰጡ ያደርጋል፤ የጉልበት ብዝበዛን የሚያስቀርና ደኖች ዘላቂ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውሉ



የሚያስችል ስለመሆኑ አስረድተዋል፡፡

በኦሮሚያ ክልል የደንና ዱር እንስሳት ቢሮ የደን ጥበቃና የሕብረተሰብ ተሳትፎ አስተባባሪ አቶ ገነነ ኃይሌ በበኩላቸው ኢትዮጵያ የደን ምርቶችን ጥራት በማስጠበቅ ተጠቃሚ የሆኑ 85 ሀገራትን መቀላቀሏ ጥሩ እድል እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

ደንን ዝም ብሎ መጠበቅ ብቻ ሳይሆን ከላዩ ላይ በአግባቡ መጠቀም ተገቢ ነው ያሉት አቶ ገነነ፤ ለዚህም የአሠራር ሥርዓትን አስቀድሞ ማወቅ ያስፈልጋል ነው ያሉት፡፡ አዲስ የጸደቀው መስፈርት (ስታንዳርድ) ስላለው ጠቀሜታ እና ጥቅም እያንዳንዱ ባለድርሻ አካል ግንዛቤ ጨብጦ ተግባራዊ ሊያደርገው ይገባልም ብለዋል፡፡

የኤፍ.ኤስ.ሲ የምስራቅ አፍሪካ አስተባባሪ ወይዘሮ አናህ አጋሻ፤ የኤፍ.ኤስ.ሲ ‹‹FSC›› ስታንዳርድ በኢትዮጵያ ደን ጥበቃ ላይ በርካታ እንድምታዎች ይኖረዋል ተብሎ እንደሚጠበቅ ተናግረዋል፡፡ ኢትዮጵያ ስታንዳርዱን ተቀብላ ጥቅም ላይ ለማዋል መዘጋጀቷ እያካሄደች ካለችው የአረንጓዴ ልማት ሥራዋ አንጻር ተጠቃሚ ያደርጋታል ነው ያሉት፡፡

የደን ዘርፍ ሥራ አስኪያጆች፣ የመንግሥት ኤጀንሲዎች፣ የንግድ ድርጅቶች፣ የልማት አጋሮች እና ሌሎችም ባለድርሻ አካላት ደረጃውን የጠበቀውን አሠራር በፍጥነት በመከተል የደን ሀብቱን ለማሳደግና ከሀብቱ ሀገራቸውን ተጠቃሚ ለማድረግ እንዲሠሩ ጠይቀዋል፡፡

የደን አስተዳደር ምክር ቤት እና የኢትዮጵያ ደን ልማት ዘላቂ የደን አስተዳደርን ለማንቀሳቀስ ያለመውን የኢትዮጵያን ጊዜያዊ የደን አስተዳደር ደረጃ ይፋ ማድረጋቸው የሚታወስ ነው፡፡

# በሀገሪቱ የሕግና የፍትህ ተቋማት በዘመናዊ መልክ የተደራጁ አይደሉም

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

አዲስ አበባ፡- በሀገሪቱ ሕግና የፍትህ ተቋማት ረዥም ታሪክ ቢኖራቸውም በዘመናዊ መልክ የተደራጁ እንዳልነበሩ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የጥናትና ምርምር ዳይሬክተር አቶ አሮን ደጎል አስታወቁ።

ዳይሬክተሩ የፍትህና ሕግ ኢንስቲትዩትን እንደገና ለማቋቋም በተዘጋጀው አዋጅ ላይ የሕዝብ ውይይት በተካሄደበት ወቅት እንደተናገሩት፤ በሀገሪቱ ሕግና የፍትህ ተቋማት ረዥም ታሪክ ቢኖራቸውም በዘመናዊ መልክ የተደራጁ አልነበሩም።

ተቋማቱን በተመለከተ የሚሠሩ ጥናቶችም በሚፈለገው ደረጃ እንዳልተካሄዱ ፤ የተካሄዱ ጥቂት ጥናቶችም ቢሆኑ በግለሰቦች እጅ እንደነበሩ አመልክተው፤ በዚህም የተነሳም ጥናቶችን መሠረት ባደረገ መልኩ የሕግ ተቋማትን በማጠናከር ረገድ እዚህ ግባ የሚባል ሥራ ሳይሠራ መቆየቱን ገልጸዋል።

የጥናትና ምርምር ሥራዎች ለፍትህ ተቋማት እና ለዳኝነት አካል የሚያስፈልገውን ያህል ትኩረት የተሰጠው አልነበረም ያሉት ዳይሬክተሩ ፤ በተመሳሳይ ሥልጠናንም በተመለከተ ዳኞችን፤ አቃብያነ ሕግን እና በፍትህ ዘርፉ ያሉትን አካላት ብቃት በየወቅቱ እየፈተሸ አቅማቸውን የሚገነባ የተማከለ ተቋም አልነበረም ብለዋል።

ዳኞች፣ ዓቃብያነ ሕግን እና ሌሎች በፍትሕ ዘርፉ ውስጥ የጎላ ሚና የሚጫወቱ የፍትሕ አካላት በአግባቡ ሥልጠና ወስደው ተቋማትን የሚቀላቀሉበት አሠራርም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ እንዳልነበረ ጠቁመው፤ የፍትህና እና የሕግ ባለሙያዎች ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በቀጥታ ወጥተው ተቋማቱን ይቀላቀሉ እንደነበር አመልክተዋል።

ይህ ለፍትሕ ሥርዓቱ መዘመን እና ቀልጣፋነት እንዲሁም ተደራሽነት እና ጥራት ያለው የፍትሕ አገልግሎት ለመስጠት ተግዳሮት እንደነበር አመልክተዋል። ከዚህ የተነሳም በፍትሕ ዘርፉ ላይ በተደራጀ ሁኔታ ጥናት እና ምርምር የሚያካሂድ ተቋም አስፈላጊ ሆኖ መገኘቱን አስታውቀዋል።

አዋጁ ሲጸድቅ የሚፈጠረው አደረጃጀት በእውቀቱ፣ በክህሎቱ፣ በአመለካከቱ፣ እንዲሁም በሥነ-ምግባሩ ብቁ የሆነና የተሟላ ሥብዕና ያለው የዳኝነት እና የፍትህ አካላት አመራር እና ባለሙያ በማፍራት የፍትህ ሥርዓቱ ውጤታማ እንዲሆን እንደሚረዳም ጠቁመዋል።

የዳኝነት፣ የፍትህ አካላትና ሌሎች ከፍትህና ሕግ ሥራ ጋር ግንኙነት ያላቸው አካላትን ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ተደራሽ ለማድረግ ጥናትና ምርምሮችን ማከናወን አስፈላጊ ነው። በዚህም ረገድ አዲሱ አደረጃጀት የሀገሪቱ የፍትህ ዘርፍ የተሰጠውን ተልዕኮ በብቃት እያሳካ ስለመሆን አለመሆኑ አስተማማኝና የተሟላ መረጃ ለመሰብሰብ እና ለማደራጀት የሚያስችል እንደሚሆንም አመልክተዋል።

ከተሰብሳቢዎች የፌዴራል ሼርያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ሼህ ሙሀመድ አዋል ሼርያ ፍርድ ቤቶች በመላው ሀገሪቱ ቢኖሩም ላለፉት አስራ ስድስት ዓመታት ሥልጠና አግኝተው አያውቁም። ፍርድ ቤቶቹ የፍትህ አካል እንደመሆናቸው በአባልነት እንዲካተት ጥያቄ የቀረበ ሲሆን ፤ጥያቄው በማሻሻያው ምላሽ የተሰጠው መሆኑ ተገልጿል።

ተቋሙ በ1990 ዓ.ም «የፍትሕ እና የሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት » በሚል በቀድሞው የአቅም ግንባታ እና በፍትሕ ሚኒስቴር ስር ሲሠራ ነበር። ከ1995 ዓ.ም ተጠሪነቱ ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሆኖ የፍትሕ አካላት ባለሙያዎች የሥልጠና ማዕከል በመባል ለበርካታ ዓመታት ሥልጠና ሲሰጥ ቆይቷል፡፡

በ2010 ዓ.ም ሁለቱም ተቋማት አንድ ወጥ ባደረገ አደረጃጃት የፌዴራል የፍትሕ እና የሕግ ምርምር እና ሥልጠና ኢንስቲትዩት ተብሎ እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡ ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ የፌዴራል ፍትሕ እና ሕግ ኢንስቲትዩት በሚል ተቀይሮ እስከዛሬ ድረስ በዚሁ ስም እየሠራ እንደሆነ መረጃዎች ያመለክታሉ።

# ፖለቲካ ፓርቲዎች አካታች ሀገራዊ ምክክር እንዲደረግ ሚናቸውን እንደሚወጡ ገለጹ

## - ኮሚሽኑ የፖስቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤትን አጀንዳዎች ተረከበ

**ሳሙኤል ወንደሰን**



አዲስ አበባ፡- ፖለቲካ ፓርቲዎች አካታች ሀገራዊ ምክክር እንዲደረግ ሚናቸውን እንደሚወጡ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ሰብሳቢ አቶ ሰለሞን አየለ ገለጹ።

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት በሰባት ክፍሎችና በ64 ዝርዝር ጉዳዮች ላይ ያዘጋጃቸውን አጀንዳዎች ትናንት ተረክቧል።

አጀንዳዎቹን የኮሚሽኑ ዋና ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን አርዓያ ከሌሎች ኮሚሽነሮች ጋር በመሆን በጋራ ምክር ቤቱ ሰብሳቢ አቶ ሰለሞን አየለ ከተመራው የምክር ቤቱ የሥራ አስፈፃሚ አባላት ልዑክ ተረክበዋል።

የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ሰብሳቢ አቶ ሰለሞን አየለ በወቅቱ እንደገለጹት፤ ፖለቲካ ፓርቲዎች አካታች ሀገራዊ ምክክር እንዲደረግ ሚናቸውን መወጣት ይገባቸዋል። የተደራጁት የፖለቲካ ፓርቲዎች አጀንዳዎች ለአካታችና አሳታፊ ሀገራዊ ውይይት የሚያግዙ እንደሚሆኑም አስረድተዋል።

ምክር ቤቱ ያስረከበው አጀንዳ በጠቅላላ ጉባኤ የፀደቀ ነው። በዚህም ታሪክና ትርክት፣ የሀገርና የተቋማት ግንባታ፣ የማንነትና የአስተዳደር ጥያቄዎችን መሠረት ያደረጉ አጀንዳዎችን ለኮሚሽኑ ማስረከቡን ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ከሀገራዊ ኮሚሽኑ ቢጋር እንደሚሠራ ገልፀው፤ በመተባበርና በመከባበር ሀገርን በጋራ እንገነባለን። በዚህ ሂደት ኮሚሽኑ ገለልተኛ ሆኖ እንዲቀጥል ምክር ቤቱ አደራ ሰጥቷል ብለዋል። እውነተኛ ዴሞክራሲ ለመገንባት የፖለቲካ ፓርቲዎች ሚና ወሳኝ መሆኑንም አጽንኦት ሰጥተዋል።

የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን አርዓያ በበኩላቸው፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለሀገራዊ ምክክር ሂደቱ ተባባሪ አካላት ናቸው። በዚህም የጋራ ምክር ቤቱ በጥልቀት ተወያይቶ ያፀደቀውን የውይይት አጀንዳ አስረክቧል ብለዋል።

ሀገራዊ ምክክሩ ሁሉም ክልሎችና ተቋማትን የሚያሳትፍ መሆኑን ገልፀው፤ የተሳታፊ ልየታ፣ መረጣና የአጀንዳ የማሰባሰብ ሥራዎችን በማጠናቀቅ ላይ ነው ብለዋል።

በቀጣይ ጊዜያት የፌደራል ባለድርሻ አካላትና ተቋማት መንግሥትን ጨምሮ አጀንዳ እንዲያስረክቡ ይደረጋል ያሉት ፕሮፌሰሩ፤ በአማራ፣ በኦሮሚያ እና በትግራይ ክልሎች የቀሩ ሥራዎችን በፍጥነት ለማጠናቀቅ እየተሠራ መሆኑን ገልፀዋል።

# የኮሪደር ልማቱ የሚፈጥራቸው ውብና ጽዱ ከተሞች የቱሪስት ፍሰትን ይጨምራሉ

**አመስወርቅ ከበደ**



አዲስ አበባ፡- የኮሪደር ልማቱ የሚፈጥራቸው ውብና ጽዱ ከተሞች ከቱሪዝም ውጭ የሆነውን እንቅስቃሴ ወደ ቱሪዝም እንዲመጣ በማድረግ የቱሪስት ፍሰትን እንደሚጨምሩ የዘርፉ ባለሙያዎች ገለጹ፡፡

በቱሪዝም ማሠልጠኛ ኢንስቲትዩት የቱሪዝም አሠልጣኝ እና ባለሙያ ዐቢይ ንጉሤ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ የኮሪደር ልማቱ በሀገሪቱ ተጨማሪ የቱሪዝም አማራጭ ይፈጥራል ፤ የሚፈጠሩት ውብና ጽዱ ከተሞች ከቱሪዝም ውጭ የሆነውን እንቅስቃሴ ወደ ቱሪዝም እንዲመጣ በማድረግ የቱሪስት ፍሰትን ይጨምራሉ፡፡

ቱሪዝም በሰው ልጅ እንቅስቃሴ ላይ የተመሠረተ እንደመሆኑ ማንኛውም ልማት ለዘርፉ ያለው ሚና ከፍተኛ መሆኑን አመልክተው፤ ለቱሪዝም መስህብ፣ መዳረሻ ቦታዎች፣ ትራንስፖርት፣ የማረፊያ ሥፍራዎች እና የተለያዩ እንቅስቃሴዎች አንኳር የሆኑ ጉዳዮች እንደመሆናቸው የኮሪደር ልማቱ እነዚህን ጥቅሞች ይዞ ይመጣል ብለዋል፡፡

አንድ ሰው ጉዞ ሲያደርግ የሚመለከተው ቦታ ውብና ጽዱ ከሆነ ቦታው በራሱ መስህብ ይሆናል ሲሉም አስረድተዋል፡፡

ከኮሪደር ከልማቱ ጋር ተያይዞ መንገዶች እንዲሰፉ መደረጉ የትራንስፖርት መጨናነቅን ይቀንሳል፡፡ አስጎብኚዎች ቱሪስቶችን ይዘው በከተሞች ጉብኝት በሚያደርጉበት ወቅት የትራንስፖርት መጨናነቅ ካለ ውስን የሆኑ ቦታዎችን ነው የሚያስጎበኙት ያሉት አቶ ዐቢይ፤ የመንገድ መጨናነቁ ሲቀንስ ተጨማሪ ጊዜ ስለሚገኝ ተጨማሪ ቦታዎችን ለማስጎብኘት እድል ይፈጠራል ሲሉ አስረድተዋል፡፡

ልማቱ የማረፊያ፣ የካፍቴሪያ እና የመመገቢያ ሥፍራዎችን ያሟላ መሆኑም፤ አንድ ሰው ጉብኝት ሲያደርግ በእነዚህ ሥፍራዎች አገልግሎት እያገኘ እንዲጓዝ ያስችለዋል፡፡ ጎብኚዎች እየተዝናኑ የእግር ጉዞ ማድረግ እንዲችሉና በሳይክል እየተጓዙ እንዲጎበኙም አመቺ ሁኔታ ተፈጥሮላቸዋል፤ ይህም ለስፖርት ቱሪዝም እድገት አስተዋጽኦ ያደርጋል ብለዋል፡፡

በኮሪደር ልማቱ የተሠሩት ማራኪ የመዝናኛ ሥፍራዎችና ጎዳናዎች የተለያዩ ሁነቶችን ለማዘጋጀት፤ ባህሎችን ለማስተዋወቅ፤ ጽዱ አካባቢን ለመፍጠር እና የፎቶ ግራፍ ሥነ ሥርዓትን ለማከናወን እንደሚጠቅሙም ገልጸዋል፡፡ የማረፊያና የመዝናኛ ሥፍራዎቹ ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድል በመፍጠር ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ያረጋግጣሉም ብለዋል፡፡

ውብና ጽዱ ከተሞች ሲፈጠሩ ከቱሪዝም ውጭ የሆነውን እንቅስቃሴ ወደ ቱሪዝም እንዲመጣ ያደርጋል ያሉት ባለሙያው ፤ በዚህም ለሥራ የመጣ ባለጉዳይ በነገሮች ተስቦ ለመጎብኘት ይገደዳል ነው ያሉት፡፡

ለምሳሌ ጎብኚዎች አዲስ አበባን በአንድ ቀን ጎብኝቶ የማጠናቀቅ እቅድ ቢኖራቸው፤ መስህቦች መጨመራቸውን ተከትሎ የጉብኝት ጊዜያቸውን ሊያራዝሙ ይችላሉ፤ ይህም ተጨማሪ ገቢ ይፈጥራል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የባህል አማካሪው አቶ ተስፋዬ ይመር በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ልማቱ ከባህልና ቱሪዝም አንጻር ያለው ሚና የጎላ ነው፡፡ ከባህል አንጻር ሲታይ የኮሪደር ልማቱ እና እየተሠሩ ያሉ የባህል ተቋማት በዘርፉ ለተሠማሩ አካላት የሥራ እድል በመፍጠር ያገለግላሉ፡፡ በሌሎች ሀገራት በመንገድ ላይ የሚደረጉ ትርኢቶች አሉ ፤ ኮሪደር ልማቱ የተሠሩ ቦታዎች የተለያዩ ኪነ ጥበባዊና ባህላዊ ትርኢቶችን ለማሳየት እንዲሁም ኤግዚቢሽኖች ለማዘጋጀት አስተዋጽኦ አላቸው ብለዋል፡፡

አብርሆት ቤተ መጻህፍትን ጨምሮ ቀደም ሲል ወደ ለሙ ቦታዎች ለመጓዝ የመንገድ መጨናነቅ እንደነበር የጠቀሱት አቶ ተስፋዬ፤ የኮሪደር ልማቱ የቱሪስት ፍሰቱን ከመጨመር አንጻርም ሚናው የጎላ እንደሆነ ጠቅሰዋል፡፡

የአዲስ አበባ የኮሪደር ልማት የሀገር ውስጥ ቱሪስቶችም ቢጎበኙት ለአካባቢያቸው የሚሆን ልምድ ይዘው እንዲሄዱ ያስችላቸዋል፡፡ በከተማው እንደልብ የመንቀሳቀስ እድል ስለሚኖር፤ ተዝናንተው ትውስታን ይዘው መሄድ ይችላሉ ነው ያሉት፡፡

ከዚህ በፊት የውጭ ቱሪስቶች ሲመጡ ከመንገድ መጨናነቅ የተነሳ ወደ መዳረሻቸው ለመሄድ ይቅርና ወደ ኤርፖርት ለመሄድ እንኳ ይቸገሩ ነበር፡፡ አሁን ግን መንገዶች ሠፍተዋል፤ የኮሪደር ልማቱም እንደመዳረሻ ሆኖ ማገልገል ችሏል፡፡ በመንገድ ዳር የሚሠሩ መጸዳጃ ቤቶችና ማረፊያ ሥፍራዎች መኖራቸውም ለቱሪስቶች ምቹ ሁኔታ ፈጠሯል ሲሉ አስተያየታቸውን ሠጥተዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ወደ ሰላም የሚደረግ ጉዞን ማበረታታት ያስፈልጋል !

መላው ሕዝባችን የሚሻውን ብልፅግና እውን ለማድረግ ከሁሉም በላይ ዘላቂ ሀገራዊ ሰላም ያስፈልገናል። ከግጭት አዙሪት ወጥተን ሰላምን በሁለንተናዊ መልኩ ማጣጣም የሚያስችል ማኅበራዊ ፤ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ የአስተሳሰብ ልዕልናን እውን ለማድረግ ም ፤ ለዚህ የሚሆን ዝግጁነት መፍጠር ግድ ይለናል።

የትናንት ተጨባጭ ታሪካችን እንደሚነግረን ፤ በቀደሙት ዘመናት ከነበርንባቸው የሥልጣኔ ማማዎች / ከፍታዎች ያወረዱን እና ዛሬ ላይ ሆነን የተገኘነውን እንድንሆን ያደረጉን በየዘመኑ የነበሩ የሰላም እጦቶች ናቸው። እነዚህ የሰላም እጦቶች ካስከፈሉን ቁሳዊ እና ሠብዓዊ ያልተገባ ዋጋ ባለፈ የእያንዳንዱን ትውልድ ተስፋዎች ነጥቀዋል።

ስለ ራሳቸው ሆነ ስለሀገራቸው ነገዎች ብዙ ህልም የነበራቸውን ትውልዶች ፤ በሰላም እጦት ምክንያት ሕልሞቻችውን መኖር ሳይችሉ ቀርተዋል። ግጭቶች በፈጠሯቸው ግራመጋባቶች ተስፋዎቻቸውን ተነጥቀው ፤ ተስፋ መቁረጥ በፈጠረው ባዶነት ወደመቃብር ወርደዋል፡፡

እንደ ሀገር የመጣንበት የግጭት አዙሪት ማንንም አላተረፈም። የግጭት ምንጭ ከሆኑ የአስተሳሰብ መዛነፎች ያተረፉ የመሰላቸውም ቢሆን ፍጻሜያቸው ያማረበት ሁኔታ አልተፈጠረም። ችግሩ ሀገር እና ሕዝብን ከአንድ የፈተና የታሪክ ምዕራፍ ወደሌላ የፈተና ምዕራፍ ከማሸጋገር ባለፈ ያተረፈው ፋይዳ አልነበረም።

ከለውጡ ማግሥት ጀምሮ ያጋጠመንን ተጨባጭ እውነታ ከዚህ የተለየ አይደለም። ይዘነው ከመጣነው እና በየዘመኑ ብዙ ዋጋ ካስከፈለን የአስተሳሰብ ዝንፈት የተቀዳ ነው። ከትናንት ካለመማራችን የሚመነጭ ፤ ለታሪክ ያለንን የተሳሳተ ግንዛቤ አደባባይ ይዞ የወጣ ፤ ያስከፈለንም ዋጋ በብዙ መልኩ ከቀደሙት ዘመናት የከፋ ነው።

በለውጡ ዋዜማ እንደ አንድ በለውጥ ውስጥ ተስፋን እንደሰነቀ ሀገር እና ሕዝብ ፤ በብዙ መነቃቃት የጀመርነው አዲስ የታሪክ ጉዞ ፤ የተዛነፉ አስተሳሰቦች በፈጠሩት ግራ መጋባት ፤ ግራ መጋባቱ በፈጠረው ጥላ፤ በተለመዱ ፈተናዎች ውስጥ ለማለፍ እና ለመንገጫገጭ ተገድዷል። መንገጫገጩ በፈጠረው ጥፋትም ብዙዎች ከተስፋቸው ጋር ተጋጭተዋል።

የተዛነፉ አስተሳሰቦች እና አስተሳሰቦቹ በወለዷቸው ግራ መጋባቶች ፤ አንዳንዶች አምጠው የወለዱትን የለውጥ አስተሳሰብ ፤ አስተሳሰቡ የወለደውን ተስፋ በአደባባይ በጠብመንጃ አፈሙዝ ተገዳድረዋል። በየዘመኑ የነበሩ ትውልዶችን ተስፋ ባመከነ መልኩ መንገድ ላይ ቆመው የራሳቸውን እና የሕዝባቸውን ከዚያም አልፎ የሀገርን ተስፋ ለማምከን ረጅም ርቀት ተጉዘዋል።

ሁሉም የዜሮ ብዜት ከመሆን ባለፈ እንደ ሀገር የፈጠረልን አንዳች ነገር የለም። በብዙ የመስዋዕትነት ተጋድሎ አሁን ላይ የደረሰችውን ሀገር ህልውና ስጋት ውስጥ ከመጨመር ፤ ስጋቱን ለመቀልበስ ያልተገባ የከፋ ዋጋ ከመክፈል ባለፈ ያመጣልን አዲስ ነገር የለም።

እንደ ትናንቱ ያለንን ከማሳጣት ባለፈ የጨመረልን ምንም ነገር የለም ፤ እንደ ትናንቱ እንደሀገር መኖራችን ሁሌም ስጋት ለሚሆንባቸው ታሪካዊ ጠላቶቻችን፤ ለጥፋት ተልዕኳቸው ተጨማሪ ዕድል ፈጠርንላቸው እንጂ ተስፋችንን ተጨባጭ ለማድረግ አቅም አልሆነንም። እንደ ትናንቱ ለለውጥ መነቃቃታችን ጥላ ሆነን እንጂ ጉልበት አልፈጠረልንም ።

አሁን ግን ከትናንት፤ ከዛም ባለፈ ዛሬ ላይ በራሳችን ከፈጠርናቸው ስህተቶቻችን በመማር ለሰላማችን ተገቢውን ትኩረት ሰጥተን ልንቀሳቀስ ይገባል። ከተዛነፉ አስተሳሰቦች እና አስተሳሰቦቹ ከሚወልዷቸው ግራ መጋባቶች ትውልዱን በመታደግ ፤ የሕዝባችንን የለውጥ ተስፋ ተጨባጭ ለማድረግ ከራሳችን ጋር መታረቅ አለብን።

መላው ሕዝባችን የሚሻውን ብልፅግና እውን ለማድረግ ከሁሉም በላይ ዘላቂ ሀገራዊ ሰላም ለማስፈን፤ ከግጭት አዙሪት ወጥተን ሰላምን በሁለንተናዊ መልኩ ማጣጣም የሚያስችል ማኅበራዊ ፤ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ የአስተሳሰብ ልእልናን እውን ማድረግ ብሎም ለዚህ የሚሆን ዝግጁነት መፍጠር ይጠበቅብናል።

በቀደሙት ዘመናት ከነበርንባቸው የሥልጣን ማማዎች / ከፍታዎች ያወረዱን እና ዛሬ ላይ ሆነን የተገኘነውን እንድንሆን ያደረጉን፤ እንደ ጥላ የሚከተሉን የሰላም እጦቶች በቀጣይ እኛንም ሆነ ቀጣዩን ትውልድ ተመሳሳይ ዋጋ እንዳያስከፍሉ በኃላፊነት መንፈስ ፤ በሰከነ አዕምሮ ልንቀሳቀስ ይገባል ።

ለዚህ ደግሞ አሁን ላይ እየሆነ እንዳለው ፤ በሀገር እና በሕዝብ ተስፋ ላይ ጠብመንጃ አንግበው ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ኃይሎች ወደ ሰላም የሚያደርጉትን ጉዞ በሚቻለው እና ባለው አማራጭ ሁሉ ማበረታታት ያስፈልጋል ፤ ወደዚህ መንገድ ለመምጣት ከቀልባቸው ያልሆኑትንም ወደ ቀልባቸው እንዲመለሱ በተመሳሳይ መልኩ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል!


## አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ
- አልማዝ አያሌው

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የዓለማችን መነጋገሪያ ቢትኮይን


**በቁምላቸው አበበ ይማም(ሞሼ ዳያን)**
fenote1971@gmail.com


**በዓለምአቀፍ የ2008 የፋይናንስ ቀውስ ሀንጎቨር ማግስት፤ ብዙም ትኩረት ያልሳበ የመጀመሪያው ክሪፕቶከረንሲ ቢትኮይን ተጸነሰ፡፡ ቢትኮይን የዲጂታል ክሪፕቶከረንሲ ወይም ገንዘብ ሲሆን፤ ግብይቱም ያለ ባንክ፣ ያለ መንግስት ያለ ፔይፓል ያለ የግል ኩባንያ ተሳትፎ የሚከናወን ነው**

በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት አሜሪካን የክሪፕቶከረንሲ መናኸሪያ አደርጋታለሁ ያሉት ትራምፕ በመመረጣቸው የቢትኮይንን ዋጋ በብዙ እጥፍ ጨምሮ በአንድ ጊዜ 100ሺህ ዶላር ሲገባ፤ሰሞኑን በHBO የቢትኮይን ፈጣሪ ከተሰወረበት በአንድ አነፍናፊ የምርመራ ጋዜጠኛ እንደተደረሰበት የሚዘግብ ሰናጅ ፊልም ስመለከት፤ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተቀባይነት እያገኘ ስላለው ምናባዊ መገበያያ ሀገራችን ምን እያሰበች ይሆን የሚለውን ጥያቄ አስመዝግቤ፤ ስለፋናወጊው ክሪፕቶከረንሲ ቢትኮይንና ሰሞኑን መነጋገሪያ ስለሆነው የዚህ ምናባዊ ገንዘብ ፈጣሪ ላስነብባችሁ ወደድሁ።

ፋና ወጊው አወዛጋቢውና አንዳንድ ጊዜም ግራ አጋቢው ክሪፕቶከረንሲ ቢትኮይን ይፋ እንደተደረገ ይጠፋል አይቀጥልም ተጠንቀቁት ከመባል ሟርት ወጥቶ ሰሞኑን በወጣ መረጃ ሀብቱ 1 ነጥብ 2 ትሪሊየን ዶላር ተገምቷል። ከጠቅላላው የክሪፕቶከረንሲ ሀብት እኩሌታው የቢትኮይን መሆኑን ልብ ይሏል። የአንድ ቢትኮይን ዋጋም ሰሞኑን 100ሺህ የአሜሪካ ዶላርን ተሻግሮ መነጋገሪያ ሆኗል። ታዲያ የዚህን ተአምረኛ ክሪፕቶከረንሲ ፈጣሪ እውነተኛ ማንነት ለማወቅ ሕዝብ አዳም ቢጓጓ ይፈረድበታል።

ብዙዎችም በወቅቱ ደፍረው ቢትኮይን ባለመግዛታቸው እየተቆጩ ነው። የዚህ ተአምረኛ ክሪፕቶከረንሲ ፈጣሪ 60 ቢሊየን ዶላር የሚያወጡ አንድ ሚሊየን ቢትኮይኖች እንዳለው ይነገራል። የዚህ ሰው ማንነት የክፍለ ዘመናችን እንቆቅልሽ እንደሆነ ቀጥሏል። ቢትኮይንን ይፋ ካደረገ በኋላ እምጥ ይግባ ስምጥ አልታወቀም። ተሰውሯል።

በዓለማችን አንቱ የተባሉ የምርመራ ጋዜጠኞች እግራቸው እስኪቀጥን ቢፈልጉትም አላገኙትም። እሱን ለማግኘት ያልፈነቀሉት ድንጋ፤ ያልወጡት አቀበት፣ ያልወረዱት ቁልቁለት የለም። አገኘነው ሲሉ ስለሚሰወር፣ እጃችን ገባ ሲሉ ስለሚያመልጠው፣ ጨበጥነው ሲሉ አረፋ ስለሚሆነው፤ ደረስንበት ሲሉ እንደ አድማስ ስለሚርቀው፣ ሲቀርቡት እንደ ሚራዥ የሚጠፋ መንፈስ ስለሆነው፤ የቢትኮይን ፈጣሪ እነሆ።

ኮቴውን ቢከተሉ ሊደርሱበት ሊያገኙት አልቻሉም። ምን አለፋችሁ የውሃ ሽታ ሆኗል። የክሪፕቶከረንሲ ማኅበረሰብም ከዓመት ዓመት የማወቅ ጉጉቱ እየጨመረ ሄዷል። አድናቂዎቹ ደግሞ እንዲታወቅ አይፈልጉም። ከታወቀ ሕይወቱ አደጋ ላይ ሊወድቅ ይችላል ብለው ይሰጉለታል። ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ደግሞ ትንሽ ፍንጭ ስለተገኘ ሚስጥራዊው የቢትኮይን ፈጣሪ ካናዳዊ ይሆን የሚል ጭምጭምታ እየተሰማ ነው።

HBO ወይም Home Box Office የተሰኘው የበይነ መረብ ፊልምና ተዝናኖት አቅራቢ ይሄን የዘመናችንን ሚስጥር በሉት እንቆቅልሽ የሚፈታ ሰናጅ ፊልም አሰናድቶ እንደገና የፍለጋ ፋይሉን አቧራውን አራግፎ አንቀሳቅሶታል። የካናዳ ዜና ማሰራጫ ወይም በምህጻሩ CBC News ሚስጥራዊው የቢትኮይን ፈጣሪ ካናዳዊ ይሆን እንዴ ብሎ ይጠይቅና፤ በቅርብ የተለቀቀው የHBO ዘጋቢ ፊልም ግን የቢትኮይን ፈጣሪ ካናዳዊ ሳይሆን አይቀርም እያለ ነው ይለናል። በዘወርዋሬ እኔ ግን በነገሩ የለሁበትም ማለቱ ነው።

የቢትኮይን ፈጣሪው ሳቶሺ ናካሞቶ በሚል የሚስጥር ስም ቢታወቅም እውነተኛ ማንነቱ ዛሬ ድረስ ሚስጥር ነው። ካናዳዊው የሶፍትዌር እና የክሪፕቶ ጠበበት ፒተር ቶድ ነው ሳቶሺ ናካሞቶ የሚሉ መረጃዎች እየወጡ ቢሆንም እሱ ግግም ብሎ አይደለሁም እያለ ነው። ቢትኮይን ከተፈጠረና ቨርቹዋል ገንዘብ ከሆነ 15 ዓመታት እንደ ዋዛ የነጎዱ ቢሆንም እንቆቅልሹ ዛሬም አልተፈተታም። የእውነተኛው የቢትኮይን ፈጣሪ ማንነት አልታወቀም ትለናለች የCBC ጸሐፊ አሌክሳንድራ ማኤ ጆንስ።

HBO "Money Electric"በሚል ርዕስ በሰነደው ምርመራዊ ዶክመንተሪ ፒተር የአጽመ ታሪኩ ማጠንጠኛ ሆኖ ቀርቧል። ሆኖም እዚያው በጸበላችሁ እኔ ሳቶሺ ናካሞቶ አይደለሁም እያለ ነው። ሊያውጣጡት ሲሞክሮ ከት ከት ብሎ እየሳቀ ኧረ በፈጠራችሁ ለምን ይሄን የማይመስል ነገር አትተውትም በማለት ይሳለቅባቸዋል። የ39 ዓመቱ ቶድ በዚህ ሰናጅ ፊልም ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው ቀዳሚው ቢሆንም፤ አዘጋጅ ኩሌን ሆባክ በ100 ደቂቃ ሰናጅ ፊልሙ፤ በቢትኮይን ዓለም ተጽዕኖ ፈጣሪ የሆኑ ዝነኞችን፣ ኢንቨስተሮችን እና ቀዳሚ የክሪፕቶከረንሲ ፈጣሪ ከሆኑት አንዱን የብሎክስትሪም ዋና ስራ አስፈጻሚውን አዳም ባክንም አካቶታል። በነገራችን ላይ አዳም ባክ በሳቶሺ ናካሞቶነት ከሚጠረጠሩ የክሪፕቶ ባለሙያዎች አንዱ ነው።

ይህ ሰናጅ ወይም ዘጋቢ ፊልም ባለፈው ሳምንት እንደተለቀቀ ባልተለመደ ሁኔታ በተደጋጋሚ ፒተር ቶድ በx ብቅ ብሎ ሳቶሺ ናካሞቶ አይደለሁም እያለ ቢያስተባብልም፤ ሌሎችም በማኅበራዊ ሚዲያ እሱ ናካሞቶ አይደለም እያሉ የሚፓስቱን ደጋግሞ ቢያጋራም ሰሚ ያገኘ አይመስልም። የሆኑ ጤና ያጡ ንክ ሰዎች ያልሆንሁትን ነው እያሉ ዝናንና ገንዘብን ለማግኘት የባጥ የቆጡን መቀባጠራቸው የማይረባ ትርጉም የሌለው የጅል ወሬ ሲል በብስጭት ይናገራል ቶድ።

ሳቶሺ ናካሞቶነትን የበላ ጅብ ባይጮህም፤ ዛሬ ድረስ እምጥ ይግባ ስምጥ ባይታወቅም የእሱ ድርሻ የእሱ ሀብት ግን እንዳለ ነው ትለናለች የCBC ዘጋቢ አሌክሳንደር። የቢትኮይን ፈጣሪው ሳቶሺ ናካሞቶነት እውነተኛ ማንነት ዛሬም እንደተሰወረ ቢሆንም ሀብቱ ግን በግልጽ ይታወቃል። በዚህ ስሙ አንድ ሚሊየን ቢት ኮይን አለው። አሁን ባለው የገበያ ዋጋ የ60 ቢሊየን ዶላር ባለፀጋ ነው። ሚስጥራዊው ሳቶሺ በሕይወት ካለና ድርሻውን መሸጥ የሚችል ከሆነ እሱም ገዢዎችም በቀላሉ ቢሊየነር ሆኑ ማለት ነው። ይህ ግን ለቢትኮይን ኩባንያ የምስራች ሳይሆን መርዶ ነው ትለናለች አሌክሳንድራ።

ወደ ገጽ 14 ዞሯል

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

# “እነሱ ይጨሁ፤ ከእኛ የሚጠበቀው ሥራችንን አጠናክረን መቀጠል ነው”

- ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ (ዶ/ር)
የውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስትር

አስቴር ኤልያስ

**በኢትዮጵያ ፊት አውራሪነት ሲሰራበት የቆየው የናይል የትብብር ማሕቀፍ ስምምነት በስድስት አገሮች በመፈረሙ ከወራት በፊት ሕግ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ሕግ ሆኖ መጽደቁን ተከትሎ ”የናይል ሪቨር ኮሚሽን” እንደሚቋቋም ሲነገር ቆይቷል፡፡ የዚህ ኮሚሽን መቋቋም ሒደት ምን ይመስላል? ኢትዮጵያ ያላትን የውሃ ሀብት በምን ያህል ልክ እየተጠቀመች ነው? ከዓባይ ግድብ መጠናቀቅ ጋር ተያይዞ ቀጣይ ስራ ምን ይመስላል የሚሉና ሌሎች ጥያቄዎችን አስመልክተን የውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስትር ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ (ዶ/ር)ን የዛሬ የወቅታዊ እንግዳ አድርገናቸዋል፡፡**


ፎቶ፡- ገባቦ ገብሬ

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ በውሃው ዘርፍ ያላት አቅምና ሀብቱን እየተጠቀ መችበት ያለው አካሔድ እንዴት ይገለጻል?**

**ኢንጂነር ሀብታሙ (ዶ/ር)፡-** ኢትዮጵያ 12 ተፋሰሶች አሏት፡፡ ከ12ቱ ተፋሰሶች ለልማት መሆን የሚችል ውሃ ያላቸው ስምንቱ ናቸው፡፡ ስምንቱም ለኃይል ማመንጫነት /ለኃይድሮፓወር/ ከፍተኛ አቅም ያላቸው ናቸው፡፡ ለመስኖ እና ለመጠጥ ውሃም የሚሆኑ ናቸው፡፡

ከዚህ ቀደምም ያለንን የውሃ ሀብት ለኃይል ማመንጫነት፣ ለመጠጥ ውሃና ለግብርና ሥራዎች ስንጠቀምባቸው ቆይተናል፡፡ ይሁንና ለኃይል ማመንጫነት ልንጠቀምበት ከምንችለው ወደ 45 ጊጋ ዋት አቅም ውስጥ እስካሁን እየተጠቀምንበት ያለው ከእስር እና ከአስራ አንድ በመቶ የማይሞላውን ነው፡፡ ይህን ቁጥር ስናይ ብዙ መልማት የሚችል ሰፊ የውሃ ሀብት እንዳለን አመላካች ነው፡፡ በመስኖም በመጠጥ ውሃ ያለን አቅም እንደዚያው ነው፡፡ በጣም ትልቅ ሀብት በእጃችን አለ፡፡ ይህ እምቅ ሀብታችን ነው፡፡

የሀገሪቱ ትልቁ ውሃ ያለው በዓባይ ተፋሰስ ነው። የዓባይ ተፋሰስ የምንለው የዓባይ ወንዝ ያለበትን ነው። በሌላኛው በኩል ስናይ ደግሞ ባሮ አኮቦ ለኃይል ማመንጫነት ሆነ ለመስኖ የሚለማ ቦታ አለው፡፡ ከዚህ ባሻገር እነ ኦሞ፣ ጊቤ፣ ዳዋ፣ ዋቤ ሸበሌ ለኃይል ማመንጫም ለመስኖም የሚሆኑ ናቸው፡፡ የአዋሽ ተፋሰስም እስካሁን ካሉን ተፋሰሶች በጣም የለማና በጣም ትልቅ ሀብት ያለበት ሲሆን በመስኖ ጭምር እየለማ የሚገኝ ነው፡፡

ውሃን በማልማት በኩል በቀዳሚነት የሚጠቀሰው ለኃይል ማመንጫነት ነው፤ ሁለተ ኛው ለግብርና መስኖ ነው፤ ሶስተኛው ደግሞ ለመጠጥ ውሃ፣ አራተኛው ለጎርፍ መከላከል ነው፡፡ ብዙዎች እንደሚያስቡት ጎርፍ አደጋ ሳይሆን በረከት ነው፡፡

ምክንያቱም ጎርፍ ማግኘት ማለት ውሃ ማግኘት እንደማለት ነው፡፡ እኛን የቸገረን ጎርፍን በረከት ማድረግ የሚያስችል አቅም ማጣት እንጂ ክረምት ላይ የሚዘንበውን ዝናብ ይዘን ማቆየት ብንችል በጋ ላይ ለሚያጋጥመን ማንኛውም የውሃ እጥረት እንጠቀምበታለን፡፡

በሌላ በኩል ግድቦቻችንን ስንገነባ ተያይዘው ሊመጡ የሚችሉ በረከቶች አሉ፡፡ ለምሳሌ ዓሳን መጥቀስ ይቻላል። ግድቦቻችን የሚያለሙት መስኖን ብቻ ሳይሆን ዓሳንም ጭምር የሚያመርቱ ናቸው፡፡ ከዚህ ሰፋ ስናደርግ ደግሞ ለቱሪዝም መስህብም መሆን የሚችሉ ናቸው፡፡

ውሃን ማልማት ማለት ከጠቀስናቸው በተጨማሪ ከእነርሱ ጋር ተዛማጅ የሚሆኑ ልማቶችን ማካሔድ መቻልን የሚያካትት ነው፡፡ ከዓሳና ከመዝናኛነት ከማገልገል በተጨማሪ ለትራንስፖርት አገልግሎት መጠቀም እንችላለን፡፡ የውሃን የመልማት አቅም ስናስተውል ሰፋ የልማት ሥራዎችን ታሳቢ የሚያደርግ ነው፡፡ ለአብነትም ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴን ግድብ ትሩፋት ማየቱ ብቻ በቂ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የኢትዮጵያ የውሃ ሀብት አስተዳደር ምን ይመስላል ? ያለንን የውሃ ሀብት በአግባቡ መጠቀም የሚያስችል ስርዓት አለን?**

**ኢንጂነር ሀብታሙ (ዶ/ር)፡-** በሚኒስቴሩ ከተያዙ የስራ ዘርፎች አንደኛ የኢነርጂ፣ ሁለተኛው የመጠጥ ውሃ፣ ሶስተኛው የውሃ ሀብት አስተዳደር ናቸው፡፡ የውሃ ሀብት በመንግስት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት የሚመራ ነው፡፡ የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደርን በመዋቅር ራሱን ችሎ መሬት እንዲረግጥ ለማስቻልም ሰፊ ስራዎች እየተሰሩ ነው፡፡ በሁሉም ተፋሰሶች ማለትም በስምጥ ሸለቆ፣ በአዋሽ እንዲሁም በዓባይ ተፋሰሶች የየራሳቸው ጽህፈት ቤቶች አሉን፡፡

ሶስተኛው ጉዳይ የውሃ ሀብት አስተዳደር ነው፣ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሲባል የአንድ ተቋም ብቻ አይደለም። በጣም ብዙ ተቋማት በቅንጅት የሚሳተፉበት ነው።ግብርና፣ ጤና እና ሌሎችም በፌዴራል ደረጃና በክልል ደረጃ ያሉ አካላት በቅንጅት የሚሰሩት ነው፡፡

ይህን ታሳቢ ያደረገ «የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ስርዓት ማሕቀፍ» የሚባል ረቂቅ አዋጅ ለምክር ቤት አቅርበናል፡፡ ሕግ ጸድቆ ወደ ስራ ሲገባ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሁሉም የሚሳተፉበት የጋራ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ ይህን በማስፈጸም ሂደት ትልቁ ድርሻ የእኛ ነው፡፡

የውሃ ሀብት አስተዳደርን በተመለከተ የኢትዮጵያ ውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር በመዋቅር፣ በአሰራር፣ በሕግና በስርዓት ተደግፎ ወደመሬት እንዲወርድ የሰራቸው ስራዎችና የጀመራቸው በጣም መልካም ክንውኖች አሉ። አሁን ባለን ደረጃ የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደርን ለማሳካት የሁሉንም የውሃ ተፋሰሶች ማስተር ፕላን እየተሰራ ነው፡፡ እየተሰራ ያለው ማስተር ፕላን በእያንዳንዱ ተፋሰስ ውስጥ ምን መሰራት እንዳለበት አመላካች ነው፡፡

ለምሳሌ መንገድ ሲሰራ፣ ከተማም ሲቆረቆር የራሱ ማስተር ፕላን አለው፡፡ ልክ እንደዚያው ከባሮ አኮቦ ውጪ የሁሉንም ተፋሰሶች ማስተር ፕላን ይዘናል፡፡ የባሮ አኮቦ ግን ትንሽ ይቀረናል፡፡ እሱም በዚህ ዓመት ያልቃል። ማስተር ፕላኑ ካለ ሁሉም በፕላኑ መሰረት በአግባቡ ይተገበራሉ፡፡

ለሁሉም የውሃ ልማት የምንመክረው ይህ ተግባራዊ እንዲደረግ ነው፡፡ የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ያለበት ጅምር እንቅስቃሴ በጣም ጥሩ ነው የሚያስብል ነው፡፡ ማሕቀፉ ሲያልቅ እያንዳንዱ ባለድርሻ አካል እንዲሳተፍ ይደረጋል ብለን ተስፋ እናደርጋለን፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ ባላት የውሃ ሀብት መስኖን ጨምሮ ለሁሉም የልማት ሥራዎች እየተጠቀመችበት ነው ማለት ይቻላል?**

**ኢንጂነር ሀብታሙ (ዶ/ር)፡-** በአሁኑ ወቅት እንደድሮ አይደለም፡፡ የትም ቦታ መስኖን መጠቀም ይቻላል፡፡ ከዚህ ቀደም መስኖን ለመጠቀም ረባዳ አሊያም ሜዳማ ቦታ ተፈልጎ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን በቴክኖሎጂ በመታገዝ በተለያዩ የውሃ ጠብታ መሳሪያና በፓምፕም ጭምር በመጠቀም ተራራ ማልማት ይቻላል፡፡

ከውሃም ከአቀማመጥም አንጻር ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ማንኛውም የእርሻ መሬት መስኖ መጠቀምን የሚከለክል አይደለም፡፡ ዋናው በአካባቢው ውሃ መኖሩን ብቻ ማረጋገጥ ነው፡፡ ለምሳሌ በአቅራቢያው ውሃ ከሌለ መሬቱ ቢለማም ትርጉም አይኖረውም፡፡

ስለዚህ እኛ ያለን የውሃ መጠን በአብዛኛው ወደምዕራቡ ነው፡፡ ትልቁን የያዘው የዓባይ ተፋሰስ ነው። የዓባይ ተፋሰስ ከአቀማመጡ የተነሳ ወጣ ገባ ነው፡፡ ስለዚህም ለመስኖ ቀላል የማይሆን ቴክኖሎጂን የሚጠይቅ የመሬት አቀማመጥ አለው። ያንን ማልማት ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ ከውሃ አንጻር ሀብት አለን። ገና ያልተነካ ሰፊ መሬትም አለን፡፡ ለዚህ ደግሞ ባለፉት ዓመታት ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን የጀመሩት የስንዴ ኢንሼቲቭ ትልቅ ማሳያ ነው፡፡ ቀደም ሲል በተለይ ኢትዮጵያ ላይ ስንዴን በመስኖ ማልማት እምብዛም አይታወቅም ነበር፡፡ ይህ ግን በኢትዮጵያ ላይ አሁን ተችሏል፡፡

ውሃ እስካለ ድረስ በጣም ብዙ ቦታ ማምረት ይቻላል። ስንዴ ብቻ ሳይሆን ሩዝም በመመረት ላይ ይገኛል፡፡ ባሮ አኮባ በታችኛው በኩል ብናይ ለሩዝ ልማት የሚመች ነው፡፡ አዋሽ ላይ ስናይ ደግሞ ቀደም ሲል የስንዴ ልማት ያልተለመደ ነበር፤ አሁን ግን በሚያስገርም ሁኔታ ተጀምሯል፡፡ ፍራፍሬም በስፋት እየለማ ነው፡፡ መሬትም ውሃም አለንና በስፋት መጠቀም ይቻላል፡፡ በዚህ ትልቅ ተስፋ አለን፡፡

ውሃ መኖሩ ብቻ ሳይሆን ጥራት ያለው ውሃ መሆኑ ደግሞ በራሱ በረከት ነው፡፡ ጨዋማ የሆነ ውሃ የለንም፡፡ ምክንያቱም የምናገኘው የዝናብ ውሃ እንደመሆኑ በጣም ንጹህ ውሃ ነው፡፡ ይህን በመጠቀም ከፍተኛ ለውጥ ማምጣት ይቻላል፤ ይህም ተጀምሯል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ታዳሽ ኃይል ከማመን ጨት አኳያ ባለን የውሃ ሀብትም ሆነ ከጸሐይ፣ ከነፋስና ከእንፋሎት ምን ያህል መጠቀም ችለናል?**

**ኢንጂነር ሀብታሙ (ዶ/ር)፡-** ኢትዮጵያ በዓለም ደረጃ በጣም ከምትታወቅበት አንዱ ታዳሽ ኃይልን በመጠቀም ነው፡፡ ከዚህ የተነሳ ኢትዮጵያ የታዳሽ ኃይል ምንጭ ባለቤት ነች ማለት ይቻላል፡፡ ከዚህ ውስጥ ትልቁን ድርሻ የሚወስደው ውሃ ነው። ከዚያም ጸሀይ፣ ነፋስ እና እንፋሎት እንደየቅደም ተከተላቸው ታዳሽ ኃይል የሚገኝባቸው ናቸው፡፡

እስካሁን ባለን መረጃ ከውሃ ኃይል ወደ 45 ጊጋ ዋት ኃይል ማመንጨት የሚያስችል አቅም አለን፡፡ እስካሁን ያመረትነው ግን ወደ አራት ነጥብ ስምንት ጊጋ ዋት ብቻ ነው፡፡ ይህ በመቶኛ ሲሰላ አስር በመቶ አካባቢ ነው። እስካሁን ካመረትናቸው ኢነርጂዎች ደግሞ የነፋስም፣ የእንፋሎትም የቆሻሻንም ጨምሮ ስናይ ከውሀ ኃይል የሚመነጨው 92 በመቶ ነው። ትልቁን ድርሻ የሚይዘው ውሃ ነው ማለት ነው፡፡ ተቋማችንም ስያሜውን ‘ውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር’ ያደረገው ከዚህ አኳያ ነው፡፡ ከውሃ ጋር ተያይዞ ኢነርጂ ስለሚጣመር ነው ፡፡

ለአብነት የታላቁ ሕዳሴ ግድብን መጥቀስ ይቻላል። ከግድቡ የሚመነጨው ኃይል ትልቅ ነው፡፡ ይህ ግድብ አልቋል፡፡ ግድቡ ሙሉ በሙሉ ወደምርታማነት ሲገባ ለውጥ ይኖራል፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ኃይል ማግኘት ያለባቸው ኬብሎች ይኑሩ እንጂ የኃይል መቆራረጡ ብዙ ነውና እሱን የሚቀንስ ይሆናል፡፡ የተመረተው ኃይል ያለብክነት በሁሉም አካባቢ እንዲደርስም ማድረግ ይጠበቃል፡፡ እኛ ከምንሰራው ውስጥ አንዱ ይህንን ነው፡፡

ሁለተኛው ደግሞ ከዋናው ቋት ውጭ የሆኑ ማለትም ራቅ ያሉ አሉ፡፡ ኃይል የምናደርሰው ከቋት ውጭ በሆነ ቴክኖሎጂ ነው፡፡ ይህ ሲሆን ደግሞ አንደኛ ምርጫችን የጸሐይ ኃይል ነው፡፡ በርካታ ቦታዎችን ከዚህ አንጻር ለይተናል፣ በርካታ ድጋፍም እያገኘን ነው፡፡ ወጣ ወጣ ያሉ የገጠር ቀበሌዎችንና ከተሞችን ጭምር ሶላር እንዲያገኙ ማድረግ ላይ የምንተገብረው ሁለተኛ ስራችን ይሆናል፡፡

ሶስተኛው ኢነርጂን በመጠቀም የምናመጣቸው አገልግሎቶችን ማሻሻል ነው፡፡ ለምሳሌ የመጠጥ ውሃ ብናይ በየገጠሩ የሚጠቀሙት ጀነሬተርን ነው፡፡ ጀነሬተር ደግሞ አካባቢ የሚበክል ነው፡፡ ነዳጅም እንደልብ አይገኝም፡፡ ስለዚህ እሱን በሶላር መተካት ያስፈልጋል፡፡ ለእሱ የሚሆን ብዙ ቦታ ያለ ከመሆኑ በተጨማሪ በቅርቡም ብዙ ሥራዎች ተጀምረዋል፡፡

ሌላው ከነፋስ ኃይል ጋር በተገናኘ የግሉ ባለሀብት በዘርፉ ለመሳተፍ ፍላጎት እያሳየ ነው፤ ለምሳሌ አይሻ ላይ የተሰራው ስራ አለ፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ እንደ አገር የተፈራረምናቸው ውሎች አሉ፡፡ ባለሀብቱ በዘርፉ መሳተፍ የሚያስችለው እድልም አለ፡፡

በጥቅሉ በኢነርጂ ላይ አንዱና ትልቁ ስራችን ከውሃ ኃይል ማመንጨት ነው፣ ትልቁን ድርሻ መያዙ እንደተጠበቀ ሆኖ የሶላርንና የነፋስን ድምር ውጤት ማሻሻል የሚጠበቅብን ይሆናል፡፡ ሶላር እስካሁን ባለው ደረጃ ሲታይ በጣም ትንሽ ነው፡፡ ስለዚህ እሱን ከፍ ማድረግ አለብን፡፡ ከውሃ ኃይል ማመንጨትን ግን አጠናክረን የቀጠልነው ሥራችን ነው ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በዚህ ዓመት ጥቅምት ወር ላይ ጸድቆ ወደስራ የገባው የናይል ተፋሰስ አገሮች የትብብር ማዕቀፍ ስምምነት ሕግ ሆኗል፤ ኢትዮጵያ የውሃ ሀብቷን በአግባቡ ማልማት እንድትችል ምን አዲስ ነገር ይዞ መጥቷል?**

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ወቅታዊ

## “እነሱ ይጩሁ፣ ከእኛ የሚጠበቀው ሥራችንን...

ከገጽ 6 የዞረ

**ኢንጂነር ሀብታሙ (ዶ/ር)፡-** ይህ ማሕቀፍ በተፋሰሱ ውስጥ ያሉ አገሮች የወንዙን ውሃ በጋራ ለመጠቀም የራሳቸው ሕግ ማድረግ ማለት ነው፡፡ በዓለም ላይ ባለው ተሞክሮ በጣም ብዙ ቦታ በሚባል ደረጃ ይህ ሕግ እንዲሰራ መፈለግ ያለባቸው አገሮች የታችኞቹ ናቸው፡፡

ምክንያቱም ሕጉ የእነርሱን ጥቅም የሚያስከብር ነውና፡፡ ኢትዮጵያ የላይኛው ተፋሰስ አገር ብትሆንም ጉዳዩ ፍትሃዊ እንዲሆን ለማድረግ እና ማሕቀፉ ስኬታማ እንዲሆን በጋራ ከሌሎቹ አገሮች ጋር በመሆን ትልቅ ስራ ስትሰራ ቆይታለች፡፡ ተሳክቶላትም ባለፈው ጊዜ ሕግ መሆን ችሏል፡፡

ሕግ ከሆነ በኋላ  አገራት በሙሉ የሚገዙት በዚህ ሕግ ሆነ ማለት ነው፡፡ ሕጉ ደግሞ እንዴት አድርጎ ውሃን መንከባከብ እንደሚቻል፣ እንዴት አድርጎ ውሃውን መጠበቅ እንደሚገባ፣ እንዴት አድርገው መረጃ እንደሚለዋወጡ የሚያስገድዷቸውን ስርዓት ያካተተ ነው፡፡

ውጤቱ  እኛ የምንኮራበት ነው፤ አሳክተነዋልም፡፡ ምክንያቱም ወደ ስድስት የሚሆኑ አገራት ይህንን ፈርመው በአገር ደረጃ ሕጋቸው አድርገውታል፡፡ በቀጣይ ሕጉን ተግባራዊ የምናደርግበት ተቋም ያስፈልገናል፡፡ እሱም ተቋም የ”ናይል ሪቨር ኮሚሽን” የሚባል ነው፡፡ የሚቀረውም እሱን ማቋቋም ነው፡፡

ኮሚሽን ሲቋቋም የሕጉን ተፈጻሚነት ይከታተላል፡፡ በአሁኑ ወቅት ያለን የናይል ተፋሰስ ሀገራት የትብብር ማሕቀፍ (ናይል ቤዚን ኢንሼቲቭ) ነው፡፡ ይህ ኢንሼቲቭ ሀገራት ወደውና ፈቅደው የሚሳተፉበት እንጂ አስገዳጅ ሕግ የለውም፡፡ እንዲሁ በመሰባሰብ የሚወሰኑ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ኮሚሽን ከሆነ ግን አቅም ያለው ይሆናል፡፡ ስርዓት አለው፤ ተጠያቂነትን ያረጋግጣል፡፡

አሁን ያንን ኮሚሽን ለማቋቋም እንቅስቃሴ ጀምረናል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም በቅርቡ ዑጋንዳ ኢንቴቤ ላይ አንድ ስብሰባ ነበረን፡፡ በስብሰባው ላይ የተገኘው ስብስብ የውሃ ሚኒስትሮች ካውንስል የሚባለው ነው፡፡ በስብሰባችን ወቅት አንድ ሀሳብ አቅርበናል፡፡

ያቀረብነው ሀሳብ የታችኞቹ አገሮች እና ሌሎቹ ያልፈሩሙ አገሮች እንዲፈርሙ ማግባባት ላይ ነው፡፡ ለዚህ ሥራ ደግሞ ኮሚቴ ተዋቅሯል፡፡ በእኛ እምነት የትኛውም የተፋሰሱ አገር ከዚህ ውጭ መሆን የለበትም፡፡  ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ይጠቀሙበታል ብለን ማመናችን ነው፡፡

ሁለተኛው ስምምነቱን  የፈረሙት ስድስቱ አገራት የኮሚሽኑን አካሔድና በቀጣይ  እንዴት መቋቋም አለበት በሚለው ላይ መነሻ ሰነድ ማዘጋጀት ነው፡፡ ለዚህም ኮሚቴ አዋቅረናል፡፡ ይህንን እናሳካዋለን ብለን እናምናለን፡፡ እንደ አገር ካየን ግን የትብብር ማሕቀፉ ከእኛ በላይ ተጠቃሚ የሚያደርገው ሌሎቹን ነው፡፡ እንዲያውም ከእኛ በላይ ማሕቀፉ ስኬታማ ይሆን ዘንድ ጫና መፍጠር የነበረባቸውም፣ ያለባቸውም እነርሱ መሆን ነበረባቸው፡፡

በተለይ ግብጽና ሱዳን ያንን ማድረግ አለባቸው፡፡ እኛ አሁን እያንዳንዱን ውሃ ወይም የፈለግነውን ውሃ እንጠቀማለን ካልን የሚያስገድደን ሕግ የለም፡፡ ምክንያቱም መጠቀም መብታችን ነው፡፡ ማሕቀፉ ሲመጣ እኛን አያግደንም፡፡ ምክንያቱም እኛ የምናምነው በፍትሐዊ ተጠቃሚነት ነው፡፡ ሁሉም ይጠቀም የሚል አመለካከት አለን፡፡

ለእኛ ትልቁ ስኬት ከማሕቀፉ ሕጋዊ መሆን ጋር በተያያዘ ቀድሞ የነበሩ ሕጎች  መሻራቸው ነው፡፡ ለምሳሌ የ1959ኙን ሕግ ሁለት አገሮች ብቻ ወስነው እንዳሻቸው የሚያደርጉትን አካሔድ ለውጦታል፤ ለእኛ ይህ ትልቅ ስኬት ነው፡፡ በቀጣይ ደግሞ ኮሚሽኑ ከመጣ እሰየው ነው፡፡ መምጣትም አለበት፤ እኛም እንደግፈዋለን፡፡ ይህ ሕግ ግን ለእኛ ሰላም የሚሰጥ ነው፤ ለሁሉም የሚጠቅም ነው፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይ አንድ መጥቀስ የምሻው፣ አሁን ከኢትዮጵያ ውጪ ብዙ አገሮች ስለማሕቀፉ ሆነ ስለኮሚሽኑ ስለገባቸው ተፈጻሚነቱ እንዲፋጠኑ እየተንቀሳቀሱ ነው፡፡ እኛም የምንፈልገው ይህንኑ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ፍትሃዊነት የሚለውን ቃል ዑጋንዳ እና ደቡብ ሱዳን በማቀንቀን ላይ ናቸው፡፡ ቀደም ሲል ስለፍትሃዊነት ስንጮህ የነበረው ብቻችንን ነበር፤ በአሁኑ ወቅት አጋዥ አግኝተናል፡፡ በአሁኑ ወቅት ስድስት አገሮች ስምምነቱን ፈርመው የሀገራቸው ሕግ አካል ስላደረጉት፤ ስለዓባይ በአግባቡ በዓለም መድረክ ላይ ማውራት ጀምረዋል፡፡ ይህ ለኢትዮጵያ ትልቅ ስኬት ነው፡፡



በዚያው ልክ ደግሞ ፈተናዎች አሉብን፡፡ የታችኞቹ አገሮች ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ፤ ሚዲያዎችንም በመጠቀም ጭምር በተለይ ግብጽ የትብብር ማሕቀፉን ማጣጣሉን ተያይዘዋለች፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም ምንም አይነት ገንዘብም ሆነ ድጋፍ እንዳይገኝ በተለያየ ቦታ በመንቀሳቀስ የማከላከል ሥራ እየሰሩ ይገኛሉ፡፡  ይህን ጉዳይ እኛ በአግባቡ ተረድተን መግለጽና ማስረዳት አለብን፡፡ ምክንያቱም ሌሎቹ እንዲረዱ ማድረጉ አስፈላጊ ነው፡፡ ፈተናም ያለብን እዚህ ላይ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ግብጽ ዛሬም የነበረ ጠላትነቷን ቀጥላለች፤ ይህ ምን ያህል ትርፋማ ያደርጋታል ይላሉ?**

**ኢንጂነር ሀብታሙ (ዶ/ር)፡-** ትርፍ አታገኝ በትም፤ እንዲያውም ይህን በማድረጓ ተሸናፊ ናት፡፡ ምክንያቱም ከዚህ ቀደምም እኛ አሸንፈን ስለምናውቅ ነው፡፡ የዓባይ ግድብ ላይ ያላደረጉትና ያልሞከሩት ክፋት አልነበረም፡፡ ዛሬ ሲታይ ግን እነርሱ ያሉት ሳይሆን እኛ ያልነው ትክክል ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ገና ከጅምሩ ኢትዮጵያ የሕዳሴ ግድብን ስትጀምር፤ ግብጽ  ኢትዮጵያ ግድቡን የጀመረችው እኛን ለመጉዳት ነው አለች፡፡ ዛሬ የዓባይ ግድብ ከበፊት ይልቅ ከነበረው የውሃ መጠን አራት እጥፍ የሚለቅላቸው ሆኗል፡፡ ከሶስት ሳምንት በፊት ወደ ሕዳሴ ግድብ አምባሳደሮችን ይዤ ሄጄ ነበር፡፡ አምባሳደሮቹ ባዩት ነገር በጣም ሲገረሙ ነበር፡፡

ለግብጻውያን የሚሄደው የውሃ መጠንንም በግራፍ በማየታቸው “ይህ ሁሉ ውሃ ይሔዳል ማለት ነው” ሲሉ ሲደነቁም ነበር፡፡ ለእኛ የግብጾች መሸነፍ ማለት ይህ ነው፡፡ ግብጾች፣ ኢትዮጵያ ስትገድብ የነበረው ግድብ ሙሉ በሙሉ እነርሱን የሚጎዳ አድርገው ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ሲናገሩ የነበረ ቢሆንም እነርሱ ሲያስቀምጡት የነበረው ትርክት   መሬት ላይ ያለ እውነታ አለመሆኑ በግልጽ ሊታወቅ ችሏል፡፡

ግብጾች፣ በዚህ ብቻ ተረትተው የሚያቆሙ እንዳልሆነ ከድርጊታቸው መረዳት ይቻላል፡፡ አይሳካላቸውም እንጂ በቀጣይም ሌላ ከመሞከር አይቦዝኑም፡፡ እኛ ማድረግ ያለብን ስራችንን በአግባቡ መስራት ነው፡፡ ዓባይ ግድብ ላይ በጣም ብዙ ነገር ሞክረዋል፡፡ በእርግጥ  ሴራቸው እኛን  ብዙ ዋጋ አስከፍሎናል፡፡ የዓባይ ግድብ የሕይወት መስዋዕትነት ጭምር የተከፈለበት   ነው፡፡ በዚህ ሁሉ ውስጥ ሆነን ግንባታውን  ማሳካት ችለናል፡፡  እውነትን ይዘን አሸናፊ መሆን ችለናል፡፡

በአሁኑ ሰዓት በዓለም መድረክ ላይ ስለ ዓባይ ግድብ እምብዛም እያወሩ አይደለም፡፡ ያንን ትተው አሁን እያደረጉ ያለው ጎረቤት አገሮችን ኬንያን፣ ሶማሊያን፣ ሱዳንን ..ወዘተ በኢትዮጵያ ላይ ለማነሳሳት መጣር ነው፡፡ እኛ ይህን ጉዳይ መንገር፤ ማስረዳት አለብን፡፡

ከኬንያውያን ጋር የምንሰራው የጋራ ልማት ነው፡፡ እኛ ዓባይ ላይ ባለማነው ኢነርጂ፣ በቀጣይም በምናለማው ኢነርጂ ኬንያ ተጠቃሚ ናት፡፡ ዛሬ ኢትዮጵያ ለኬኒያ ኢነርጂ ትልክላታለች፡፡ በተመሳሳይ ጅቡቲም ተጠቃሚ ናት፡፡ እንዲሁ ሱዳንም ከኢትዮጵያ ተጠቃሚ ናት፡፡ ለየአገራቱ ኢነርጂ እየሸጥንላቸው ነው፡፡

እነሱ ጩኸታቸውን ይጩሁ  ከእኛ የሚጠበቀው ትልቁ ነገር ስራችንን ከወትሮው በተለየ ሁኔታ አጠናክረን መቀጠል ነው፡፡ እንደሚታወቀው ሕዳሴ ግድብን ስንጠቀምበት የነበረው ለኢነርጂ ብቻ ነበር፡፡ እውነቱን ለመናገር በአካባቢው  በመስኖ ሊለማ የሚችል አቅም አለን፡፡ ስለሆነም በጣም ገፍተው ከመጡ መሬቱም ውሃው የእኛ ነው፤ ሉዓላዊ አገር ነን፡፡ በአካባቢው ያለው ሰፊ መሬት ነው፡፡ ስለዚህ መጠቀም እንችላለን፡፡  እነሱ ያላሰብነውን ጭምር እንድናስብ እያደረጉን ነው፡፡

ለግብጻውያን የሚሻለው ነገር ባልተገባ መንገድ ወዲህና ወዲያ ማለት ሳይሆን  በጠረጴዛ ዙሪያ መነጋገር ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ጥሩው እና አዋጩ መንገድ የትብብር ማሕቀፉ ነው፡፡ ሕግ ሆኖ የጸደቀው ማሕቀፍ ሁሉንም የተፋሰሱ አገሮች ማስጠለል የሚችል ትልቅ ጥላ ነው፡፡ እኛ ለዜጎቻችን የምናስበውን ያህል ለግብጾችም ለሱዳኖችም እናስባለን፡፡

ኢትዮጵያን በመረበሽ የሚያገኙት ትርፍ የላቸውም፡፡ ምናልባት ሕዝባቸውን “ኢትዮጵያን እንዲህና እንዲያ አድርገናታል” በሚል ለወሬ ፍጆታ ካልሆነ በስተቀር የሚገኝ ፋይዳ አይኖርም፡፡ ዓባይ ግድብ ላይ ሕዝባቸውን ሲዋሹ ነበር፤ ነገር ግን በመጨረሻም እውነታው ሌላ ሆኖ በመገኘቱ ሕዝቡ ራሱ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ጥያቄ የሚያነሳባቸው ይሆናል፡፡

እንደማይሳካለቸው የሚታወቀው ደግሞ የሄዱት ጎረቤቶቻችን ዘንድ ነው፤ እኛ ደግሞ ብዙ ጊዜ የጎረቤቶቻችንን እንቅስቃሴ እናውቃለን፡፡ ለምሳሌ ሶማሊያን ብንወስድ ለራሷ ችግር ውስጥ ያለች አገር ናት፡፡ እዛ ሔደው ኢትዮጵያ ላይ ማበር የማይቻል ነገር ነው፡፡ ሌላው ኤርትራ ጋር መሄድ ተመሳሳይ ነገር ነው፡፡ ምክንያቱም ኤርትራውያንም የራሳቸው ችግር ያለባቸው ናቸው፡፡ ስለዚህ አካሄዳቸው እንዲሁ ኢትዮጵያን የመጉዳት ሀሳብ እንጂ መሰረት የሌለው ነው፡፡ ምክንያቱም ኢትዮጵያን ሊጎዱም፤ ሊሳካላቸውም አይችሉም፡፡

ለኢትዮጵያውያን ትልቁ አዋጭ ጉዳይ በአንድነት መቆም ነው፡፡ የሚያወዋጣን የተጀመረውን ስራ መቀጠል ነው፡፡  ሕዳሴን ገንብተን አጠናቅቀናል፡፡ ይህም በጣም የተሳካ ሥራ ነው፡፡ ከዓባይ በኋላ በጣም ብዙ ሕዳሴዎች መገንባት አለባቸው፡፡ ዳቡስ፣ ዴዴሳ፣ በሽሎ፣ አንገር እነዚህ ትልልቅ የዓባይ ወንዝ ገባር ወንዞች ናቸው፡፡ በሌላኛው በኩል ደግሞ በለስ ወንዝ አለ፡፡ እነዚህን ሀብቶቻችን አስበንበት ለኢነርጂ፣ ለመስኖና ለሁሉም የልማት ስራዎች ለማከናወን ቆርጠን መነሳት ያስፈልገናል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የዓባይ ግድብ መጠናቀቁ እየተነገረ ይገኛል፤ አሁን ላይ ያለበት ሁኔታ ምን ይመስላል? በቀጣይስ ከሕዝቡ ምን ይጠበቃል?**

**ኢንጂነር ሀብታሙ (ዶ/ር)፡-** ዓባይ ግድብን ስናነሳ ኢትዮጵያውያን መያዝ ያለባቸው ሁለት ነገሮችን ነው፡፡ ግድቡን ጨርሰናል ስንል ግንባታው አበቃ ማለት አይደለም፡፡ ምክንያቱም አሁንም ድረስ የሕዝብን ድጋፍ የሚሻ ስራ ነው፡፡  ኢትዮጵያውያን ማወቅ የሚገባቸው ዓባይን ጨረስን ስንል ውሃውን መያዝ የሚያስችል የውሃ መጠን ላይ መኖራችን ነው፡፡ ሲቪል ዎርኩ የግድቡ አካል ነው፡፡ ይህ አልቋል ማለት ሌሎች የሚሰሩ ሥራዎች የሉም ማለት አይደለም፡፡ የሚጠናቀቁ ሥራዎች አሉ፡፡ ሁሉም የሕዝቡን ድጋፍ የሚፈልጉ ናቸው፡፡

ሌላው በዓባይ ግድቡ አካባቢ የሚሰሩ ተጨማሪ ሥራዎች አሉ፡፡ ዓባይን ለኢነርጂ መጠቀማችን እውነት ነው፤ ትልቁም ሥራ እሱ ነው፡፡ ይሁንና ብዙ ጥቅም የምናገኝባቸው ሌሎች ሥራዎችም አሉ፡፡ እነሱ ቀጣይነት ይኖራቸዋል፡፡ ይህ የሕዝብ ድጋፍ የሚፈልግ ነው፡፡ ስለሆነም ኢትዮጵያውያን በሚችሉት ሁሉ ድጋፍ ማድረጋቸውን ማቋረጥ የለባቸውም እላለሁ፡፡ ከሕዳሴ ጋር ተያይዞ በቀጣይ የሚሰሩ ሥራዎችን ማገዝ ያስፈልጋል፡፡በዚህ አጋጣሚ ለዜጎቻችን ጥሪ ማስተላለፍ እወዳለሁ ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ንጹህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ምን ደረጃ ላይ ይገኛል? ያልተዳረ ሰባቸው አካባቢዎች ለማድረስ እየተሰራ ያለው ምንድን ነው?**

**ኢንጂነር ሀብታሙ (ዶ/ር)፡-** የሚኒስቴር መ/ቤታችን ተቋማት የትኩረት አቅጣጫ ከሆነው አንዱ የመጠጥ ውሃ ነው፡፡ የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ዘርፍ ላይ ትኩረት እናደርጋለን፡፡ እንደ አገር ያለውን ስሌት ትተን በሰው ቁጥር ስናይ ወደ 71 ሚሊዮን አካባቢ የሚሆን ሰው የመጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ሆኗል፡፡ ይህ ቁጥር የከተማውንም የገጠሩንም የሚያጠቃልል ነው፡፡በቂ ነው ወይ ከተባለ የሕዝቡ ቁጥር ስለሚታወቅ በቂ አይደለም፡፡

ስለዚህ በኢትዮጵያ ውስጥ ካለው የሕዝብ ቁጥር ጋር ሲነጻጸር አሁን ያለው የውሃ መጠን ተመጣጣኝ አይደለም፡፡ በጣም ከፍተኛ የሆነ ስራ የሚፈልግ ነው፡፡ እንዴት ነው የሚሰራው ወደሚለው ሲመጣ አንዱ መንግስት በቻለው አቅም የሚሰራቸው ስራዎች አሉ፡፡

ሁለተኛው ደግሞ ከተለያየ ድጋፍ ሰጪ አካላት፣ ከዓለም ባንክ፣ ከዩኒሴፍና መሰል ከሆኑ ተቋማት ድጋፍ የሚሰሩ ናቸው፡፡  እዚህ ላይ ማንሳት የምፈልገው  ዜጎች በራሳቸው ተነሳሽነት / ኢኒሼቲቭ የራሴ የሆነ ውሃ ሊኖረኝ ይገባል ብለው  ማሰብ ይኖርባቸዋል ፡፡

እኛ እንደ ሚኒስቴሩ “ግድቤን በደጄ” የሚል አንድ ኢኒሼቲቭ ጀምረናል፡፡ “ግድቤን በደጄ” ማለት ዝናብ ሲዘንብ ሰው የሚወርደውን ዝናብ ይዞ አቆይቶ የተጣራ ውሃ በራሱ ማግኘት እንዲችል ማስቻል ነው፡፡ ይህን የጀመርነው በትምህርት ተቋማት ላይ ነው፡፡ እንደ ኢትዮጵያ ያለች ደሃ አገር ቀርቶ ሌላውም ይህን መጠቀም ግድ ይለዋል፡፡ ምክንያቱም ያደጉ አገሮችም ይህን ይጠቀሙበታል ፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የአመለካከት ችግር መንግስት ሁሉን እንዲያቀርብ መፈለጉ ላይ ነው፡፡ ይህ በጣም ከባድ ከመሆኑም በላይ ሊደረግ የማይችል ነው፡፡ በተፈጥሮ ፈጣሪ ዝናብ ሰጥቶናል፡፡ ዝናብ በየጊዜው እየዘነበ በደጃችን ሲያልፍ እያየን በነጋታው ግን ሰው ውሃ የለንም ብሎ ሲቸገር ይስተዋላል፡፡ ሩቅ ሰፈርም ውሃ ፍለጋ ይኳትናል፡፡

ነገር ግን በደጁ የሚያልፈውን ውሃ ይዞ ለነገ ለአትክልቱም፤ የዝናብ ውሃ ስለሆነ ንጹህ ነውና ለመጠጡም ማዋል ይቻላል፡፡ ከብትም የሚጠጣው ይሆናል፤፤ እንደዚህ አይነት ተነሳሽነቶች /ኢኒሼቲቮች ያስፈልጋሉ፤ እኛ ጀምረናቸዋል፡፡ የዝናብ ውሃን አሰባስቦ መጠቀምን እንደ ተጨማሪ አማራጭ ካደረግን አዋጭ ነው፡፡  ዋጋው ርካሽ ነው፡፡ ጊዜንም የሚወስድ አይደለም፡፡ ሰው ከቀዬው ውሃ ሳያጣ ለተለያየ ዓላማ መጠቀም ይችላል፡፡

ከዚህ ባሻገር በከተማ ውስጥ ያጋጠመን ትልቁ ችግር ከተሞች ለሌሎች የልማት ሥራዎቻቸውም ሆነ ለሚያስፈልጋቸው ጉዳይ በጀት እንደሚመድቡት ሁሉ ለመጠጥ ውሃም በጀት አለመመደባቸው ነው፡፡ ስለዚህ ለመጠጥ ውሃም እንደሌሎቹ ሁሉ በጀት ሊይዙለት ይገባል፡፡ ምክንያቱም ውሃ ሳይኖር መንገድም ሆነ ሌላ ነገር አይታሰብም፡፡ ስለዚህ በዚህ ላይ በአግባቡ መስራት ያስፈልጋል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ሰፋ ያለ ማብራሪያ ስለ ሰጡን ከልብ አመሰግናለሁ፡፡**


**ኢንጂነር ሀብታሙ (ዶ/ር)፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

ዜና

# ክህሎት መር ኢኮኖሚ እንዴት ይገነባል?

ዳግም ከበደ

**ዜና ትንታኔ**



መንግሥት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ክህሎት መር እንዲሆን እየሠራ ነው። ለውጤታማ ኢኮኖሚ ግንባታም ክህሎት ቁልፍ መሠረት መሆኑን ባለሙያዎች ይናገራሉ። ለመሆኑ «ክህሎት መር ኢኮኖሚ» ስንል ምን ማለታችን ነው? እንዴትስ ይገነባል?

አቶ ሙህዲን አባሞጋ በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የቴክኖሎጂና ሙያ ዘርፍ የሥልጠናና ተቋማት አቅም ግንባታ መሪ ሥራ አስፈፃሚ ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት፤ ዜጎች በኢኮኖሚ ውስጥ የሚኖራቸው ተሳትፎ ባላቸው ክህሎት መጠን ይወሰናል። ሁለም ዜጎች በተለያዩ ሙያዎች ላይ የሚኖራቸው ክህሎት ለጠቅላላው የኢኮኖሚ እድገት ጉልህ አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው። ክህሎት መር ኢኮኖሚ ግንባታ ፅንሰ ሃሳብም ይህንን ያቀናጀና የዜጎችን ክህሎት የማዳበር ግብ የያዘ ነው።

«አሁን የምንኖርበት ዓለም ውድድር የበዛበት፣ የሠለጠነ የሰው ሃይል የሚፈልግና ፈጣን የቴክኖሎጂ መለዋወጥ የሚታይበት ነው» የሚሉት አቶ ሙህዲን፤ ከጊዜው ተለዋዋጭነት ጋር እራስን ማብቃት፣ በክህሎት ብቁ ሆኖ መገኘት የሚጠይቅ ወቅት መሆኑን ያስረዳሉ።

ገበያው ላይ መቆየትና ተወዳዳሪ መሆን የሚቻለው ምርቶችን በብዛትና በጥራት የሚያመርት በተሠማራበት የሙያ መስክ የተካነ የሰው ኃይል ማፍራት ሲቻል እንደሆነ ያስረዳሉ።

ኢኮኖሚውን እየመሩ ያሉ ሀገራት የዜጎቻቸው ክህሎት ልማት ላይ በሠሩት መጠን ነው፤ የሚሉት አቶ ሙህዲን፤ ኢትዮጵያም ይህንን መንገድ መከተል እንደሚገባት ያስረዳሉ። ዜጎች በኢኮኖሚው ውስጥ በፍትሃዊነት ተጠቃሚ መሆን እንዲችሉ፣ ምርቶችን ወደ ውጭ በብዛት መላክ እና የገቢ ምርትን በሀገር ውስጥ ለመተካት የሚያስችል አቅም መፍጠር ያስፈልጋል ይላሉ። ይህንን ስኬታማ ለማድረግ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ በዜጎች ክህሎት ልማት ሊደገፍ ይገባል ነው ያሉት።

ዜጎች ሙያዊ ብቃታቸው ከፍ እንዲል በኢትዮጵያ መንግሥት ሰፊ ትኩረት መሰጠቱ ተገቢና ወቅቱን ያገናዘበ መሆኑን አቶ ሙህዲን ይናገራሉ። በክህሎትና ምርታማነታቸው ብቁ የሆኑ ዜጎች ለመፍጠር የሪፎርም ትግበራ መጀመሩንም ያስረዳሉ። ከኢኮኖሚ ጥገኝነት ለመውጣት የሚያስችል ሉዓላዊነት ለመፍጠር ትግበራዎች መከናወናቸውን ያስረዳሉ።

«ከዚህ ቀደም የነበረው የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ተግባር ተኮርነት የሚጎለው ነው» የሚሉት አቶ ሙህዲን፤ ይህም አንድ ዜጋ በሚሠራበት የሙያ መስክ ውጤታማ ለመሆን የሚያስችል (የተፍታታ እጅ) ክህሎት እንዳይኖረው እንቅፋት መሆኑን ይናገራሉ።

የኢትዮጵያ 70 በመቶ ሕዝብ ወጣት መሆኑን የሚያነሱት መሪ ሥራ አስፈፃሚው፤ አብዛኛው ወጣት በትምህርትና ሥልጠና ላይ የሚገኝ ቢሆንም በቁጥሩ ልክ ሀገሪቱ በኢኮኖሚ ተጠቃሚ አለመሆኗን ያስረዳሉ። ይህ የሆነው ክህሎትን ያማከለ የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ከዚህ ቀደም አለመዘርጋቱ እንደሆነ ያብራራሉ።

የሥልጠና ማእከላት መብዛትና በርካታ ባለሙያዎች መውጣታቸው እሙን ቢሆንም በኢኮኖሚው ውስጥ ግን የሚፈለገውን ተፅእኖ የፈጠሩ አለመሆኑ ይገልፃሉ።

የትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ ካርታው ይህንን ክፍተት በመለየት ክህሎት ላይ ትኩረት ማድረግ እንደሚያስፈልግ በመንግሥት መታመኑ ተገቢ ነው የሚሉት አቶ ሙህዲን፤ በተለይ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት ክህሎት የማልማት ተግባር ላይ ድርሻቸው ከፍተኛ እንደሆነ ያነሳሉ። ይህንን በሙሉ አቅም መተግበር ሲቻል የሀገር ገፅታ የሚቀይርና ዜጎች በኢኮኖሚ ውስጥ የሚኖራቸውን ተሳትፎ የሚያሳድግ መሆኑን ያነሳሉ።

የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ኢትዮጵያ የምትፈልገውን ያህል ክህሎትን ለማልማት ብዙ ይቀራቸዋል የሚሉት አቶ ሙህዲን፤ ወርክሾፖች በሚፈለገው ልክ ተግባር ተኮር ሥልጠና ለመስጠት የሚያስችል አቅም ሊፈጥሩና የዘመኑን ቴክኖሎጂ ሊታጠቁ እንደሚገባ ገልፀዋል።

ያነጋገራቸው ሌላኛው ባለሙያ በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ማስፋፊያ አቅም ግንባታ ዴስክ ኃላፊ አቶ አምላኩ አለባቸው እንደሚሉት «ክህሎት መር ኢኮኖሚ ተገንብቷል» ማለት የሚቻለው በተለይ በቴክኒክና ሙያ ማሠልጠኛ ተቋማት የሚሠጡ ሥልጠናዎች በትክክል በኢኮኖሚው ላይ ለውጥ ማምጣት የሚችል ተፅእኖ ማሳደር ሲጀምሩ እንደሆነ ይናገራሉ።

«በኢትዮጵያ የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ማሠልጠኛ ተቋማቶች የአካባቢያቸውን ኢኮኖሚ ፀጋ ያማከለ ሥልጠና መስጠት አለባቸው» የሚሉት አቶ አምላኩ፤ መንግሥት ያስቀመጠውን አቅጣጫ ተከትሎ በዚህ አግባብ በየአካባቢው ፀጋዎቹን የለየ ምደባዎች እየተከናወነ መሆኑን ያነሳሉ።

በምሳሌነት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የሚያነሱት አስተያየት ሰጪው አሶሳ ላይ የሚገኙ ማሠልጠኛ ተቋማት ከማእድን ልማት ጋር የተያያዘ የክህሎት ልማት ላይ እንዲያተኩሩ መደረጉን ይገልፃሉ። ይህን መሰል ትግበራ መኖሩ በኢኮኖሚው ላይ በቀጥታ በጎ ተፅእኖ መፍጠር የሚችል የሰው ሃይል ማፍራት እንደሚቻል ያስረዳሉ።

የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና በባህሪው ከፍተኛ የሆነ ሀብትን የሚጠይቅ መሆኑን የሚያነሱት አቶ አምላኩ፤ ሀብት ውስን በመሆኑ የሚፈለገውን በሙያውና በክህሎቱ ብቁ ሙያ የታጠቀ የሰው ሃይል ለመፍጠር እክል እንደሚፈጠር ይናገራሉ።

ይህንን ችግር ለመፍታት መንግሥት መፍትሄ ማስቀመጡን ተናግረው፤ እያንዳንዱ ቴክኒክና ሙያ ማሠልጠኛ ተቋማት ከዘልማዳዊ አሠራር እንዲወጡና በራሳቸው በሥራ ፈጠራ ተሠማርተው ከመንግሥት በጀት የሚላቀቁበት አማራጭ መዘርጋቱን እንደ መልካም አጋጣሚ ይጠቅሳሉ። ይህ መሆኑ ክህሎት መር ኢኮኖሚ ለመገንባትና ዜጎችም በተሠማሩበት ሙያ ላይ አምራችና ብቁ እንዲሆኑ መንገድ እንደሚያበጅ እምነታቸውን ገልፀዋል።

መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ሀገራዊ ሪፎርሙን ተከትሎ ክህሎት መር ኢኮኖሚ ለመገንባት ይረዳሉ ተብሎ ከታሰቡ መሥሪያ ቤቶች መካከል የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የፌዴራል መንግሥት አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 ተቋቁሟል፡፡

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ብቁ የሰው ሀብት፣ ምቹና አስተማማኝ የሥራ ዕድል የምትፈጥር ኢትዮጵያን ለመገንባት፣ በተለይ ደግሞ የክህሎት ልማት ላይ ለማተኮር እንደተቋቋመ ማወቅ ይቻላል። የዝግጅት ክፍላችን ያነጋገራቸው ሁለቱም የዘርፉ ምሁራን ይህንን መሰል ተቋማት መገንባት እቅዱን ወደ መሬት ለማውረድ እንደሚያግዝ ያምናሉ። ኢንዱስትሪዎች የሚያነሱትን የሠለጠነና ብቁ የሰው ኃይል ችግርን በዘላቂነት እንሚፈታ የሚጠበቅ ይሆናል፡፡

## የዓባይ ግድብ ለምስራቅ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በኢህአዴግ ዘመን ግድቡ ከተጀመረ በኋላ ችግር አጋጥሞት እንደነበረና በሥራው መጓተት ምክንያት 450 ሚሊዮን ዶላር ኪሳራ ማስከተሉን አስውስተዋል። ይሁንና የለውጡ መንግሥት ግድቡን በመታደግና ተደጋጋሚ ጫናዎችን በመቋቋም ለፍሬ አብቅቶታል ብለዋል።

መድረኩን በንግግር የከፈቱት አፈጉባኤ አቶ ታገሰ ጫፎ፤ ዜጎች በሀገራቸው ጉዳይ የሚወያዩበትና ሃሳባቸውን የሚያንጸባርቁበት መድረክ በተለይም በአሁኑ ጊዜ አስፈላጊ በመሆኑ ይህ መድረክ ተዘጋጅቷል ብለዋል።

የመጀመሪያው መድረክ ትኩረት የዓባይ ግድብ እንደሚሆን እና በቀጣይም በየወሩ በተለያዩ አንገብጋቢና አነጋጋሪ ጉዳዮች ዙሪያ መድረኩ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታውቀዋል።

በውይይት መድረኩ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት፣ የሚዲያ አመራሮች፣ ምሁራን በመገኘት ገንቢ ሃሳቦች ሰንዝረዋል።

## “እኛ ለዜጎቻችን የምናስበውን...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ጉዳይ ሕዝባቸውን ሲዋሹ ነበር፤ በመጨረሻም እውነታው ሌላ ሆኖ በመገኘቱ ሕዝቡ ራሱ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ጥያቄ የሚያነሳባቸው ይሆናል፡፡” ብለዋል፡፡

ለኢትዮጵያውያን ትልቁ አዋጭ ጉዳይ በአንድነት ቆሞ የተጀመረውን ሥራ አጠናክሮ መቀጠል ነው፡፡ የዓባይ ግድብን ገንብተን አጠናቅቀናል፤ ይህም በጣም የተሳካ ሥራ ነው፡፡ ከሕዳሴ በኋላ በጣም ብዙ ሕዳሴዎች መገንባት አለባቸው ያሉት ሚኒስትሩ፤ ዳቡስ፣ ዴደሳ፣ በሽሎ፣ አንገረብ፣ በለስ እነዚህ ትልልቅ የዓባይ ወንዝ ገባር ወንዞች ናቸው፡፡ እነዚህን ሀብቶቻችንን አስበንበት ለኢነርጂ፣ ለመስኖና ለሁሉም የልማት ሥራዎች ለማከናወን ቆርጠን መነሳት እንደሚያስፈልገን ኢንጂነር ሀብታሙ (ዶ/ር) ጠቁመዋል፡፡

አሁን ላይ ያላሰብነውን ጭምር እንድናስብ እያደረጉን ነው፡፡ እንደሚታወቀውም የዓባይ ግድብን ስንጠቀምበት የነበረው ለኢነርጂ ብቻ ነበር፡፡ በአካባቢው በመስኖ ሊለማ የሚችል መሬት አለን፡፡ በጣም ገፍተው ከመጡ መሬቱም ውሃው የእኛ ነው፤ ሉዓላዊ ሀገር ነን፤ በአካባቢው ያለው ያንን ሰፊ መሬት መጠቀም እንችላለን ብለዋል፡፡

የናይል ተፋሰስ ሀገራት ማእቀፍ ከተፋሰሱ ሀገራት ከግማሽ በላይ በሆኑት ሕግ ሆኖ መጽደቁ የምንኮራበት ነው፤ አሳክተነዋልም፡፡ ምክንያቱም ወደ ስድስት የሚሆኑ ሀገራት ይህንን ፈርመው በሀገር ደረጃ ሕጋቸው አድርገውታል፡፡ በቀጣይ ሕጉን ተግባራዊ የምናደርግበት የ”ናይል ሪቨር ኮሚሽንን” ማቋቋም ነው ሲሉ አስረድተዋል።

ኮሚሽን ለማቋቋም እንቅስቃሴ ጀምረናል ያሉት ሚኒስትሩ፣ ከዚህ ጋር ተያይዞም በቅርቡ ዑጋንዳ ኢንቴቤ ላይ አንድ ስብሰባ እንደነበራቸውና በስብሰባው ላይ የተገኘው ልዑክ የውሃ ሚኒስትሮች ካውንስል የሚባለው እንደሆነ አመልክተዋል፡፡ እርሳቸው እንደገለጹትም፤ በስብሰባቸው ወቅት ካቀረቡት ሃሳብ አንዱ የታችኞቹ ሀገሮች እና ሌሎቹ ያልፈረሙ ሀገሮች እንዲፈርሙ ማግባባት ላይ ነው፡፡ ለዚህ ሥራ ደግሞ ኮሚቴ ተዋቅሯል። በኢትዮጵያ እምነት የትኛውም የተፋሰሱ ሀገር ከዚህ ውጭ መሆን የለበትም፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ሀገራቱ ይጠቀሙበታል ተብሎ ስለሚታመን ነው።

ለእኛ ትልቁ ስኬት ከማዕቀፉ ሕጋዊ መሆን ጋር በተያያዘ ቀድሞ የነበሩ ሕጎች መሻራቸው ነው፡፡ ለምሳሌ የ1959ኙን ሕግ ሁለት ሀገሮች ብቻ ወስነው እንዳሻቸው የሚያደርጉትን አካሔድ ለውጦታል፤ ለእኛ ይህ ትልቅ ስኬት ነው፡፡ በቀጣይ ደግሞ ኮሚሽኑ ከመጣ እሰየው ነው፡፡ መምጣትም አለበት፤ እኛም እንደግፈዋለን፡፡ ይህ ሕግ ግን ለእኛ ሰላም የሚሰጥ ነው፤ ለሁሉም የሚጠቅም ነው ብለዋል፡፡

አሁን ከኢትዮጵያ ውጪ ብዙ ሀገሮች ስለማሕቀፉ ሆነ ስለኮሚሽኑ ስለገባቸው ተፈጻሚነቱ እንዲፋጠን እየተንቀሳቀሱ ነው፡፡ እኛም የምንፈልገው ይህንኑ ነው። በአሁኑ ወቅት ፍትሃዊነት የሚለውን ቃል ዑጋንዳ እና ደቡብ ሱዳን በማቀንቀን ላይ ናቸው፡፡ ቀደም ሲል ስለፍትሃዊነት ስንጮህ የነበረው ብቻችንን ነበር፤ በአሁኑ ወቅት አጋዥ አግኝተናል፡፡ ስድስት ሀገሮች ስምምነቱን ፈርመው የሀገራቸው ሕግ አካል ስላደረጉት፤ ስለዓባይ በአግባቡ በዓለም መድረክ ላይ ማውራት ጀምረዋል፡፡ ይህ ለኢትዮጵያ ትልቅ ስኬት ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

የናይል ወንዝ የትብብር ማሕቀፍ ስምምነት ከጥቅምት 3 ቀን 2017 ዓ.ም. ጀምሮ ወደ ተፈጻሚነት መግባቱ የሚታወስ ነው፡፡

## የሰላም መንገድ አማራጭ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

አመራሮች የዓድዋ ድል መታሰቢያን እና ሌሎች የልማት ሥራዎችን ተዘዋውረው ከጎበኙ በኋላ ከንቲባ አዳነች አቤቤ እንኳን ወደ ሰላም መንገድ መጣችሁ ብለው ተቀብለዋቸዋል፡፡

ከንቲባ አዳነች አቤቤ በጃል ሰኚ ነጋሳ የተመሩ የኦሮሞ ነፃነት ሠራዊት አባላት ጋር በተወያዩበት ወቅት፤ የሰላም መንገድ አማራጭ የሌለው እና ሁሉንም ተጠቃሚ የሚያደርግ መንገድ መሆኑን በመረዳት መንግሥት ላደረገው ጥሪ የኦሮሞ ነፃነት ሠራዊት አባላት የሰጡት ምላሽ የሚያስመሰግን መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

ስምምነቱ የፖለቲካ እና የሃሳብ ልዩነቶችን ዘመናዊ በሆነ መንገድ በውይይትና በሰላም መፍታት ለሌሎችም አርአያ የሚሆን ተግባር መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የኦሮሞ ነፃነት ሠራዊት ከፍተኛ አመራር ጃል ሰኚ ነጋሳ በበኩላቸው፤ ለተደረገላቸው አቀባበል አመስግነው፤ የሰላም ጥሪውን የተቀበሉት የሕዝብን ጉዳት ለመቀነስ እና የሰላም አማራጭን መቀበል ብልህነትና አዋቂነት መሆኑን በመረዳታቸው እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

በኦሮሚያ ክልል መንግሥት እና የኦሮሞ ነፃነት ሠራዊት ከፍተኛ አመራሮች መካከል የሰላም ስምምነት መፈራረሙን ተከትሎ የኦሮሞ ነፃነት ሠራዊት አባላት የዓድዋ ድል መታሰቢያን፣ አንድነት ፓርክን እንዲሁም በአዲስ አበባ የተገነቡ ሌሎች ፕሮጀክቶችን ተዘዋውረው መጎብኘታቸውን የከንቲባ ፅህፈት ቤት መረጃ ያመለክታል።

በሌላ በኩልም የኦሮሚያ ክልል መንግሥት እና የኦሮሞ ነጻነት ሠራዊት አመራሮች የደረሱትን የሰላም ስምምነት ተከትሎ በተለያዩ አካባቢዎች የሚንቀሳቀሱ የኦሮሞ ነጻነት ሠራዊት አባላት ወደ ተዘጋጁላቸው ማዕከላት መግባታቸውን ቀጥለዋል ሲሉ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ለገሰ ቱሉ (ዶ/ር) ገለጹ።

ሚኒስትሩ በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ባሰፈሩት መልዕክት፤ የሠራዊቱ አባላት ወደ ማዕከላቱ በሚያደርጉት ጉዞም ሕዝቡ አቀባበል እያደረገላቸው መሆኑን አመልክተዋል።

ሰላም ለኢትዮጵያውያን በሙሉ ይሁን፣ ይህን የሰላም ጥሪ ተቀብለው እየገቡ ላሉት ሁሉ ምስጋና ይገባል ብለዋል።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## የትራንስፖርት ዘርፉን የታዳሽ ኃይል መጠቀም አስፈላጊነት ያመላከተው ኤግዚቢሽን

ፋንታነሽ ክንዴ




በዓለም የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት እየተባባሰ መምጣቱ ይገለጻል፡፡ ለእዚህ ምክንያት ከሆኑት መካከል ነዳጅ የሚጠቀሙ ተሽከርካሪዎች መሆናቸውም ይታወቃል፡፡ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ እ.ኤ.አ በ2029/30 የተሽከርካሪዎች የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት 40 ሚሊዮን ቶን እንደሚደርስ ይጠበቃል፡፡ ይህም በአየር ንብረት ለውጥ ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ተጽዕኖ ከፍተኛ ነው፡፡

ችግሩን ለመቅረፍ ሀገራት የተለያዩ ተግባሮችን እያከናወኑ ሲሆን፤ ከእነዚህ መካከል በታዳሽ ኃይል የሚሠሩ ተሽከርካሪዎችን መማተር አንዱ ነው፡፡ ይህን ተከትሎ በተከናወነው ተግባርም በኤሌክትሪክ የሚሰሩ ተሽከርካሪዎች በአውራ ጎዳናዎች በስፋት እንዲንቀሳቀሱ እየተደረገ ነው፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥትም የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች በነዳጅ ከሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች ጋር ሲነፃፀሩ ያላቸውን አንፃራዊ ጥቅም ከግምት ውስጥ በማስገባት እንዲሁም ታዳሽ ኃይልን መሠረት ያደረገውን የትራንስፖርት ዘርፍ መገንባት ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚን ግንባታ ያለውን ፋይዳ በመገንዘብ ለዘርፉ ልማት ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ይገኛል፡፡ የታዳሽ ኃይል በአግባቡ የሚጠቀም፣ በማኅበረሰቡ ጤናና በአካባቢ ብክለት ላይ ጉዳት የማያስከትል አረንጓዴ ትራንስፖርት እውን የማድረጉ ስራም በአሥር ዓመቱ ዕቅድ መሰረት ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡

መንግሥት በኤሌክትሪክ የሚሰሩ ተሽከርካሪዎች ኢንቨስትመንት ላይ የሚሰማሩ ኢንዱስትሪዎችንና አስመጪዎችን የሚያበረታታ፣ ህብረተሰቡንም የዚህ አገልግሎት ተጠቃሚ የሚያደርግ የታክስ ማሻሻያ ተግባራዊ ማድረጉ ይታወቃል፡፡ የታክስ ማሻሻያው ዓላማ በኢትዮጵያ በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ የመጣውን የተሽከርካሪዎች ቁጥር በፖሊሲ ማዕቀፍ ከአካባቢ ደህንነት ጋር የሚስማማ ለማድረግ፣ በህብረተሰቡ ጤና ላይ ጉዳት የማያስከትል፣ በአየር ንብረትና በብዝሃ ህይወት ላይ ተጽእኖ የማያሳርፍ እና ታዳሽ የኃይል ምንጮችን በአግባቡ የሚጠቀም የመጓጓዣ ሥርዓት ተግባራዊ ለማድረግ እንዲሁም የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች በተመጣጣኝ ዋጋ ለህብረተሰቡ እንዲቀርቡ ማስቻልን ያለመ ስለመሆኑ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

እነዚህ ተሽከርካሪዎች ቀደም ሲል ከውጭ በቀጥታ እንዲገቡ ይደረግ የነበረ ሲሆን፣ የተሽከርካሪዎቹን ፋይዳ የተረዳው መንግሥት ከውጭ በስፋት ሊገቡ የሚችሉበትን ምቹ ሁኔታ ከመፍጠር ባሻገር በሀገር ውስጥ ሊገጣጠሙ የሚችሉበትን ምቹ ሁኔታም ፈጥሯል፡፡ ይህን ተከትሎም ባለሀብቶች በኤሌክትሪክ የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎችን የመገጣጠም ኢንቨስትመንት ላይ የተሰማሩበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ጎዳናዎች ላይ በኤሌክትሪክ የሚሰሩ የቤት አውቶሞቢሎች፣ ሚኒባሶችና አውቶቡሶች እየተንቀሳቀሱ ያሉበት ሁኔታም ይህንኑ ያመለክታል፡፡ የእነዚህን ተሽከርካሪዎች አገልግሎት ለማስፋትም ሰፊ እቅድ ተይዞ እየተሰራ ነው፡፡

መንግሥት የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን ለማበረታታት የወሰዳቸውን እርምጃዎች ተከትሎ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ቁጥር እንደጨመረ ይገኛል፡፡ የባለፈው ወር መረጃ እንዳመለከተው፤ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን በሀገር ውስጥ የሚገጣጠሙ ድርጅቶች 15 የደረሱ ሲሆን፣ ተሽከርካሪዎቹን የሚያስመጡት ደግሞ ከ200 በላይ ሆነዋል፡፡

በቅርቡ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ባዘጋጀው በአረንጓዴ ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ላይ ያተኮረ ኢትዮ- ግሪን ሞቢሊቲ 2024 ዓለም አቀፍ አውደ ርዕይ እና ሲምፖዚየም ላይ እንደተጠቆመው ፤ ሀገሪቱ በዚህ ለአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ እና ከነዳጅ ጥገኝነት ለመላቀቅ ትልቅ ፋይዳ ባለው ኢንቨስትመንት ላይ በቀጣይም በስፋት መስራት ያስፈልጋል፡፡

በመድረኩ መክፈቻ ላይ የተገኙት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈጉባኤ ታገሰ ጫፎ እንደገለጹት፤ የአየር ንብረት ለውጥ እየፈጠረ ያለውን ዓለም አቀፍ ተፅዕኖ መቋቋም የሚችል ዘላቂና አስተማማኝ አረንጓዴ ልማት ማካሄድ ይገባል፡፡ ኢትዮጵያ አረንጓዴ ትራንስፖርትን ሊደግፍ የሚችል እምቅ ታዳሽ ኃይል ባለቤት ናት፡፡ ይህን አቅም በመጠቀም የአረንጓዴ ትራንስፖርት ፈር ቀዳጅ ለመሆን እየሠራች ነው።

ሀገሪቱ ያላትን አረንጓዴ እምቅ ኃይልን በመጠቀም በአካባቢ ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለማስቀረትና ለረጅም ጊዜ ሀገራዊ ብልጽግናን የሚደግፉ ጠንካራ የታዳሽ ኃይል ማመንጫዎችን እውን በማድረግ ላይ እንደምትገኝ አመልክተዋል፡፡ ኢትዮ- ግሪን ሞቢሊቲ 2024 ኤግዚቢሽን እና ሲምፖዚየምም ሀገሪቱ ያላትን እምቅ የአረንጓዴ ኃይል እንዴት መጠቀም እንደምትችል ማሳያ መሆኑን ጠቅሰው፤ ዓለም በዘርፉ የደረሰበትን ደረጃና ከፊታችን የሚጠብቀንን ትልቅ ሥራ እንደሚያመላክት አስታውቀዋል፡፡

አፈ ጉባኤው እንዳሉት፤ በሀገሪቱ የተሟላ ለውጥ ለማምጣት፣ እድገትና ብልጽግናን ለማረጋገጥ እና የሕዝብን ኑሮ ደረጃ በደረጃ ለማሻሻል በሚደረገው ርብርብ ተስፋ ሰጪ ውጤቶች እየተመዘገቡ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ገጽታ ያላቸው ተጨማሪ ትግል የሚፈልጉ የአየር ንብረት ለውጥ ያስከተላቸው ችግሮችና የከተሞች መጨናነቅን የመሳሰሉ ተግዳሮቶችም አሉ፡፡ እነዚህን ችግሮች ለማሸነፍ በሚደረጉ ጥረቶችም አዳዲስ ፈጠራዎችና መልካም እድሎች እየተስተዋሉ ነው፡፡ ይህም ኢኮኖሚን ለማሳደግና እምቅ ሀብትን ለመጠቀም እድል ይፈጥራል፡፡

ሀገራት በካርቦን ምንጭ ላይ ከተመሠረተው የትራንስፖርት አገልግሎት በመውጣት በኤሌክትሪክና በሌሎችም ታዳሽ ኃይል የሚሠሩ ተሽከርካሪዎችን ወደ አገልግሎት በማስገባት ላይ መሆናቸውን አፈጉባኤ ታገሰ ጠቅሰው፣ በኢትዮጵያም በትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ዘርፍ የግሪን ሀውስ ጋዝ ልቀትንና በነዳጅ ጋዝ ላይ ያለውን ጥገኝነት ለመቀነስ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

እሳቸው እንዳብራሩት፤ በሀገሪቱ በኤሌክትሪክ የሚሰሩ ተሽከርካሪዎችን የማምረትና የመገጣጠም ሥራን በማበረታታት እንዲሁም ለዚህ አገልግሎት የሚውሉ መሠረተ ልማቶች ላይ የሚደረጉ ኢንቨስትመንቶችን ለማበረታታት የሚያስችል ፖሊሲ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ እየተደረገ ነው፡፡ ታዳሽ ኃይል ዘላቂነት ያለውና የዜጎችን ሕይወት ለማሻሻል የማዕዘን ድንጋይ በመሆኑ በዚህ በኩል ለሚደረግ ኢንቨስትመንት ስኬት ሁሉም ባለድርሻ አካላት ርብርብ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ የበካይ ጋዝ ልቀትን በመቀነስ የበለፀገ ማህበረሰብ ለመፍጠር ፖሊሲ አውጪዎችና የዘርፉ ባለድርሻ አካላት በቅንጅት መሥራት ይገባቸዋል።

የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስትር አለሙ ስሜ(ዶ/ር) በበኩላቸው፤ መርሃ ግብሩ ኢትዮጵያ ለአረንጓዴ ልማት ያላትን ቁርጠኝነት ጠቅሰው፣ የዜጎችን እኩል ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ አረንጓዴ ኢኮኖሚን እውን ለማድረግ ከታለሙ እንቅስቃሴዎች አንዱም ይሄው መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ኢትዮጵያ ያላትን እምቅ የታዳሽ ኃይል ሀብት በመጠቀም በአረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት ፈርቀዳጅ ለመሆን የትራንስፖርት መልክዓ-ምድሯን እያሻሻለች እንደምትገኝ አመልክተዋል፡፡

የአሥር ዓመቱ የትራንስፖርት እቅድም ለሞተር አልባ የትራንስፖርት ስትራቴጂዎች፣ ለሕዝብ ትራንስፖርት ፖሊሲዎችና ለኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ቅድሚያ እንደሚሰጥ ገልጸው፣ ለዚህም አስፈላጊውን መሠረተ ልማት ማሟላትና ጤናማ የአኗኗር ዘይቤን ለመፍጠር እየተሠራ መሆኑን አመላክተዋል፡፡ የትራንስፖርት ሚኒስቴርም ታዳሽ ኃይል ለሚጠቀሙ ተሽከርካሪዎች ወይም ለኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ልዩ ልዩ ማበረታቻዎች የማድረግና ምቹ መሰረተ ልማት ለመዘርጋት በትኩረት እየሠራ መሆኑንም አስታውቀዋል፡፡

ሚኒስትሩ እንዳብራሩት፤ የአዲስ አበባ ከተማን የዲፕሎማሲና የኢኮኖሚ ማዕከልነት ለማስጠበቅ የተጀመሩ የአረንጓዴ ልማት ሥራዎችን በአረንጓዴ ትራንስፖርት ለመደገፍ በትኩረት እየተሰራ ነው፡፡ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች የትራንስፖርት ዘርፉን ከነዳጅ ጥገኝነት በማላቀቅ ለነዳጅ ግዢ የሚወጣውን የውጭ ምንዛሪ ለመቀነስ ይጠቅማሉ፤ ዘርፉ ለኢኮኖሚያዊ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያለው ሲሆን፣ ሚኒስቴሩም በዘርፉ ለተሰማራውና ለሚሰማራው የግል ዘርፍ አስፈላጊውን ድጋፍ እያደረገ ይገኛል።

በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሠሩ ተሽከርካሪዎች ከኢኮኖሚ ጠቀሜታና የአየር ብክለትን ከመከላከል ባለፈ የድምፅ ብክለትን ለማስቀረትና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ለማፋጠን እንደሚረዱ ሚኒስትሩ አስገንዝበዋል፡፡ ከተሽከርካሪ መሰረተ ልማት ባለፈ የሳይክልና የእግረኛ መንገዶችን በማስፋት ከነዳጅ ጥገኝነት ለመላቀቅ፣ የበካይ ጋዝን ለመቀነስና ጤናማ ማህበረሰብ ለመፍጠር የሚደረገው ጥረት ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም አረጋግጠዋል፡፡

በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የኤሌክትሪፊኬሽንና የኢነርጂ መረጃ መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ መስፍን ዳቢ ኢትዮ- ግሪን ሞቢሊቲ 2024 አውደ ርዕይና ኤግዚቢሽን ከነዳጅ ውጪ የታዳሽ ኃይል ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም የሚያስችል ሰፊ እድል መኖሩን የሚያመላክት መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ በሂደትም ነዳጅ ላይ መሠረት ያደረገውን የትራንስፖርት ዘርፍ ሙሉ በሙሉ ታዳሽ በሆነ የኃይል አቅርቦት ልንተካው እንደምንችል ትልቅ ልምድ የሰጠ ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

እሳቸው እንዳብራሩትም፤ ታዳሽ ኃይልን መሠረት ያደረገ የትራንስፖርት አገልግሎት ወደ ሥራ መግባት ከነዳጅ የሚወጣውን የካርቦን ልቀት በማስቀረት የአየርን ንብረት ለውጥን በመከላከል በኩል ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረክታል። በተጨማሪም ሀገሪቱ ለነዳጅ ግዢ በየዓመቱ የምታወጣውን ከፍተኛ የውጪ ምንዛሪ በማስቀረት በኩል የሚኖረው ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ከፍተኛ ነው፡፡

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር በሁሉም ዘርፍ ላይ የታዳሽ ኃይል አጠቃቀም እንዲያድግ እንደሚሠራ ጠቁመው፤ በአምራች ኢንዱስትሪው፣ በትራንስፖርት ዘርፉ ብሎም በቤተሰብ ደረጃ ያለው የኃይል ፍጆታ ሙሉ በሙሉ በታዳሽ ኃይል ቴክኖሎጂዎች ላይ የተመሠረተ እንዲሆን እየተሠራ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡ ለዚህም የኢነርጂ ልማቱ ታዳሽ ኃይልን መሠረት ያደረገና አካታች እንዲሆን የሚያስችል ፖሊሲ ተቀርጾ እየተተገበረ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

የታዳሽ ኃይል ቴክኖሎጂዎች ከታክስ ነጻ ሆነው ወደሀገሪቱ እንዲገቡ ማድረግን ጨምሮ ዘርፉ ላይ የተለያዩ ማበረታቻዎች እየተደረጉ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ ይህም የትራንስፖርት ዘርፉን ጨምሮ በሁሉም መስክ የተፋጠነ የታዳሽ ኃይል ልማት እንዲኖር እገዛ ያደርጋል ብለዋል፡፡

በአውደ ርዕዩ ከተሳተፉ ተቋማት አንዱ የሆነው የበላይነህ ክንዴ ግሩፕ የኮሙኒኬሽን ኃላፊ አቶ ሰጠኝ እንግዳው፤ የበላይነህ ክንዴ ግሩፕ ላለፉት ስምንት ዓመታት የደረቅና ፈሳሽ ጭነት መኪኖችን በሀገር ውስጥ ሲያመርት መቆየቱን ጠቅሰው፣ ከ2015 ዓ.ም መጨረሻ ጀምሮ ደግሞ የኤሌክትሪክ መኪኖችን ወደመገጣጠም ተሸጋግሯል ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

በዚህም በመጀመሪያው ዙር 216 የሚደርሱ ከ15 ሰው በላይ የሚጭኑ የኤሌክትሪክ ሚኒባሶችን ገጣጥሞ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና በሌሎች ተቋማት ወደ ስራ ማስገባቱን አመልክተው፣ ቬሎሲቲ የተባለ እህት ኩባንያ አቋቁሞ በ20 ሚኒባሶች እና ሁለት አውቶቡሶች አማካኝነት በአዲስ አበባ ከተማ የትራንስፖርት አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል ሲሉ ያብራራሉ፡፡

ኩባንያው ሚኒባሶች ላይ ትኩረት አድርጎ ሲሠራ መቆየቱን አስታውሰው፤ ደብረብርሃን ከተማ ላይ በገነባው ፋብሪካ አማካኝነት ደግሞ አብዛኛውን ማህበረሰብ ተደራሽ ማድረግ የሚያስችሉ የኤሌክትሪክ አውቶቡሶችን እየገጣጠመ ለገበያ እያቀረበ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ እስካሁንም አሥር ያህል አውቶቡሶችን ገጣጥሞ ለተጠቃሚዎች ማቅረቡን አስታውቀዋል፡፡

እንደ ሀገር የሚስተዋለውን የኤሌክትሪክ መኪና ቻርጀር ችግር ለመቅረፍም ከ60 እስከ 160 ኪሎ ዋት አቅም ያላቸው ፈጣን የኤሌክትሪክ ቻርጀሮችን አስመጥቶ ለገበያ ማቅረቡን ገልጸዋል፡፡

በሀገሪቱ የአረንጓዴ ልማት ጥረት ውስጥ ተሳታፊ ሆነን ትልቅ ሀገራዊ አስተዋጽኦ ማድረግ በመቻላችን ደስተኞች ነን ያሉት ኃላፊው፤ ኩባንያው አብዛኛውን ማህበረሰብ ተጠቃሚ በሚያደርግ መልኩ ሥራውን አጠናክሮ እንደሚቀጥል ይገልጻሉ፡፡ የኢትዮ ሞቢሊቲ መድረክ የገበያ ትስስር ለመፍጠር፣ የዘርፉን መልካም አጋጣሚዎች ለመመልከትና ተግዳሮቶችን ለመፍታት ፋይዳው ከፍተኛ መሆኑን አቶ ሰጠኝ አስታውቀዋል።

በአውደ ርእዩ የተሳተፈው የካኪ ሞተርስ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ እንግዳሰው ደምሴ እንደሚሉት፤ ካኪ ሞተርስ በሀገሪቱ የተለያዩ የጭነት መኪኖችን በስፋት ሲያቀርብ ከሃያ ዓመት በላይ ሆኖታል፤ በሀገር ውስጥ ግዙፍ የአይሱዙ መገጣጠሚያ ከፍቶ አገልግሎት እየሰጠም ይገኛል፡፡

በሀገሪቱ ለታዳሽ ኃይል የተሰጠውን ትኩረት ለማሳካት እንዲቻል በኤሌክትሪክ የሚሠሩ ተሽከርካሪዎችን ወደሀገር እያስመጣ ለተጠቃሚዎች እያቀረበ መሆኑን ጠቅሰው፣ በቀጣይነትም ከውጪ የሚገቡ የኤሌክትሪክ መኪኖችን በሀገር ውስጥ ለመገጣጠም የሚያስችል ሥራ እየሠራ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ ኢግዚቢሽኑ በዘርፉ ምን ያህል አቅም እንዳለ ማመልከታቸውን ገልጸው፣ ለገበያ ትስስር ያለው ፋይዳ ከፍተኛ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

በሀገሪቱ ለመጀመሪያ ጊዜ በተካሄደው ኢትዮ ግሪን ሞቢሊቲ 2024 አውደ ርዕይና ሲምፖዚየም ላይ ከ700 በላይ ባለድርሻዎች መሳተፋቸውን መረጃዎች ያመላክታሉ። ዝግጅቱም የአረንጓዴ ትራንስፖርትና መሰረተ ልማት አምራቾችን፣ ገጣጣሚዎችን፣ አስመጪዎችን፣ የኢንዱስትሪ መሪዎችን፣ ፖሊሲ አውጪዎችን እና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን አገናኝቷል፡፡ይህም የትብብር እድሎችን ለመፍጠር፣ ምርጥ ተሞክሮዎችን ለመለዋወጥ እንዲሁም ለአረንጓዴ እና ደህንነቱ ለተጠበቀ ቀልጣፋ የትራንስፖርት ዘርፍ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ቴክኖሎጂዎችን ማሳደግ ዓላማ አድርጎ የተካሄደ መሆኑ ተጠቁሟል፡፡

# ከሰላም እንጂ ከጦርነት ማትረፍ አይቻልም

እስማኤል አረቦ

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላም ወዳድ ሕዝብ ነው።ለዘመናት አብሮ ተከባብሮ በመኖርና የሰላም ተምሳሌት በመሆን በአርአያነት ሲጠቀስ የኖረ ነው፡፡ ከኢትዮጵያውያን ዘመን ተሻጋሪ አኩሪ መገለጫዎች መካከል የብሔር፣ የእምነት፣ የቋንቋ፣ የባህልና ሌሎች ልዩነቶችን ዕውቅና በመስጠት ተሳስቦና ተከባብሮ መኖር ትልቁ እሴት ነው፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሀገሩ ዳር ድንበር የሚዋደቅ፤ከራሱ በፊት ሀገሩን የሚያስቀድም፤ቅኝ ገዢዎችንና ሌሎች ወራሪ ኃይላትን አሳፍሮ የሚመልስ ጀግና ሕዝብ ነው ፡፡ ኢትዮጵያውያን ከራሳቸው አልፈው ለሌሎች ሀገራት ነጻነትና እኩልነት የሚታገሉ፤በአፍሪካ የነጻነት ተምሳሌት የሆኑ ኩሩ ሕዝቦች ናቸው፡፡ ይህም ጀግንነትና አይበገሬነት በተባበሩት መንግሥታት ጭምር እውቅና አግኝቶ ጀግናው የመከላከያ ሠራዊታችን በሩዋንዳ፣ በቡሩንዲ፣በላይቤሪያና በሶማሊያ ተሰማርቶ ጀግንነቱን አስመስክሯል፡፡

ሆኖም በተሳሳተ የፖለቲካ እሳቤ እና አንዳንድ ጊዜም በውጭ ኃይላት ግፊት ኢትዮጵያ በርካታ ጦርነቶችን እና የእርስ በእርስ ግጭቶችን አካሂዳለች፡፡ እነዚህ እርስ በእርስ ግጭቶች የሕዝቦችን አብሮ የመኖር ተስፋ ያቀጨጩ እና እንደ ሀገርም የሚያስማማ ሀገረ መንግሥት ለመገንባት እንቅፋት ሆነው ቆይተዋል፡፡

በተለይም ባለፉት 50 ዓመታት በነበረው የተዛባ የፖለቲካ አመለካከት እና ከውይይት ምክክርን ከማስቀደም ይልቅ ችግሮችን በኃይል አማራጭ ለመፍታት ሲደረጉ በነበሩ እኩይ ሥራዎች ኢትዮጵያ ሰላሟን አጥታ ቆይታለች፡፡ በደርግ እና ነጻ አውጪ ነን በሚሉ አካላት መካከል፣በደርግ እና በኢህአፓ፣መኢሶንና ሌሎች የፖለቲካ ቡድኖች መካከል በኢትዮጵያ እና በኤርትራ መካከል በርካታ ጦርነቶች እና ግጭቶች ተካሂደዋል፡፡

በአጠቃላይ ባለፉት 50 ዓመታት የተዘራው ዘር በኢትዮጵያውያን መካከል ለዘመናት ጸንቶ የቆየውን አንድነት የሚያላላ እና በሂደትም ኢትዮጵያ እንድትዳከም ለማድረግ የታለመ ነው፡፡ ይህንኑ እኩይ ተግባር የያዙ አካላትም ለኢትዮጵያ ተቆርቋሪ በመምሰል ሕዝቡን ለስቃይ እና ለመከራ ሲዳርጉት ኖረዋል፡፡

እነዚህ ቡድኖች በወረሱት መጥፎ እሳቤ የተነሳ የጦርነት እና የግጭት አባዜ የተጸናወታቸው ናቸው። ከውይይት ይልቅ ነፍጥ ማንሳት የሚቀናቸውና ሰላም ወዳዱን ሕዝብ የሚረብሹ፣አብሮነቱን የሚያውኩ፣ የኢትዮጵያን መረጋጋትና ሉአላዊነት የሚገዳደሩ ቡድኖች እዚህም እዚያም አቆጥቁጠዋል፡፡

እነዚህ ወገኖች በሚፈጥሩት ሁከትና ብጥብጥም ልማት ተደናቅፏል፤የሰዎች ወጥቶ መግባት ተስተጓጉሏል፤አለፍ ሲልም የሀገር ህልውናንም አደጋ ላይ ወድቋል፡፡

ሕዝብ ሳይሾማቸው ለሕዝብ ቆመናል የሚሉ ቡድኖችና ፖለቲከኞች ችግርን በሰላማዊ መንገድ ከመፍታት ይልቅ ነውጠኛ ደጋፊዎችን የማሰባሰብ ሴራ ውስጥ ስለሚገቡ፣ በኢትዮጵያ እዚህም እዚያም ግጭቶች በርክተው ይታያሉ። እነዚሁ ኃይላት ኃላፊነት የጎደላቸው ስለሆኑም ግጭትና መገዳደልን ጨምሮ የሀገርን ተስፋ የሚያጨልሙ ድርጊቶች እንዲበራከቱ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ ለሀገርና ለሕዝብ ከማሰብ ይልቅ ከመጠን ያለፈ ራስ ወዳድነት ስለተጠናወታቸውም ቆመንለታል ያሉትን ሕዝብ ሳይቀር በቁሙ ሲዘርፉ ተስተውለዋል፡፡

እነዚህ የግጭት ነጋዴዎች ከመተማመን ይልቅ ጥርጣሬ፣ ከትብብር ይልቅ መገፋፋት፣ በግልጽ ከመነጋገር ይልቅ መተማማት ስለሚቀናቸው የማህበራዊ ሚዲያዎች እና ሌሎች የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ሕዝቡን አላስፈላጊ ወደ ሆነ ጥርጣሬ ውስጥ በመክተት አንዴ በብሔር ሌላ

**የኦሮሞ ነጻነት ሠራዊት ከመንግሥት ጋር በነበረው ቅራኔ በኦሮሚያ አለፍ ሲልም እንደሀገር በርካታ ቀውሶች ደርሰዋል፡፡ በርካታ የሰው ህይወት ተቀጥፏል፤አካል ጎድሏል፤ንብረት ወድሟል፡፡ሆኖም በስተመጨረሻም በዚህ መልኩ ሰላም መውረዱ ለብዙዎቻችን እፎይታ የሰጠ ነው**

ጊዜ በሃይማኖት እየከፋፈሉ የዘመናት አብሮነቱን ሊነጥቁት ሲሯሯጡ ይታያሉ፡፡ በእነዚህ ስግብግቦች የተነሳ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከባድ ጊዜን ለማሳለፍ ተገዷል፡፡

በእነዚህ እኩይ ዕሳቤዎች የተነሳ ባለፉት አምስት ዓመታት በርካታ ግጭቶች እና መፈናቀሎች ተስተውለዋል፡፡ አለፍ ሲልም ጦርነቶች ተካሂደዋል። በመንግሥት እና በወያኔ መካከል ለሁለት ዓመታት ያህል የተካሄደውም ደም አፋሳሽ ጦርነት በዚህ ረገድ ተጠቃሽ ነው፡፡ በርካታ ህይወት ተቀጥፏል፤አካል ጎድሏል፤ሀብት እና ንብረት ወድምሟል፡፡ ሆኖም በስተመጨረሻ ሁለቱ አካላት በተስማሙት መሰረት በፕሪቶሪያ ስምምነት አድርገው ሰላም አውርደዋል፡፡

ለሁለት ዓመታት ያህል በመንግሥትና በሕወሓት መካከል ሲደረግ የነበረው ጦርነት ጥቅምት 23 ቀን 2015 በፕሪቶሪያ በተካሄደው የሰላም ስምምነት ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን መሠረት አድርጎ ሉአላዊነትንና የግዛት አንድነትን እና ብሄራዊ ጥቅምን ባከበረ መልኩ ዕልባት አግኝቷል፡፡ የተደረሰው ስምምነት ደም አፋሳሹን ጦርነት ለማስቆም፣ ዕርዳታ እና መሠረታዊ አገልግሎቶች ለማስጀመርና የሀገሪቱን የድንበርና የግዛት አንድነት እንዲሁም ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት እንዲከበር የማድረግ አላማ አለው።

የፕሪቶሪያው ስምምነት ከያዛቸው አንኳር ጉዳዮች አንዱ 'ኢትዮጵያ አንድ የሀገር መከላከያ ሠራዊት ብቻ ነው ያላት' የሚለው ጉዳይ ነው። በዚሁ መሠረትም የኢትዮጵያ ፌዴራል የፀጥታ ኃይሎች "በትግራይ ክልል ውስጥ የሚገኙትን ሁሉንም የፌዴራሉን ተቋማትና አየር ማረፊያዎችንና አውራ ጎዳናዎችን ጨምሮ ዋነኛ መሠረተ ልማቶችን" ሙሉ ለሙሉ የመቆጣጠር መብትን ያረጋግጣል።

ይህንኑ መነሻ በማድረግም በትግራይ ታጣቂዎችን ትጥቅ የማስፈታት እና የማቋቋም ሥራዎች እየተሠሩ ነው፡፡ ትግራይን ጨምሮ በሚቀጥሉት ሁለት ዓመታትም 371ሺ የቀድሞ ታጣቂዎችን መልሶ ለማቋቋም የሚያስችሉ ሥራዎች እየተሠሩ ነው፡፡ ይህም የፕሪቶሪያውን ስምምነት ወደ ተሟላ ትግበራ ለማስገባት ከማስቻሉም በላይ በትግራይ ዘላቂ ሰላም ለማምጣት ወሳኝ ምእራፍ እንደሆነ ይታመንበታል፡፡

በአጠቃላይ ባለፉት ሁለት ዓመታት በትግራይ ዘላቂ ሰላም ለማስገኘት እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች ፍሬ ማፍራት ጀምረዋል፡፡ በተለይም መንግሥት በጦርነቱ በእጅጉ የተጎዳውን የትግራይ ሕዝብ መልሶ ለማቋቋምና ጦርነቱ ያሳረፈበትን ስነልቦና ለማከም በርካታ ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል። ከስምምነቱ መፈረም በኋላ የጥላቻውን ጉም በመግፈፍ ወደ ትግራይ በግንባር ቀደምነት የተጓዘው በአፈ ጉባዔው የተመራው የፌዴራል መንግሥቱ ልዑክ ነበር። ይህ ልዑክ ከተጓዘ በኋላ የቴሌኮሙኒኬሽን፣ የባንክና የአውሮፕላን አልግሎቶች በፍጥነት እንዲጀምሩ ተደርገዋል።

የትግራይ ጊዜያዊ አስተዳደር በተመሠረተ ጊዜ መሳሳብና መጓተትን ለማስቀረት ሲባል የአመራሩን ድርሻ ክልሉ እንዲወስድ በማድረግ ጊዜያዊ አስተዳደሩ ፋታ አግኝቶ ፊቱን ወደ ሰላምና ልማት እንዲያዞር ተደርጓል።

የግብርና ሥራውን ለማገዝ የሚመለከተው የሚኒስቴር መሥሪያ ቤት በክልል ደረጃ ከሚጠበቅበት በላይ ሠርቷል። ዩኒቨርሲቲዎችንና ትምህርት ቤቶችን ወደ አገልግሎት ለመመለስ የትምህርት ሚኒስቴር በርካታ ተግባራትን አከናውኗል። በክልሉ ተቋርጦ የነበረውን ትምህርት እንዲጀመር ከማድረግ ባሻገር ከሁለት ዓመታት በኋላ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ተማሪዎች እንዲወስዱ ምቹ ሁኔታን መፍጠር ተችሏል፡፡

የመከላከያ ሠራዊት የሕዝቡን ችግር ለመፍታት ከራሱ በጀት ቀንሶ አያሌ ተግባራት አከናውኗል። የሰላም ስምምነቱን እንደ ዕድል በመጠቀም ሕዝብን ከችግር በማዳን፣ መንግሥታዊና ማኅበራዊ አገልግሎቶችን በማስመጀር ኃላፊነቱን ተወጥቷል። ከፌዴራል መንግሥቱም አልፎ ክልሎች ከአነስተኛ በጀታቸውና ገቢያቸው በመቀነስ የትግራይ ክልልን ደግፈዋል።

ይሁን እንጂ በመንግሥት በኩል የተደረገውን ያህል የሚመጥን ምላሽ ከዚያኛው ወገን ተገኝቷል ማለት አይቻልም፡፡ በሰበብ አስባቡ የፕሪቶሪያውን ስምምነት የሚጋፉ ድርጊቶችና አሉታዊ ሃሳቦች ጭምር በየጊዜው ሲደመጡና ሲታዩ ሁለት ዓመታት አልፈዋል። ይህ ደግሞ የተጀመረው የሰላም ጥረት በሚፈለገው መልኩ ውጤት እንዳያመጣ እንቅፋት ሆኖ ቆይቷል፡፡

ሆኖም ይህ ሁኔታ ግን አንድ ቦታ ማብቃት አለበት ፡፡የትግራይ ሕዝብ በሰላም የመኖር እና የማደግ መብት እንዳለው መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ብልጭ ድርግም የሚለው የሰላም ሁኔታ ተሻሽሎ ዘላቂነት ባለው ሁኔታ የሰላም አየር በክልሉ ሊነፍስ ይገባል፡፡ ክልሉ ለበርካታ ዘመናት ያህል በጦርነት የተጎዳ በመሆኑ የበርካታ መሠረተ ልማት እጥረት እና የምግብ ዋስትና ችግር የሚስተዋልበት ነው፡፡

ይህን ክግምት በማስገባት መንግሥት የተለያዩ ጥረቶችን ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ ከእነዚህ ጥረቶች አንዱ የቀድሞ የትግራይ ክልል ታጣቂዎች ችግሮችን በሰላማዊ ውይይት በመፍታት ለሀገር ዕድገት በትብብር እንዲሠሩ የሚያስችል ዕቅድ ነድፎ ተግባራዊ ማድረጉ ተጠቃሽ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅትም በርካታ ቁጥር ያላቸው ታጣቂዎች የተሃድሶ ስልጠና በመውሰድ እና እራሳቸውን የሚያቋቁሙበት የገንዘብ ድጋፍ በማግኘት ወደ ሰላማዊ ህይወታቸው እየተመለሱ ነው፡፡

እነዚሁ ሰልጣኞች ባስተላለፉት መልዕክትም ስልጠናውን ወስደው ወደማህበረሰቡ ሲመለሱ የልማትና የሰላም አካል የሚሆኑበትን ዕድል እንደሚፈጥርላቸው ገልጸዋል፡፡ በስልጠናው መሠረት በሚደረግላቸው የገንዘብ ድጋፍ በግልም ሆነ በማኅበር በመደራጀት የተሻለ የልማት ስኬት ለማስመዝገብ ዝግጁ መሆናቸውን ተናግረዋል።

በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚስተዋሉ የሰላም ችግሮችንም በሰላማዊ ውይይት መፍትሔ በመስጠት ለሀገር ዕድገት በትብብር መሥራት እንደሚያስፈልግ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል። በቀጣይም አቅማቸው በፈቀደው ሁሉ የሀገር የልማት አካል በመሆን ለሰላም አማራጭ ቅድሚያ ሰጥተው እንደሚሠሩ አረጋግጠዋል።

ከዚሁ በሻገር ደግሞ ሰሞኑን የኦሮሚያ ክልል መንግሥት እና የኦሮሞ ነጻነት ሠራዊት ያደረጉት የሰላም ስምምነት ለኢትዮጵያ የሰላም እጦት እፎይታ የሚሰጥ ነው፡፡ በተለይም ደግሞ የኦሮሞ ነጻነት ሠራዊት ከመንግሥት ጋር በነበረው ቅራኔ በኦሮሚያ አለፍ ሲልም እንደሀገር በርካታ ቀውሶች ደርሰዋል፡፡ በርካታ የሰው ህይወት ተቀጥፏል፤አካል ጎድሏል፤ንብረት ወድሟል፡፡ ሆኖም በስተመጨረሻም በዚህ መልኩ ሰላም መውረዱ ለብዙዎቻችን እፎይታ የሰጠ ነው፡፡

በሌላም በኩል ራሱን "የቅማንት ታጣቂ ቡድን" ብሎ የሚጠራው ኃይል የመንግሥትን የሰላም ጥሪ ተቀብሎ በሰላማዊ መንገድ በምህረት ለመግባት መስማማቱን ገልጸዋል። በሀገር ሽማግሌዎች አገናኝነት በተደረገው ውይይት "የቅማንት ታጣቂ ቡድን" የመንግሥትን የሰላም ጥሪ ተቀብለው በሰላማዊ መንገድ በምህረት ለመግባት ተስማምቷል።

በቀጣይም በሥራቸው ያሉ እስከ 250 የሚደርሱ አባሎቻቸውን ይዘው መንግሥት በሚሰጣቸው አቅጣጫ መሠረት የተሃድሶ ሥልጠና ወስደው ወደ ቀደመ ሕይወታቸው እንደሚመለሱም መግባባት ላይ ተደርሷል። ታጣቂዎቹ ከሕዝባቸው ጋር በመቀላቀል ከሀገር ሽማግሌዎች፣ ከቀበሌ መሪዎች እና ከመንግሥት አካላት ጋር አብረው ለመሥራት ተስማምተዋል። የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት አባቶች እና የአካባቢው ማኅበረሰብም ታጣቂዎችን ለማቋቋም በመንግሥት በኩል የሚደረገውን ጥረት በልዩ ልዩ መንገድ ለመደገፍ እንደሚሠሩ ገልጸዋል።

እነዚህ የሰላም ጥረቶች ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ለሰላም ያላትን ቁርጠኝነት ያሳዩ ናቸው፡፡ መንግሥትም ከየትኛውም ወገን ጋር ቢሆን ሰላም ለማውረድ ያለውን ቁርጠኝነት ያመላከቱ ናቸው፡፡

ሆኖም አሁንም ቢሆን የተሳሳተ አማራጭ ወስደው በየጫካው የሚገኙ ቡድኖች አሉ፡፡ እነዚህ አካላት ከጦርነት ይልቅ ሰላምን በመምረጥ ለሀገራቸው ውለታ ሊውሉ ይገባል፡፡ በረባ ባልረባው በሚነሳ ጦርነት እና ግጭት እየተሰቃየ ያለውን ሕዝብም መታደግ እና የሰላም አየር እንዲተነፍስ ማድረግ ይገባል፡፡

ከሰላም እንጂ ከጦርነት የሚገኝ ነገር እንደሌለ በመገንዘብ ሁሉም አካላት ፊታቸውን ወደ ሰላም ማዞር ይጠበቅባቸዋል፡፡ ኢትዮጵያ ዛሬ የሚያስፈልጋት አንድነት እና ወንድማማችነት ነው። ኢትዮጵያ ለዘመናት በጦርነት የቆሰለች ሀገር በመሆኗ ከዚህ በላይ ጦርነት እና ግጭትን የሚሸከም ትከሻ የላትም፡፡

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

## ኦዳ በአፍሪ ሜዳ

ሙሉጌታ ብርሃኑ

ውቧ ወርቃማ ወፍ በጥበብ ሰማይ በራሪ እንደ ኦሮዮን ኮኮብ መስላ የአፏን ፍሬ ከለምለም መስኩ ላይ ጣል አድርጋው ነበር፡፡ ፍሬው እንቡጥ ያማረ ዘር ሆኖ ዛሬ ልክ እንደ ኦዳው ዛፍ ከሜዳው ላይ ተንዠርግጓል። ለምለሙ አረንጓዴ ሜዳ በኦዳ ቅርንጫፎችና ቅጠሎች ከላይ ተንጣሎ፣ ከስር ጥላው ለጥበብና ጠቢባን ማረፊያ ሆኗል፡፡

ሜዳው ኦዳ አፍሪ፣ ጥበብ አፈራሽ ነው፡፡ ኦዳም ስሩን እየሰደደ፣ ግንዱ ሽቅብ ወደላይ፣ ቅርንጫፎቹም በአራቱም ማዕዘናት “አፍሪ! አፍሪካ!” ሲሉ በኅብረ ዝማሬ እየተንሰራፉ ከሀገር ወጥተው ጉዞ ወደ ምሥራቅ አፍሪካ ብለዋል፡፡ ትንሽዬዋ ኦዳ በቅላ ሰማይ ጠቀስ መምዘግዘጓን ቀጥላለች፡፡

ከሰባት ዓመታት በፊት ከምለሚቷ የኦሮሚያ ጥበብ፣ ከተዋበው ሜዳ ላይ ብቅ ያለው ኦዳ ከክልል አጥር ዘሎ፣ ዛሬ ላይ ከኢትዮጵያም ወጥቶ በምሥራቅ አፍሪካ፣ በጥበብ ተራሮች አናት ላይ እንደ ችቦ በርቶ ከሩቅ ይታያል። ኦዳ ቅርንጫፎቹን በነፋሻማው ንፋስ እንደ ባንዲራ እያውለበለበ “አፍሪ አፍሪካ ላምባዲና፤ ኑ! ወደኛ ኑ! መዲና” እያለ ይጣራል፡፡ እስከ ዘንድሮው ዓመት ድረስ በመላው ምሥራቅ አፍሪካ ድምፁ ከፍ ብሎ ተደምጧል። ቀጣይ እያየለ መላውን አፍሪካ እንደሚያጥለቀልቀው ተስፋ ብቻ ሳይሆን ከልብ የሞላ እምነትም አይዋዥቅም፡፡

አሁን አሁን የሀገራችን የጥበብ ዋልታና ካስማ ጠንከር ማለት መጀመሩን እያስመለከተን ይመስላል፡፡ የጥበብ ባለውለታ ከዋክብቶቻችን በየዘመናቱ አስታዋሽ አጥተው እዬዬ! ሲያስብለን እንዳልነበር አሁን ከኛ አልፈን ወደ ጎረቤት ሀገራት ወደ አፍሪካ አደባባይ እየወጣን ያለን መስሎ ይታያል፡፡ ብርታት በወኔ ታላቅነትና ጥበብ አፍሪ መጋቢ ነው፡፡ “በርታ!” ያሉት ፈረስ እንኳን ቁልቁለት አዳልጦ፣ ዳገት አይዘውም፡፡

ደግ ደጉን በሠራ ቁጥር ሁሉ “በርታ አለንልህ!” ያሉት የጥበብ ልጅም ግዛቱ እስከዓለም መዳረሻ ነው፡፡ እነኚህ “በርታ!” ባዮችም ዛሬ ላይ በሀገራችን በርከት እያሉ መጥተዋል፡፡ ስራቸውን ስር እየሰደዱም አፍሪ ጠቢብ ሆነው፤ አኩሪ ጥበብ ከዋክብትን እያበዙ ናቸው፡፡ ከአንድ ወር በፊት የ10ኛውን የጉማ በረከት በልተን ጠጥተናል፡፡ አሁን ደግሞ ከኦዳ ሜዳው ላይ ዱብ! ዱብ! ጀምሯል፡፡

ከጉማ የ2 ዓመት ታናሽ የሆነው ኦዳ ስምንት ዓመት ሆነው፡፡ 8ኛውን ዙሩም አክሮ መጥቷል፡፡ ከኦሮሚያ ብቅ ብሎ ከመሐል አዲስ አበባ ፈንድቷል፡፡ ሀገራዊ ሆነ ከማለታችን በመግነጢሳዊ ፍጥነትና ለውጥ ፍንጥርጣሪው በመላው የምሥራቅ አፍሪካ ያደረገበትን ሁለተኛ ዓመት፣ 8ኛው ዙር የሚጠብቀው ኅዳር 27 ቀንን ነው፡፡ አዲስ አበባ የአፍሪካ መዲና እንደመሆኗ የምንለውና የሚያስፈልገንም ይኼው ነበር፡፡ መዲናነት የበኩርነት ነውና ጅማሬውን አስቀጥለን ገና መላውን አፍሪካ ማዳረስ ይጠብቀናል፡፡

በአዲስ አበባ ሰማይ ላይ ከፍ ብሎ መውለብለብ ያለበት ባንዲራዎቻቸው ብቻ ሳይሆን ጥበቦቻቸው ጭምር ነው፡፡ ሠገነቷ ለአፍሪካ የጥበብ ልጆች መናገሻ ማማ መሆን አለበት፡፡ ‹‹ማማ አፍሪካ...››

ጉዞው ተጀምሯል፡፡ ዓመታዊው ኦዳም ከክልል ተነስቶ የዚህ ጉዞ መሪና ጀማሪ ሆኗል፡፡ እንደ ክልል ጀምሮ እንደ አሕጉር ሊከሰት አስቧል፡፡ በባለፈው ዓመት የ7ኛ ዙር ላይ በምሥራቅ አፍሪካ ደረጃ ለማሳካት ችሏል፡፡ አጀማመሩ ሲታይ በ2010 ዓ.ም ሲነሳ ዓይኖቹን በኦሮሚኛ ቋንቋ በተሠሩ የጥበብ ሥራዎች ላይ ብቻ አድርጎ ነበር፡፡ ግን በረገጠበት እግሩን ተክሎ አልቀረም፡፡ በየዓመቱ አዳዲስ ነገሮችን ነስነስ እያደረገ ይበልጥ ጣፋጭ አድርጎታል፡፡

እስከ ሦስተኛ ዙር ድረስ በክልል ዛቢያ ተሽከርክሮ በመስፈንጠር በአራተኛው ዙር አንድ ከፍ ብሎ በሌሎች ቋንቋዎች የተሠሩ ሥራዎችንም በማካተት ሀገራዊነቱን አሳየ፡፡ ሁለት ዓመታትን በሀገር ቤት ቆይቶ በ7ኛው ዙር ወደጎረቤት አለ፡፡ ከመጀመሪያው አንስቶ 3...2...እያለ መጥቷልና ለመጪው አንድ ደግሞ አንድ ብሎ ክብረ ወሰኑን በመስበር አፍሪካ አደባባይ ላይ እንጠብቃለን፡፡

በሄደው ኅዳር 17 ቀን 2017 ዓ.ም አዘጋጆቹ የሚዲያ ጥሪ አድርገው ነበር፡፡ ሚዲያው ሁሉም ጠሪ አክባሪ ነውና ደርሶ ካሜራና ጆሮውን ሰጥቷል፡፡ የዚህ ዝግጅት ፊት ዘማቹ በሻቱ ቶሎማሪያም መልቲሚዲያ ጉዳዩን ከማብራሪያ ጋር አውግቶታል፡፡ ለዚህ ሽልማት ለእጩነት ያበቃው ቀን መቁጠር የጀመረው በ2016 ዓ.ም መስከረም 1 ቀን ሲሆን መጥቶ መጨረሻውን የገጨው በጳጉሜ 5 ቀን 2016 ዓ.ም ነው፡፡ 365 ቀናት ድፍን አንድ ዓመት ሞላ ማለት ነው፡፡ በእነዚህ ቀናት መካከል ከተሠሩ ሥራዎች ተመራርጠው ለመሸለም ተዘጋጅተዋል፡፡

ጠቅለል ባለው ቁጥራዊ መዳረሻው 14 ዓይነት ሽልማቶች በሦስት መቅረዞች ተቀምጠዋል፡፡ እኚህ ሦስት መቅረዞችም ሙዚቃ፣ መጽሐፍ እና የሕይወት ዘመን ናቸው፡፡ ከ14ቱ ስምንት ያህሉ በሙዚቃ የሰፈሩ




ናቸው። ምርጥ አልበም፣ ነጠላ ዜማ፣ የቪዲዮ ክሊፕ፣ ድምፅና ምርጡን ጥምረት ያካተት ነው፡፡ በመጽሐፍ ዘርፍ “የዓመቱ ምርጥ ልቦለድ” እና “የዓመቱ ምርጥ የግጥም መድብል” በሚል በሁለት ጎራ ተመድበዋል፡፡ በሕይወት ዘመን ተሸላሚነትም ሦስቶቹ ነጥረው ወጥተዋል፡፡

ደግሞ ሌላም አለ፤ “ኢስት አፍሪካን ሱፐር ስታር” የሚል፡፡ በኦዳ ቤተኛው ብቻ አይደማምቅም፤ የጎረቤት ጀመአው ሁሉ ሽር ብትን ሊልበት ነው፡፡ ከቀድሞዋ ልጅ ከኤርትራ፣ ከኬንያ፣ ግራና ቀኝ ከቆሙት ሁለቱ ሱዳኖች፣ ከሶማሊላንድ፣ ከዩጋንዳና ከሲሸልስ ታጅበው አዲስ አበባ ይገባሉ፡፡

መግባታቸው እንዳለ ሆኖ በባሕልና ቋንቋ ለየቅል የሆኑትን እኚህን ኦዳ በምንስ መስፈርትና እንደምን አድርጎ መረጣቸው? የብዙዎች ጥያቄ ሊሆን እንደሚችል ግልጽ ነው፡፡ በዚህ ደረጃ የራቁትን ቀርቶ እዚሁ በራስ ቋንቋን ባሕል የሠሩትንም አበጥሮ ማውጣቱ ምርኩዝ ያልተያዘበት ተራራ ነው፡፡ ይሁንና የምሥራቅ አፍሪካ ታላላቅ ከዋክብቱን በመመልመል ሂደቱ አዘጋጆቹ የተጠቀሙት መላ አዲስ አበባ ውስጥ በሚገኙት በየሀገራቱ ኤምባሲዎች በኩል ማለፍን ነበር፡፡ እነርሱም ልክ እንደኛው በኪነ ጥበብና ሥነ ጥበብ ዘርፍ የሚሠራ መንግሥታዊ ተቋም አላቸውና ከኤምባሲው ጋር ተጣምሮ የቤት ሥራውን ለተቋሞቻቸው ማስረከብ ነበር፡፡

የነርሱን ኮከብ የመምረጥ ኃላፊነቱን የወሰዱት ተቋማት እንደራሳቸው ፍላጎትና የኦዳን ቅኝታዊ እሳቤ በሚጣረስ መልኩ እንዳይሆን አስቀድሞ በዳኞቹ የተቀመጠው መስፈርት ተልኮላቸዋል፡፡ የቋንቋና ባሕል ሁኔታው እያንገዳገደም ቢሆን ዳኞቹም በተቻላቸው ሁሉ ተጨማሪ እይታና ግምገማ ለማድረግ ይጥራሉ፡፡

በዘንድሮው ኦዳ ስምንት የዝግጅቱ አጋሮችም በርከት ብለዋል፡፡ ከመካከል የኢትዮጵያ ባሕልና ስፖርት ሚኒስቴር ብቅ ብሏል፡፡ በመጀመሪያዎቹ ዓመታት ኦዳ ሽር ሲል የነበረው ከኦሮሚያ ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ ጋር ነበር፡፡ እርምጃውን አፈጣጥኖ ከክልል ሲወጣ በሀገር ከባሕልና ስፖርት ሚኒስቴር ተቃቅፏል፡፡ ከእንግዲህ ወዲያም የሚለያዩ አይመስልም፡፡

ጋዜጣዊ መግለጫ በተሰጠበት ዕለትም የባሕልና ስፖርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ፤ ክብርት ነፊሳ አልማህዲ ተገኝተው የጽ/ቤቱን እቅድ ሀሳብ አጋርተዋል፡፡ “አንጋፋዎቹን መሸለም ማለት ተተኪን ማፍራት ማለት ነው፡፡ ይህን ሲመለከቱ ከውስጣቸው ተነሳሽነትና የአዕምሮ ለውጥ ለመፍጠር ይቻላል፡፡ መሸለም ያለባቸው አካላት ያለምንም አድሎ መሸለም እንዲችሉም እኛ በሙሉ ደጋፊነት ከአዘጋጁ ጎን እንቆማለን” ብለዋል፡፡ እኛም የቆሙበት አያዳልጣቸው ብለናል፡፡

ከሙያዊ ድጋፍ ባሻገር በገንዘብ ቢሆን ወሳኝ ለሆኑ ጉዳዮች እጇን አጣምሮ እንደማይመለከት አንስተውታል። በጎን ደግሞ የበሻቱ ቶሎማሪያም መልቲሚዲያ ዋና ሥራ አስኪያጅ ራሷ በሻቱ ቶሎማሪያም ነበረች፡፡ “ኦዳ አዋርድ መለያው ያደረገው ታማኝነቱን፣ የውድድር ሂደቱን ከአድሎ የፀዳ፣ ሥራና ሥራን ማማከል ብቻ ነው” ብላለች።

ሁለቱ አካላት ከሌሎች ጋር ተጣምረው ከብሔር ብሔረሰቦች የጥበብ ጫካ ይገባሉ፡፡ የመንግሥት እንደራሴው የባሕልና ስፖርት ሚኒስቴር ካለው ልምድ መራጮቹን ይመርጣል፡፡ ተመራጭ ዳኞችም ምርጥ ምርጡን የጥበብ ሰው አድነው ያቀርባሉ፡፡ ከሀገር ውስጥ ትልቁ ኮታ በኦሮሚኛ ለተሠሩ ሥራዎች ቢሆንም ሌሎቹም ቀላል አይደሉም፡፡

ኦዳ በአንድ ቋንቋና ብሔር የተሠራ ቅርጫት እንዳይሆን በኅብር ተውቧል፡፡ በባለፈው ዓመት አፋር፣ ቤንሻንጉል፣ ሶማሌ፣ ሐረሪና ሲዳማ ገብቶ ታላላቆችን አውጥቷል፡፡ በዘንድሮው ደግሞ ከኦሮሚያ ባሻገር ወደ ትግራይና ቤተ ጉራጌ ገብቷል፡፡

የኦዳ ትልቁ ዓላማ የሠራውን በሥራው መሸለም ስለሆነ ሥራን ከሥራ፣ ሠሪን ከስሩ መመልመሉ እንደመሸለም ቀላል ነገር አይደለም፡፡ ከመሸለም ከባዱ የሚሸልሙትን አንጥሮ ማውጣቱ ላይ ነው፡፡ ባሕልና ስፖርት ሚኒስቴርም ለታላላቅ የሀገራችን የሙያ ጠበብት ካለው ቅርበት በመነሳት ይህቺን አቅጣጫ ለማሳለጥ ማሰቡ መልካም ነው፡፡ በዚህ የሁለትዮሽ መረጣም ዓይኖቻቸው ያረፈው በጥበብ ብቻ ሳይሆን በቀለምም ወደመጠቁት ሆኗል፡፡ በምርምር ሥራዎቻቸው ልቀው የሄዱትንና በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ውስጥ በመምህርነት የቀለሙትን መርጠዋል፡፡ እንግዲህ በኦዳ መድረክ ላይ ሲምነሸነሹ የምንመለከታቸው ሁሉ የእነዚህ ዳኞች የፍርድ ውሳኔ ናቸው፡፡ ዳሩ ግን በሙዚቃው ዘርፍ በምንመለከታቸው ላይ 30 ከመቶው በሕዝብ ውሳኔ የሚጸና ነው፡፡ ለምርጫው የምርጫ ካርድ ሳያወጡ በእጅ ስልክ 8030’ን ጠቅ በማድረግ የፈለገ ሁሉ የራሱን ጀግና ለማንገስ ይችላል፡፡

ኦዳ 2017 ለክብር አጭቶ በሕይወት ዘመን ተሸላሚነት ያሰፈራቸውን አስቀድሞ ይፋ አድርጓል፡፡ ብሔር ብሔረሰባዊ አድርጎ ለሁሉም የወጣው ወደ ሙዚቃው ተራራ ነው፡፡ ታዲያ ከመካከል አንዱ የሆነውን ድምፃዊ ኪሮስ ዓለማየሁን ሲጠሩ፤ ከሞተ ስንቱ ዓመት አልፏልና ምን ነካቸው ያስብል ይሆናል፡፡ ግን ጠቢብ እንጂ ጥበብ ሞታ አታውቅም፣ ሠሪን እንጂ ሥራንም አፈር አይበላውም፡፡ መቃብርም ችሎ አይውጠውም፡፡

የሽልማቱ ገበታዎች ሥራዎቹ ናቸውና እርሱ በሕይወት ኖሮ ባይቀበልም ሥራዎቹ ቆመው በጭብጨባና ፉጨት ያግሉታል፡፡ እነርሱ ተቀብለው በማይሞተው ስሙ አናት ላይ እንደ ክብር አክሊል ያኖሩለታል፡፡ አፈሩን ገለባ ያድርግለትና በትግርኛ ሙዚቃዎቹ አብዝተን የምንወደው ኪሮስ ዓለማየሁ አንደኛው ነው፡፡ ሴቷ ድምፃዊት እልፍነሽ ቀኖ በኦሮሚኛ ትከተላለች፡፡ ሰቦ ሶሬሳ ደምሴ ተካ ደግሞ በጉራጊኛ ሙዚቃ ለሦስት አብረው የክብር ጃኖ ይለብሳሉ፡፡

የኦዳ አካሄድ አንድም በጋራ መቆም ስንችል ምንም ነገር ያለምንም ገደብ ለማድረግ እንደምንችል የሚያሳየን ነው፡፡ ወጪ ካሉ በጠቅላላው ለዚህ ዝግጅት የሚያስፈልገው ከ6 ሚሊዮን ብር በላይ እንደሆነ አንስተውታል፡፡ ነገር ግን ኦዳ ባለው አቅም ይሄ የሚታሰብ አይደለም፡፡ አንድነት ኃይል ያደረገው ነገር ከግማሽ በላይ ወይም ግማሽ ያህሉ የተሸፈነው በአጋር አካላትና በሌሎች ሙያዊ፣ ቁሳዊና የጉልበት በመሳሰሉትን የበጎነት ችሮታ ነው፡፡

መንገዱን ቀይሶ፣ ንድፉን በቦታና ጊዜ፣ ምስለ መልኩን በልብ ወረቀት ካሰፈሩት ሕንፃውን የሚያቆመው አይጠፋም፡፡ አነሳሽ ይኑር እንጂ የሚነሳው ብዙ ነውና ለሌሎችም ብርታት ይሆናል፡፡

በ2016 ዓ.ም ጀንበር፣ ከመስከረም 1 ንጋት እስከ ጳጉሜ 5 አመሻሽ በየወራቱና ሳምንታቱ ከሥራዎቻቸው ብልጭታ ጋር ብቅ እያሉ ሲያበሩ ከነበሩት የኦርዮን ከዋክብት መካከል ኦዳ 2017 ሌላ እነማንን መርጦ... ከኢትዮጵያ አይድል ተነስቶ በማይጠገብ የኦሮሚኛ አልበሙ መላው የሙዚቃ አፍቃሪ በእግሮቹ ቆሞ ያጨበጨበለት አንዷለም ጎሳ (ቢሊሌ) በምርጥ የቪዲዮ ክሊፕ እንዲሁም በሁለቱም ዘርፎች ተካቷል፡፡ ለምለም ኃይለሚካኤል (ዋለኔ) በምርጥ የቪዲዮ ክሊፕ፣ በዓመቱ ምርጥ ሴት ድምፃዊት፣ ቀጥሎም በሦስተኛው የነገ ተስፋ ከተጣለባቸው ምርጦቹ እንቡጥ መካከል ተካታለች፡፡

ሌላኛዎቹ ባለተስፋ ደግሞ አዳዲስ ባለተስፋዎች አሳንቲ አስቹ (ሚራራ ኮ)፣ ሐና ተስፋዬ (ሎቴ)፣ መሳይ በቃሉ (ሌሎ)፣ አብሳ አዱኛ (ታካ ታካ) ናቸው፡፡ በዓመቱ ምርጥ ሴት ድምፃውያን ጉብታ ላይ በእጩነት አሳንቲ አስቹ (ሚራራ ኮ)፣ ኤልሳ ንጉሴ (ጉዲን)፣ ሐና ተስፋዬ (ሎቴ)፣ ያኔት ድንቁ (ዳማ ዳሙ) ተቀምጠዋል፡፡

ሹክሪ ጀማል (ፍርቱ)፣ አብራር እንዳለ (ዳዎ)፣ ሌንጮ ገመቹ (ዋላቡ)፣ ሌንጮ ጉዲና (ሲን ማራሩ) በነጠላ ዜማዎቻቸው የዓመቱ ምርጥ ለመሆን በዕጩነት ተካተዋል፡፡ አብዲ ሃጫሉ (ኪሊማንጃሮ)፣ ጉቱ አበራ (ኢዮሌ)፣ ዮናን ብሩክ (አዋሽ) የምርጥ የቪዲዮ ክሊፕ ዕጩዎች ሆነዋል፡፡ ሌላኛውና ከፍ ያለው የ2016 ዓ.ም ምርጡ የአልበም ሥራ የማን ይሆን የሚለው ነው፡፡ በዚህ ዘርፍ ዕጩ ሆነው የቀረቡት ጉቱ አበራ (ጋፊኮ)፣ ሞቲ ሮባሌ (ዱጋ)፣ ተስፋዬ ጥላሁን (ኤባ) አልበሞች ናቸው። እያንዳንዱ ሙዚቀኛ በሜዳው መምና በዙሪያው ማራቶን ሁሉ ሮጦ በግል ክብረወሰኑን ለመስበር ከምርጥ ሥራው ጋር ሜዳዩን ይጠባበቃል፡፡

ከግል ጥረት ወጣ ብሎ በኦዳ ምርጡ ጥምረት እንደ ቡድን ሥራ እነማን ነበሩ? ይላል፡፡ ጣምራዎቹ ዕጩዎችም አዳም መሐመድና ጫልቱ ቡቶ (በጋዳ ማሌ)፣ አወል ሲሮና ሃሊማ አብደላ (በሻኒ ኬሳ)፣ ጫልቱ ናኔሶና ባሮ ዲዳ (በኬ አና)፣ ካሊድ አማንና ሌንጮ አብዱሻኩር (በ ና አማን)፣ ተስፋዬ ጥላሁንና ሃልኮ ቃሳሮ (በአርሲ ባሬዳ) አንደኛው ጥምረት ዋንጫውን ከፍ ያደርጋል፡፡ የምሥራቅ አፍሪካ ከዋክብትም ከፍ ብለው ይቀጥላሉ፡፡

ከሙዚቃ ሥራዎች ውጪም ባለቅኔዎቹ ገጣሚያንና ብዕረኞቹ ደራሲያን ይቀጥላሉ፡፡ የክብር ካባ ደርበው፣ ለውለታቸው ትንሽ ትልቁ ሁሉ ከፍ ዝቅ ብሎ የሚያመሰግናቸው የሕይወት ዘመን ተሸላሚዎችም የምንጊዜም ምርጦች ሆነው ይነግሳሉ፡፡

ከአንጋፋው እስከ አዳዲስ ጀማሪ ከዋክብት በዚህ ልክ ሁሉም ልኩን ያገኛል፡፡ ዕጩዎች በታዛቢነት ቆመው ሥራዎቻቸው ከሌሎች ሥራዎች ጋር አንገት ላንገት ከሜዳው ላይ ትግል ይገጥማሉ፡፡ ዳኞች በትኩረትና በጥንቃቄ እያንዳንዱን እየመረመሩ ያወዳድራሉ፡፡ የአሸናፊዎቹ ሁሉ አሸናፊ ሆነው በድል የረቱ ሥራዎች፤ ለባለቤቶቻቸው የኒሻን ዓርማ ሆነው ድል በድል ይደምቃሉ፡፡ የዋርካ ጥላው ኦዳ ነው፡፡ ሜዳው የጥበብ ነው፡፡ ጥበብና ጥበበኛው ሁሉ ወደ ሜዳው ገብቷል፡፡

ከሜዳው በላይ ከፍ ብሎ የቲፎዞው ድምፅ ይሰማል። ካታንጋ የለ ሚስማር ተራ፤ አኩሪና አፍሪ ሁሉም ሸራተን አዲስ ነው፡፡ ሁሉም በነገው እለት ችቦውን ያበራል፡፡ ደማቁ አመሻሽም በኦሪዮን ኮከብ፣ ከክዋክብቱ ጋር ሽር ብትን ይላል፡፡

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## በዕድሜ ማምሻ ላይ...

መልካምሥራ አፈወርቅ

ወደምገባው ማዕከል ለመግባት ጉዞ ከጀመሩት በርካቶች መሀል የአንዱ አዛውንት ሁኔታ ዓይን ይስባል፡፡ ዕድሜ የሰበረውን አንገታቸውን ዝቅ አድርገው ወደ ውስጥ ያማትራሉ፡፡ በእጃቸው የያዙትን የምሳ ዕቃ እንዳጠበቁ ነው፡፡ በጥልቅ ሃሳብ መናዋዛቸው ያስታውቃል፡፡ በልቦናቸው ምን እንዳለ ባላውቅም ውስጣቸው በትካዜ ስለመያዙ ነጋሪ አላሻኝም፡፡

አስተውሎ ላያቸው ገጽታቸው በእጅጉ ያሳዝናል። የዕድሜ ጅረት ያለፈበት አካላቸው የትናንቱን ውጣውረድ እየመሰከረ ነው፡፡ በአዛውንቱ ውስጠት ብዙ ድካም መኖሩ ያስታውቃል፡፡ የእስከዛሬው ህይወታቸው ስለማንነታቸው ይመሰክራል፡፡

እሳቸው እስካሁን በበዛ ችግር ተንገላተዋል፡፡ በመከራ ተፈትነዋል፡፡ ኑሯቸውን ላስተዋለው አሁንም ዛሬም ህይወታቸው ከዚህ እውነት የራቀ አይደለም። ከዕድሜ፣ ከኑሮና ሕይወት ጋር ትግል ገጥመዋል፡፡ በሕይወት ለመዝለቅ የሁል ጊዜ ትግላቸው ቀጥሏል፡፡ ሁሌም ይታትራሉ፣ ላለመውደቅ ይታገላሉ፡፡

አሁን ላይ በእጃቸው የጨበጡት ሰሀን ደግሞ ለእሳቸው ውስጡ እንጀራ ብቻ አይደለም፡፡ ውስጡ ዕልፍ ሚስጥር የተቋጠረ ታሪክ ፣የሚነገር ሕይወትን ይዟል፡፡ ..ገመቹ አመንሲሳ

በአቃቂ ሰፊ መስክ ላይ እሱን ከመሰሉ ህጻናት ጋር ሲዘል፣ ሲጫወት፣ አድጓል፡፡ እረኝነት ለእሱ የቀደመ ሕይወቱ ነው፡፡ ዕድሜው ከፍ ሲል መልካም ገበሬ ሆነ፡፡ ከእርሻው ውሎም እንደወጉ ምርቱን አፈሰ፡፡ ጎተራውን ሞላ፡፡ ጥቂት ዓመታትን የዘለቀበት የግብርና ውሎ ከኪሳራ አልጣለውም፡፡ በጉልበቱ ድካም፣ በላቡ ወዝ አሳድሮታል፡፡

አሁን ግን ልቡ የመሀል ሀገር ኑሩን ሸቷል፡፡ ጧት ማታ ከተማ ሄዶ መኖርን እያሰበ ነው፡፡ የገጠር ሕይወት መሠረቱ ቢሆንም ዛሬ ላይ ልቡ ለውጥ እየፈለገ ርቆ መሄድን አስቧል፡፡ ገመቹ በውሳኔው ጸንቷል፡፡ ልቡ መንገድ ካሰበ ወዲህ ዕንቅልፍ ይሉት ርቆታል፡፡ ከቀዬው ተቀምጦ ከመቆዘም ራቅ ብሎ ቢሠራ እንደሚበጅ ከገባው ቆይቷል፡፡

ከአዕምሮው ደጋግሞ መከረ፤ ከውስጡ ተስማማ፣ ከቤቱ ወጥቶ ከቀዬው ራቀ፡፡ ገመቹ አሁን የከተሜ ሰው ሆኗል፡፡ አቃቂንና አካባቢውን ርቆ መሀል ሀገር በገባ ጊዜ የመጀመሪያ መተዳደሪያው የቀን ሥራ ሆነ፡፡ ውሎ አድሮ ከአንድ ድርጅት በቋሚነት ተቀጠረ፡፡ ያም ሆኖ ውሎው ከጉልበት ሥራ አላለፈም፡፡

ከቀን ሥራ በወር የሚያገኘው ገቢ በቂው ነው። የቀድሞ ህልሙ መልካም ገበሬ ሆኖ ምርት ማፈስ ነበር፡፡ አሁን ደግሞ እግሮቹ ሌላ ዓለም ላይ ቆመዋል። እንዲያም ሆኖ ባለበት ሕይወት አልተከፋም፡፡ ጉልበቱን ከፍሎ በላቡ ወዝ ያድራል፡፡

ገመቹ ዓመታትን በገፋበት የአዲስ አበባ ኑሮ አዲስ ሕይወትን ጀምሯል፡፡ አብሮት የቆየው የጉልበት ሥራ ልምድ ሆኖትም በአዲስ ሥራና መሥሪያቤት በደሞዝ ተቀጥሯል፡፡ ይህ አይነቱ ለውጥ ለገመቹ ሌላውን የሕይወት ምዕራፍ ከፈተ፡፡ የግራ ጎኑን ባገኘ ጊዜ ትዳር ይዞ ጎጆ ቀለሰ፡፡ ጅማሬው መልካም ሆነለት፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላም ዓይኑን በዓይኑ አየ፡፡ የግራ ጎኑን ካገኘ ወዲህ ብቸኝነቱ ቀረ፡፡ ለእኔ ማለት ተወግዶ ለእኛ ማለትን ያዘ፡፡

በትዳራቸው አራት ልጆችን ያፈሩት ጥንዶች «አንተ ትብስ፣ እኔ እየተባባሉ ኑሮን መግፋት ይዘዋል። ለሚኖሩበት የቀበሌ ቤት ብዙ ክፍያ አይጠየቁም። ገቢያቸውን አቻችለው ልጆቻቸውን ያሳድጋሉ፡፡ በህንጻ ግንባታ ሥራዎች ለበርካታ ዓመታት የቆየው ገመቹ አሁን በዕድሜው ገፍቷል፣ በሥራ ብዛት ደክሟል፡፡

እንደትናንቱ ሮጦ ለማደር፣ ለፍቶ ለማግኘት እየጣረ አይደለም፡፡ ድካም እየረታው፣ ዕድሜ እየፈተነው ቤት መዋል ከያዘ ዓመታት ተቆጥረዋል። ዛሬ የቀድሞው ጎልማሳ በቀድሞ አቋሙ አይደለም። ከሥራው በጡረታ ከተሰናበተ ቆይቷል፡፡ እሱና ባለቤቱ ኑሮ እየከበዳቸው ሕይወት እየፈተናቸው ነው፡፡

ልጆቻቸው ከጎናቸው አይደሉም፡፡ ሁሉም በራሳቸው ዓለም ለራሳቸው ሕይወት እየሮጡ ነው። አዛውንቶቹ ባልና ሚስት ዛሬም በፍቅር ይኖራሉ፡፡ የዘንድሮ ኑሮ በአቅማቸው ልክ አልሆን ቢል በችግር ሊያልፉ ግድ ብሏል፡፡ ከጡረታ ክፍያ የሚገኘው ገንዘብ ከዕለት ወጪ አይዘልም፡፡ አንዱን ቀዳዳ ሲደፍኑት ሌለው ተከፍቶ ይታያል፡፡ ሌላውን ሞላ ሲሉት ጎዶሎው ይሰፋል፡፡ በቂ ገቢ የሌላቸው ዕድሜ ጠገቦች ችግር እያንገላታ ድህነት ይፈትናቸው ይዟል፡፡

የገመቹ ባለቤት ጤና ካጡ ቆይቷል፡፡ ቤት መዋል ከጀመሩ ወዲህ ተስፋና ረዳታቸው ባለቤታቸው ብቻ ናቸው፡፡ የሁለቱም ዕድሜ ገፍቷልና፡፡ አቅማቸው እየደከመ ነው፡፡ ይህ እውነታ ገመቹን በአክብሮት «አንቱ» ብዬ እንድጠራቸው አስገድዶኛል፡፡ አሁን ከአቶ ገመቹ ጋር ጭውውት ይዣለሁ፡፡

የተገናኘነው ልደታ ክፍለከተማ ከሚገኘው የምገባ ማዕከል ውስጥ ነበር፡፡ አረፍ ብለን ጨዋታ ከመጀመራችን በፊት በእጃቸው አጥብቀው የያዙትን የላስቲክ ቋጠሮ በዓይኖቼ መረመርኩ። አልተሳሳትኩም፡፡ በፌስታል የታሰረው ቋጠሮ ምግብ የያዘ የምሳ ዕቃ ነው፡፡

በምገባ ማዕከሉ በርካታ አቅመ ደካሞች፣ አካል ጉዳተኞች፣ እናቶችና ልጆች የያዙ ሴቶች በሰዓታቸው ተገኝተዋል፡፡ ቤቱ በእንጀራና በትኩስ ወጥ ሽታ እየታወደ ነው፡፡ ከቀረበው ማዕድ ተካፍለው፣ ከልብ አመስግነው የሚወጡትን አስተዋልኩ፡፡

የአዛውንቱ ገመቹ ሁኔታ ግን ከሌሎች ሁሉ ይለያል፡፡ እሳቸው እንደሌሎች እንጀራቸውን በትኩስ ወጥ እየጎረሱ፣ ከውሃው ሲጎነጩ አልተመለከትሁም። ከወሰዱት ምግብ አንዳች ሳይቀምሱ በምሳ ዕቃ ቋጥረው ከአዳራሹ ለመውጣት ተዘጋጅተዋል፡፡

የመጡበትን በወጉ አለማድረሳቸው እያስገረመኝ ነው፡፡ ስለምን እንዲህ ሆነ? ጥያቄው በአዕምሮዬ ተመላለሰ፡፡ አይቼ ዝም ማለት አልቻልኩም። የውስጤን ሃሳብ ፈጥኜ አወጣሁት፡፡ አዛውንቱን በቀስታ እያወጋሁ ጠየኳቸው፡፡

ገመቹ ከፉና ደጉን በእኩል የተጋሩት ባለቤታቸው በህመም ከአልጋ መዋል ከያዙ ቆይቷል፡፡ በሽታቸው የከፋ ነውና መላ አካላቸው አይታዘዝም። ሚስታቸውን ከማስታመም ባለፈ የቤቱን ሥራ የሚከውኑት ሽማግሌው አባወራ ናቸው፡፡ ብዙ ጊዜ ከቤት የሚላስ የሚቀመስ ሲጠፋ ጥንዶቹ የዘመድ ጎረቤቱን እጅ ሊያዩ ግድ ይላቸዋል፡፡

ባለቤታቸው በህመም አልጋ ይዘው ቤት ከዋሉ ወዲህ የገመቹ የዓመታት ግዴታ እሳቸውን መንከባከብና የቤቱን ሥራ መሸፈን ሆኗል፡፡ አሁን ባሉበት ዕድሜ ጎንበስ ቀና ማለቱ በእጅጉ ይከብዳል። ዓመታትን በትዳር ከእሳቸው የዘለቁት ሚስት ከባለቤታቸው ሌላ «አለሁ» ባይ አጋር የላቸውም፡፡

ገበና ሸፋኛቸው፣ አልባሽ ፣አጉራሻቸው አዛውንቱ፤ ግማሽ አካላቸው፣ የልጅነት ባላቸው ብቻ ሆነዋል፡፡ ከዓመታት ወዲህ ሕይወት በሁለቱ አዛውንቶች ቤት ከባድ ሆኖ ዘልቋል፡፡ አሁን የአዛውንቱ የምሳ ዕቃ ምስጢር ተገልጦልኛል፡፡ ሰውዬው አንዳች ሳይቀርሱ፣ ሳይቀምሱ ይዘው መውጣታቸው እንደሁልጊዜው ከሚስታቸው ጋር በእኩል ለመጋራት ነው፡፡

ሽማግሌው በምገባ ማዕከሉ የመጠቀም ዕድል ካገኙ ወዲህ የሚሰጣቸውን ምግብ እንደቋጠሩ ከቤት ይወስዳሉ፡፡ ሁሌም ለታማሚ ባለቤታቸው ያጎርሳሉ፡፡ ለእሳቸውም ይቀምሳሉ፡፡ የዚህ የምገባ ማዕከል በረከት የአዛውንቶቹ ባልናሚስት የዘወትር ልምድና የብዙ ችግራቸው ማቅለያ ሆኖ ቀጥሏል፡፡

# ዓለም አቀፍ

## ሩሲያ እና አሜሪካ በሶሪያው ጦርነት መባባስ እርስ በእርስ ተካሰሱ

ሰሞኑን በተመድ በተካሄደው የጸጥታ ምክር ቤት ስብሰባ ላይ በሶሪያ የተቀሰቀሰው ጦርነት እንዲባባስና ሽብርተኝነትን በመርዳት ሩሲያ እና አሜሪካ እርስ በእርሳቸው ተካሰዋል።

የሶሪያ አማጺያን አሌፖ የተባለችውን ከተማ ባለፈው ሳምንት ተቆጣጥረዋል። የዚህ አማጺያን ቡድን መሪ ሀያት ታህሪር አል-ሻም ሲሆን እኤአ በ2016 በይፋ ከመገንጠሉ በፊት በሶሪያ የአልቃ ኢዳ ክንፍ ነበር። በተመድ የጸጥታው ምክር ቤትም ማዕቀብ ተጥሎበታል።

በተመድ የአሜሪካ ምክትል አምባሳደር ሮበርት ውድ በሶሪያ ያለው ግጭት እንዲቆም እና ንጹሃን ከጥቃት እንዲጠበቁ ጥሪ አድርገዋል። የአማጺያኑ እንቅስቃሴ በሀያት ታህሪር አልሻም መመራቱም እንዳሰጋቸው አምባሳደሩ ገልጸዋል።"ሀያት ታህሪር አልሻም በአሜሪካ እና በተመድ ሽብርተኛ ተብሎ መፈረጁ ብቻ በአሳድ አገዛዝ እና በሩሲያ የሚፈጸሙ ግፎችን ምክንያታዊ አያደርጋቸውም" ነው ያሉት ውድ።

አምባሳደሩ የሶሪያውን ፕሬዚዳንት በሺር አላሳድን እና ሩሲያን በትምህርት ቤቶች እና ሆስፒታሎች ላይ ጥቃት በማድረስ ከሰዋል። የሩሲያው የተመድ አምባሳደር ቫሳሊ ነበንዚያ ለውድ በሰጡት ምላሽ" በሰላማዊ የሶሪያ ከተሞች ላይ የደረሰውን የሽብር ጥቃት ለማውገዝ ወኔ የለህም" ብለዋል።

"ዋሽንግተን ዓለም አቀፍ ሽብርተኝነት ትዋጋለች የሚል እምነት የለም" ሲሉ ንበንዚያ ተናግረዋል። "ግልጹን ለመናገር አሁን ላይ ከእናንተ በተቃራኒ በመቆማችን ደስተኞች ነን።" ነው ያሉት፡፡

አምባሳደር ወድ በበኩላቸው ነበንዚያ "በዚህ ጉዳይ እኛን ሊያስተምር አይችልም"፤ ምክንያቱም ሞስኮ "በመላው ዓለም ሽብርተኞችን የሚረዱ አገዛዞችን ትረዳለች" ሲሉ መልሰዋል። አምባሳደሩ አሜሪካ ለበርካታ አስርት ዓመታት በመላው ዓለም



ሽብርተኝነትን መዋጋቷን እና ይህንኑ ተግባሯን እንደምትገፋበት ተናግረዋል።

እኤአ ከየካቲት 2022 ሩሲያና የዩክሬን ጦርነት ተከትሎ የሩሲያ እና የአሜሪካ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት በከፍተኛ ውጥረት ውስጥ መግባቱን ጠቅሶ አል ዐይን ዘግቧል።

## ወታደራዊ ሕግን ለመደንገግ በሞከሩት ፕሬዚዳንት ላይ ክስ የመመሥረት ሂደት ተጀመረ

ፓርላማው ሀገራቸው በወታደራዊ ዕዝ ሥር እንድትሆን ባወጁት የደቡብ ኮሪያው ፕሬዚዳንት ዩን ሱክ የዎል ላይ ክስ የመመሥረት ሂደት ጀመረ ። የደቡብ ኮሪያ ፓርላማ አባላት በአስቸኳይ የፕሬዚዳንቱን ድንጋጌ ከሻሩ በኋላ ፕሬዚዳንቱ ውሳኔያቸውን ለመቀልበስ ተገደው ነበር።

ፕሬዚዳንቱ ወታደራዊ ሕግን ለመደንገግ ካደረጉት ያልተሳካ ሙከራ ጋር በተያያዘ የሀገሪቱ ሕግ አውጪዎች ክስ ለመመሥረት ሂደት ጀምረዋል። የደቡብ ኮሪያ ዋና ተቃዋሚ ዴሞክራቲክ ፓርቲ ክሱን ካቀረበ በኋላ የፕሬዚዳንቱን ወታደራዊ ሕግ "የአመጽ ባህሪ" ሲል አውግዞታል። ፓርላማው በፕሬዚዳንቱ ላይ ክስ ይመሥረት በሚለው ላይ ቅዳሜ፣ ኅዳር 28/2017 ዓ.ም. ውሳኔ ይሰጣል።

ደቡብ ኮሪያ በወታደራዊ ሕግ (ማርሻል ሎው) ስር



እንድትሆን የታወጀው የፕሬዚዳንቱ ትዕዛዝ በፓርላማ አባላት ታግዷል። ሕጉ መታገዱን ተከትሎ ፕሬዚዳንቱ አወዛጋቢ የተባለውን ሕግ ለማንሳት ተገደዋል። የደቡብ ኮሪያ ፕሬዚዳንት ዴሞክራሲ በሰፈነባት ሀገራቸው በወታደራዊ ሕግ (ማርሻል ሎው) ስር እንድትሆን በድንገት ማክሰኞ፣ ኅዳር 24/2017 ዓ.ም. ማወጃቸው ሀገሪቱን ያስደነገጠ ክስተት ሆኗል።

ፕሬዚዳንት ዩን ሱክ የዎል ሀገሪቱ በአምስት አስርት ዓመታት አይታው የማታውቀውን ይህንን አስደንጋጭ ውሳኔ ለመወሰን ምክንያታቸው "ፀረ መንግሥት ኃይሎች" እና የሰሜን ኮሪያን ስጋት በመጥቀስ ነው። ፕሬዚዳንቱ ከሰሜን ኮሪያ ኮሚኒስት ኃይሎች አገራቸውን ለመጠበቅ ወታደራዊ ሕጉ አስፈላጊ ነው ሲሉ ተናግረዋል።


ነገር ግን ወታደራዊ ሕጉ በታወጀ ሁለት ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የፓርላማ አባላቱ ፕሬዚዳንቱን ተቃውመው በምክር ቤት ከተሰበሰቡ በኋላ አስቸኳይ ድምጽ በመስጠት ውሳኔውን አግደዋል። ፕሬዚዳንቱ ይህንን ሕግ እንዲያውጁ ምክንያት የሆናቸው እሳቸው እንዳሉት የውጭ ኃይሎች ስጋት ሳይሆን ውስጣዊ የፖለቲካ ችግሮች እንደሆኑ ግልጽ የሆነው ብዙም ሳይቆይ ነበር።

በሺዎች የሚቆጠሩ ደቡብ ኮሪያውያን ውሳኔውን በጽኑ ተቃውመው ወደ ፓርላማ አምርተው ነበር። አንዳንዶች የሕንጻውን አጥር ጥሰው በመግባት እንዲሁም በአጥሮች ላይ ተንጠላጥለው ወደ ፓርላማው ለመግባት ሲሞክሩ ታይተዋል። በተቃዋሚዎች እና በፖሊሶች መካከል ግጭት መፈጠሩን አውስቶ ቢቢሲ ዘግቧል።

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# የዓለማችን መነጋገሪያ…

ከ5ኛው ገጽ የዞረ

**ኦክስፎርድ መዝገበ ቃላት ‘ክሪይፕቶከረንሲን’ እንዲህ ሲል ይገልጸዋል፤ የገንዘብ ልውውጦችን ደህንነት የሚያረጋግጥ፣ የተጨማሪ አሃዶችን መፈጠርን የሚቆጣጠር እና ገንዘብ መተላለፉን የሚያረጋግጥ ጠንካራ ክራፕቶግራፊ የሚጠቀም መገበያያ እንዲሆን ተደርጎ የተቀረጸ ዲጂታል ገንዘብ**

እንደ ፈረንጆቹ የዘመን አቆጣጠር በወርሀ ጥር 3 ቀን 2009፤ በዓለምአቀፍ የ2008 የፋይናንስ ቀውስ ሀንጎቨር ማግስት፤ ብዙም ትኩረት ያልሳበ የመጀመሪያው ክሪፕቶከረንሲ ቢትኮይን ተጸነሰ። ቢትኮይን የዲጂታል ክሪፕቶከረንሲ ወይም ገንዘብ ሲሆን፤ ግብይቱም ያለ ባንክ፣ ያለ መንግስት ያለ ፔይፓል ያለ የግል ኩባንያ ተሳትፎ የሚከናወን ነው። የሀሳቡ ዘፍጥረት ወይም ጄነሲስ ሳቶሺ ናካሞቶ በሚባል ሀሳብ አመንጪነት ሲሆን፤ በምስረታው የመጀመሪያ ዓመታት ሳቶሺ ንቁ ተሳታፊ ነበር። እንደ ባክ ካሉ የሙያ አቻዎቹ ጋርም በኢሜል ይገናኝ ነበር። ከ2011 በኋላ ድንገት ብን ብሎ ጠፋ።

የሚገርመው በሀንጋሪ ቡዳፔስት ሳቶሺ ናካሞቶ እንደ ሀገር ባለውለታ፣ እንደ ጀግና ሀውልት ቆሞለታል። በሀንጋሪ ለምን የሚለው ጥያቄ ዛሬ ድረስ መልስ አላገኘም። CBC News አንዲት እንስት ከሀውልቱ ጋር ሴልፊ የተነሳችውን ፎቶ በዘገባው አካቷል። ብዙም ሳይቆይ ስለ ሳቶሺ እውነተኛ ማንነት እዚህም እዚያም መረጃዎች መውጣት ጀመሩ። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ሳቶሺ የብዕር ስም ተደርጎ ነው የሚታመነው።

ከፍ ብሎ ለመግለጽ እንደተሞከረው ሳቶሺ ናቸው ተብለው ከሚጠረጠሩት አንዱ የሃሽካሽ ሀሳብ አፍላቂ አዳም ባክ ነው። በነገራችን ላይ በሳቶሺ የሀሳብ ማፍለቂያ ጹሑፍ የአዳም ባክ ስም ተጠቅሷል። አዳም ከቢትኮይን ሀሳብ አፍላቂዎች ከእነ ሳቶሺ፣ ሀል ፊንዪ እና ኒክ ዛቦ ጋር ኢሜል ሲለዋወጥ የነበረ መሆኑ ሳቶሺ ሳይሆን አይቀርም የሚል ጥርጣሬ አስነስቷል። በርካታ ሚዲያዎችም ይሄን ሀሳብ እየተጋሩት ይገኛል።

የTIME አምደኛ አንድሪው ቾው በሰሞነኛ የመጽሔቱ እትም፤ “A filmmaker’s quest to unmask Bitcoin’s creator” በሚል ርዕስ ባስነበበን መጣጥፉ ሳቶሺ ናካሞቶ በሚል username ባለቤትነት በ2009 የተፈጠረው ቢትኮይን እውነተኛ መስራች ማን ነው የሚለው ፍለጋ ወደ አዲስ ምዕራፍ ተሸጋግሯል ይለናል። የቢትኮይን አልያም የክሪፕቶከረንሲ አቀንቃኞች ለዓመታት የቢትኮይን ፈጣሪውን እውነተኛ ማንነት ለማወቅ በጥፍራቸው ቆመው ቢጠባበቁ፤ የምርመራ ጋዜጠኞች ለዓመታት የሳቶሺ ናካሞቶን እውነተኛ ማንነት ላይ ለመድረስ ቢማስኑም ሳይሳካላቸው ቀርቷል።

ከመቼውም ጊዜ በላይ የሳቶሺን እውነተኛ ማንነት የማወቅ ጉጉት ጨምሯል። አዎ እንደ ሀይማኖት ዓለምን እያዳረሰ ያለውን ቢትኮይንን ፋና ወጊ ሆኖ የመሰረተን ሰው ማንነት ማወቅ ለዚህ ትውልድ አጓጊ ነው። ይህ እውነተኛ ማንነቱ ሚስጥር የሆነ ሰው ያለው ቢትኮይን የ60 ቢሊየን ዶላር ጌታ እና የምድራችን 25ኛው ዲታ መሆኑ የሕዝበ አዳምን የማወቅ ጉጉት ጨምሮታል ይለናል አንድሪው።

በአናቱ ፕሬዚዳንት ትራምፕ በምርጫ ቅስቀሳቸው ክሪፕቶከረንሲን እንደሚደግፉና እንደሚያበረታቱ ቃል መግባታቸውና 47ኛው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ሆነው ዳግም ኋይታወስ መመለሳቸው ቢትኮይንን ጨምሮ የክሪፕቶከረንሲን ዋጋ ስላናረው የሳቶሺን እውነተኛ ማንነት የማወቅ ጉጉት ከምንጊዜውም በላይ ከፍ ብሏል።

ባለፈው ወርሀ ጥቅምት የኩሌን ሆባክ ዘጋቢ ፊልም ማለትም፤”Money Electric: The Bitcoin Mystery,”ማክሰ ላይ ሲለቀቅ የሳቶሺ ፍለጋ አከተመ።ሳቶሺ የ39 ዓመቱ ካናዳዊ የክሪፕቱ ሊቅ ፒተር ቶድ ነው።ሆኖም ለመጽሔቱ እኔ የምትሉት ሳቶሺ አይደለሁም በማለት ኢሜል አደረገ።

ፒተር ቶድን በቅርብ የሚያውቁ ቢትኮይነሮች ቶድን ሳቶሺ ነው ብለው ለመቀበል ይቸገራሉ። እነሱ የሚያውቁት ቶድ ኮድ የማድረግ አቅሙም ሆነ ባህሪው ለዚህ የሚታጭ ሰው አያደርገውም። ሆባክ ግን ግዴላችሁም እመኑኝ ሳቶሺ ቶድ ራሱ ነው እያለ ነው። በእርግጥ ሰዎች እነሱ ስኬታማ ይሆናል ብለው የሚጠብቁት ሰው ኅበዝና የተለይ ተሰጥኦ ያለውን ነው። ተወደደም ተጠላም ባለኝ መረጃ መሰረት ፒተር ቶድ ሳቶሺ ራሱ ነው።

ነገሩ ወዲህ ነው ይለናል TIME ነገርን ከስሩ ውሃን ከጥሩ እንዲሉ። ኩሌን ሆባክ የሳቶሽን ዳና የሚከተል ዘጋቢ ፊልም እንዲሰራ የጠቆመው የHBO ዋና አዘጋጅ አዳም ማክኬይ ነው። ሆባክ ከ2017 ዓ.ም ወዲህ በሴራ ኀልዮት የተለወሰ ለቀኝ አክራሪ የወገነ ሀሰተኛ መረጃን በመንዛት በአጭር ጊዜ ውስጥ ታዋቂ የሆነውን ኪውአኖን ወይም QAnon መስራች ማንነት የሚያጋልጥ ሰናጅ ፊልም በ2021 ሰርቶ እንደለቀቀ ነበር የHBO ዋና አዘጋጅ እንደዋዛ ቀጣዩ ስራህ የሳቶሽን እውነተኛ ማንነት አነፍንፈህ አደባባይ ማስጣት ነው ያለው።

ሆባክም አለቃው የሰጠውን የቤት ስራውን ለመወጣት ለተከታታይ ዓመታት ጥሯል። ግሯል። የሳቶሽን ዳና ተከትሎ ዓለምን ዞሯል። ከቢትኮይን ጋር ተያይዞ ስማቸው የሚነሱ ታዋቂ ሰዎችን በየሀገራቱ ዞሮ አነጋግሯል። ሆኖም ፍለጋው መና አልቀረም። ልፋቱም ከንቱ አልሆነም። በመጨረሻ የቢትኮይኑ ፈጣሪ ሳቶሺ እውነተኛ ማንነት ካናዳዊው የክሪፕቶከረንሲ ሊቅ ፒተር ቶዶ መሆኑን አረጋግጧል።

ለነገሩ ፒተር ቶድ ገና ከወጣትነቱ አንስቶ ዲጂታል ካሽ የመፍጠር ፍላጎት ነበረው። የተዋጣለት ኮደር ለመሆን ራሱን በራሱ ያስተማረ መሆኑና አቅሙም ከፍ ያለ መሆኑ ሳቶሺ ነው ቢባል አያስገርምም ይለናል የTIME መጽሔት አምደኛ አንድሪው ቾው። ሳቶሺ እምጥ ይግባ ስምጥ ከመሰወሩ ሁለት ቀን በፊት 2010 ላይ ቢትኮይን የበይነመረብ መወያያ ወይም ፎረም ላይ የቢትኮይንን ኮድ ቴክኒክ አስመልክቶ በጥቂት አንቀጾች የተቀነበበ ማብራሪያ ጹሑፍ ይለጥፋል። ወዲያው ፒተር ቶድ በግል ኢሜሉ ይገባና ይሄን ልጥፍ ያርማል።

የዚህ ጊዜ ነው ላካ የመጀመሪያው ልጥፍ የሳቶሺ ሳይሆን የፒተር ቶድ የራሱ ነበር የሚል ጥርጣሬ ያጫረው። ሳቶሺ ራሱ ፒተር ቶድ መሆኑ የተነቃው በሳቶሺ ስም የተለጠፈን ጹሑፍ በሳቶሺ ዩዘርኔም ማረም ሲገባው በስህተት በራሱ በፒተር ቶዶ ስም ገብቶ አርትኦት ማድረጉ እንዲጋለጥ አድርጎታል። ለዚህ ነው ሆባክ ደረቱን ነፍቶ እርግጠኛ ነኝ እመኑኝ ሳቶሽ ራሱ ፒተር ቶድ ነው የሚለን። ዘጋቢ ፊልሙ ላይ ሆባክ ይህን መረጃ ይዞ ፒተር ቶድን ሲሞግተው፤ ይሄ ተራ ልግጫ ሲል ጥያቄውን ያጣጥልበታል። ከፊቱ ላይ ይነበብ የነበረው መረበሽ ፍርሀትና መርበትበት ግን ሳቶሺ በእርግጥም ፒተር ቶድ መሆኑን ያሳብቃል። የዚህ ጊዜ መደምደሚያዬ ትክክል እንደሆነ ተሰማኝ ይለናል ሆባክ በአሸናፊነት መንፈስ።

ሆኖም ሳቶሺ እውነተኛ ማንነት ላይ ለመድረስ ያደረገው ጥረት ፈታኝ ከመሆኑ ባሻገር አደገኛ ነበር። የቢትኮይን ፈጣሪ እውነተኛ ማንነት እንዲደረስበት ከማይፈልጉ ደጋፊዎች በሚደርስበት ማስፈራሪያና ዛቻ የተነሳ ራሱን እስከመደበቅ ደርሶ እንደነበር ያወሳል። ክሪፕቶከረንሲን በአደባባይ በማገበያየት የሚታወቀው ኮይንቤዝ የቢትኮይን ፈጣሪ ሳቶሺ ፒተር ቶድ መሆኑን ይፋ አድርጓል። በአንጻሩ የቢትኮይን ደጋፊዎች የሳቶሺ እውነተኛ ማንነት በመጋለጡ HBO ላይ ቁጣቸውን እየገለጡ ይገኛሉ። ማንነቱ መታወቁ በመንግስታት ሊሳደድና ክስ ሊመሰረትበት፤ ሕይወቱም ለአደጋ ሊጋለጥ ይችላል እያሉ ስጋታቸውን እየገለጹ ይገኛሉ።

የቢትኮይንና የክሪፕቶከረንሲ ነገር ከተነሳ አይቀር ትንሽ እንበል።በጊዜ ሂደት እና በቴክኖሎጂ እድገትም የአኗኗር ዘያችን በፍጥነት እየተቀየረ መጥቷል። ለዚህም ማሳያ የሚሆነን ደግሞ ‘ዲጂታል ገንዘቦችን’ ለምርት እና አገልግሎት መገበያያነት ማዋል መቻላቸው ሊጠቀስ ይችላል። 21ኛው ክፍለ ዘመን ካስተዋወቀን የቴክኖሎጂ ምጡቅ ቃላት መካከል ብዙ እየተባለለት ያለው ‘ክሪይፕቶከረንሲ’ አንዱ ነው።

አክስፎርድ መዝገበ ቃላት ‘ክሪይፕቶከረንሲን’ እንዲህ ሲል ይገልጸዋል፤ የገንዘብ ልውውጦችን ደህንነት የሚያረጋግጥ፣ የተጨማሪ አሃዶችን መፈጠርን የሚቆጣጠር እና ገንዘብ መተላለፉን የሚያረጋግጥ ጠንካራ ክራፕቶግራፊ የሚጠቀም መገበያያ እንዲሆን ተደርጎ የተቀረጸ ዲጂታል ገንዘብ። ከላይ የተጠቀሰውን መስፈርት የሚያሟሉ በርካታ አይነት ክሪፕቶከረንሲዎች አሉ። በስፋት ከሚታወቁት መካከል ቢትኮይን፣ ኤቴሪያም፣ ሪፕል እና ቢትኮይን ካሽ የሚባሉት ከበርካታ ክሪፕቶከረንሲዎች መካከል ሊጠቀሱ ይችላሉ። በቅድሚያ የ’ዲጂታል ከረንሲውን’ ተቀላቅሏል ሚባልለት እና በስፋት በሚታወቀው ቢትኮይን ላይ ትኩረታችንን እናድርግ። ቢትኮይን ማለት በቀላል ቋንቋ፤ ዲጂታል ገንዘብ መገበያያ በማለት ማጠቃለል ይቻላል። ይህ መገበያያ በኪሳችን ተሸክመን እንደምንዞረው የብር ኖት ወይም ሳንቲም ሳይሆን ‘ኦንላይን’ የሚቀመጥ ዲጂታል ገንዘብ ነው። ሌላው የቢትኮይንና የተቀሩት የክሪይፕቶከረንሲዎች ልዩ ባሕሪ በመንግሥታት እና በባንኮች አለመታተማቸው እንዲሁም ቁጥጥር አለመደረጉ ነው።

ቢትኮይን የሚፈጠረው ‘ማይኒንግ’ በሚባል ሂደት ነው። በመላው ዓለም በኔትወርክ በተሳሰሩ ኮምፒውተሮች ቁጥጥር ይደረግበታል። ቢትኮይንን የፈጠረው ግለሰብ/ቡድን በዓለም ላይ 21 ሚሊዮን ቢትኮይኖች ብቻ እንዲፈጠሩ ገደብ እንዳስቀመጠ ይታመናል። የብሎክቼይን መረጃዎች እንደሚያሳዩት እስካሁን 17 ሚሊዮን ያህል ቢትኮይኖች ማይንተደርገዋል። እንደ ጎርጎሮሳውያን አቆጣጠር በ2018 የአንድ ቢትኮይን ዋጋ 10,031 የአሜሪካ ዶላር ነበር። ከአንድ ዓመት በኋላ ግን የአንድ ቢትኮይን ዋጋ ወደ 3,561 የአሜሪካ ዶላር ዝቅ ብሏል። ሰሞኑን ፕሬዚዳንት ትራምፕ 47ኛው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ሆነው መመረጣቸው የክሪፕቶከረንሲን ዋጋ አንሮታል። ዛሬ ላይ የአንድ ቢትኮይን ዋጋ ከ100 ሺህ ዶላር በላይ እያወጣ ይገኛል።

**ሻሎም ! አሜን×፲።**

# ስፖርት





## የከተማዋን የአትሌቲክስ ማዘውተሪያ ችግር ለመቅረፍ የተጀመረው ጥረት

ብርሃን ፈይሳ

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ክለቦች በርካቶቹ መቀመጫቸውን በአዲስ አበባ ከተማ እንደማድረጋቸው ከተማዋ የበርካታ አትሌቶች መዳረሻ ናት፡፡ ሀገርን በኦሊምፒክ እና የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና መድረኮች በድል ያስጠሩት እንደ አትሌት መሠረት ደፋር፣ ሚሊዮን ወልዴና ሌሎችም ጀግና አትሌቶች የከተማዋ ፍሬዎች ናቸው።ዛሬም ቢሆን የአትሌቲክስ ስፖርት ፍላጎትና አቅም ያላቸው በርካታ ታዳጊና ወጣቶች የነገን ስኬት አልመው በዝችው የአፍሪካ መዲና ይንቀሳቀሳሉ፡፡ ይሁን እንጂ ለልምምድም ሆነ ለውድድር ብቁ የሆነ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችን ማግኘት ለነዚህ አትሌቶች ፈተና ነው፡፡

የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች እጥረት ሀገራዊ ችግር ቢሆንም እንደ አዲስ አበባ ባሉ ከተሞች ደግሞ ካለው ፍላጎት አንፃር የጎላ ሆኖ ይታያል፡፡ በአንጻራዊነት ከተማ አስተዳደሩ ችግሮቹን ለመቅረፍ በየቦታው 3 በ 1 ሜዳዎችን እየገነባ ቢሆንም ካለው የታዳጊዎችና ወጣቶች ፍላጎት አንጻር በቂ አይደለም፡፡ ከዚህ ባለፈ በርካታ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁነቶችን የምታስተናግደው አዲስ አበባ ሀገር አቀፍም ሆነ አህጉር አቀፍ ስፖርታዊ ውድድሮችን በማስተናገድ ረገድ እንቅስቃሴዋ ደካማ የሚባል ነው፡፡

ኢትዮጵያ በዓለም ደረጃ በታወቀችበት የአትሌቲክስ ስፖርት ደግሞ ለልምምድም ሆነ ለውድድር ምቹ የሆኑ ጥርጊያ ሜዳዎች፣ የአሸዋ እና ደረጃቸውን የጠበቁ መሞች እንዲሁም ለሜዳ ተግባራት ስፖርቶች የሚሆኑ ሥፍራዎችን ማግኘት እየከበደ ነው፡፡ በፕሮጀክቶች የታቀፉና በየክለቡ የሚገኙ አትሌቶች በስፖርት አዘውታሪዎች በተጣበበው ጃንሜዳ ልምምድ ማድረግ አስቸጋሪ በመሆኑ ወደ መኪና መንገዶች ወጥተው አስፓልት ላይ በመሥራት ለአደጋ እየተጋለጡ ይገኛሉ፡፡

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ውድድሮችን በአዲስ አበባ ስታዲየም እድሳት እና በአበበ ቢቂላ ስታዲየም ለውድድር ብቁ ባለመሆን የተነሳ የኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ እያካሄደ ይገኛል፡፡ የአካዳሚው መም ደግሞ በብቸኝነት መሰል ኩነቶችን እያስተናገደ ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰበት ነው፡፡

ከዚህም ጋር ተያይዞ የአዲስ አበባ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን መፍትሄ ለማበጀት እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ የከተማው ፌዴሬሽን በተለይም በታዳጊ አትሌቶች ልማት፣ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች እንዲሁም ውድድርን በማዘመን ላይ ትኩረት አድርጎ እየሠራ ነው፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ ወሳኝ የሆነው የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች ችግር ለመቅረፍ የገቢ ማሰባሰቢያ መርሃግብር ከሰሞኑ አዘጋጅቷል። የገቢ ማሰባሰቢያው የሚውለውም ለመገንባት ለታቀዱት ሶስት ማዘውተሪያዎች ሲሆን፤ በጃንሜዳ ስፖርት ማዕከል ለውድድር ብቁ የሆነ የአሸዋ መም ቀዳሚው ነው፡፡ ባለ ስምንት መም የሆነው የአሸዋ መሮጫ ውድድሮችን በበቂ ሁኔታ ለማካሄድ ታስቦ ዲዛይኑ ሲዘጋጅም እስከ ስድስት ሚሊዮን ብር እንደሚፈጅ ታውቋል፡፡

ቀሪዎቹ የልምምድ ሥፍራዎች ደግሞ በጃንሜዳ የሚገነባ ሁለት ኪሎ ሜትር የአሸዋ ሜዳ እንዲሁም ለታዳጊ ፕሮጀክት ጥቅም እንዲሰጥ የታቀደው በወንድይራድ ትምህር ቤት ጊቢ ውስጥ የሚሠራ ነው፡፡ ለዚህም መቀመጫቸውን በከተማዋ ያደረጉ የአትሌቲክስ ክለቦች፣ ማናጀሮች እና ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት በመድረኩ ላይ ተገኝተው የድርሻቸውን አበርክተዋል፡፡ በጉልበት እና በሙያ ለማገዝ ቁርጠኝነታቸውን ከገለጹት ባለፈም 3 ሚሊዮን ብር ቃል ተገብቷል፡፡

በመድረኩ ከተገኙት መካከል ጀግናውን አትሌት ቀነኒሳ በቀለን ጨምሮ በርካቶችን ያፈራው አሠልጣኝ ጌታመሳይ ሞላ አንዱ ነው፡፡ የማዘውተሪያ ሥፍራዎች ችግር በተለይ በስፖርቱ ተሳታፊ ለሆኑ አካላት አሳሳቢ ጉዳይ በመሆኑ እገዛ ማድረግ እንደሚገባም ጠቁመዋል፡፡ በአንድ መም ላይ በርካታ አትሌቶች እየተጋፉ እየሠሩ ስፖርቱ ላይ ተጽእኖ እያደረሰ በመሆኑ ከፌዴሬሽኑ ጎን በመቆም ለመሥራት ዝግጁ መሆናቸውንም አሳውቀዋል፡፡

በኢትዮጵያ የአትሌቲክስ ስፖርትን በበላይነት የሚቆጣጠረው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የክልልና የከተማ አስተዳደሮች ፌዴሬሽኖችን ይደግፋል፡፡ ድጋፉ በሙያ በገንዘብና በቁሳቁስ እንደመሆኑም የአዲስ አበባ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ለተነሳበት የአትሌቲክስ ዓላማ አጋር በመሆን የድርሻውን በገንዘብ ለማበርከት ቃል ገብቷል። የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የፋሲሊቲ እና ማህበራት አገልግሎት ዳይሬክተር አቶ አሰፋ በቀለ፤ የሚገነባው የማዘውተሪያ ሥፍራ ለከተማዋ ብቻም ሳይሆን አትሌቶች ላሉባቸው አህጉራዊና ዓለም አቀፍ ውድድሮች ዝግጅት ሊያደርጉ የሚችሉበትና አሁን ላይ ላለው እጥረት ማስተንፈሻ ሊሆን እንደሚችልም ጠቁመዋል፡፡ በከተማዋ የሚገኙ ክለቦችና ማናጀሮችንም ጭምር ተጠቃሚ የሚያደርግ በመሆኑ ሌሎችም ይህንኑ አርዓያ መከተል እንዳለባቸውም አሳስበዋል፡፡

የከተማዋ ፌዴሬሽን በተተኪዎች እና ወሳኝ በሆነው የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች ላይ አተኩሮ እየሠራ መሆኑን የጽህፈት ቤት ኃላፊዋ ወይዘሮ እታፈራሁ ገብሬ ተናግረዋል፡፡ እንደ ኃላፊዋ ገለፃ፣ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽንን ጨምሮ በተለያዩ አካላት ድጋፍ እንዲሁም የከተማዋ ፌዴሬሽን ያስጀመራቸው የታዳጊ ፕሮጀክቶች በየክፍለ ከተማው አሉ፡፡ ይሁንና ለልምምድም ሆነ ለውድድር የሚሆኑ በቂ የማዘውተሪያ ሥፍራ የለም፡፡ ችግሩ የከተማው ብቻም ሳይሆን ሀገር አቀፍ ቢሆንም ሁሉም የአትሌቲክስ ባለድርሻ አካላት የተቻላቸውን ድጋፍ በማድረግ መፍትሄ ሊበጅ ይገባል፡፡